# አዲስ ልሳን

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ADDIS MEDIA NETWORK

ቅጽ 32 ቁጥር 3546 | ቅዳሜ ጥቅምት 29 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር







# መጠገን የሚሻው ስብራት

- ኢትዮጵያ ያለአግባብ ያጣችውን የባሕር በሯን የመጠየቅ ሕጋዊ፣ ፍትሐዊ እና ታሪካዊ መሠረት እንዳላት ተመላክቷል

**በመለሰ ተሰጋ**

ኢትዮጵያ ዐባይን እንደ መቀነት ታጥቃ፣ ቀይ ባህርን እንደ ጋቢ ተከናንባ፣ ብዙ ህዝብ፣ አያሌ ታሪክ እና እውነትን አንግባ እንዴት የባሕር በር አጣች? የሚለውን ስናስብ፣ የሆነብንና የሆነልን ሁሉ ሲተነተን ውስብስብነት አያጣውም።

በ1983 ዓ.ም ስልጣን የተቆጣጠረው ኃይል የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል እንዲፈርስ አደረገ። በዚያች ክፉ ቀን እንዲህ ሆነ፡፡ ጥቂቶች ግን ቆፍጣናዎቹ የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል አባላት የባሕር በራችንን አናስደፍርም ብለው ደንጎሎ ላይ አሸለቡ፤ በእምባትካላ ወደቁ፡፡ በምፅዋ እና በአሰብ ረገፉ፤ የተረፉትም በሳህል በርሃ ሞቱ። ብዙዎቹም ከሀገር በላይ ምንም! ብለው በየተራ ተሰው።

የሀገር ልጆች፣ እነዚያ የማር እጆች፣ በማወቅም ባለማወቅም በተተበተበ የሴራ ሰንሰለት ተጠለፉ፡፡ እነዚያ እንቁዎች፣ የሀገር ማገሮች፣ ጀግናና ገራገሮቹ፣ ባለ ሀገሮቹ ቀይ ባሕርን፣ አሰብ ወደባቸውን

ወደ ገጽ 3 ዞሯል




ፎቶ- ከገፀ ድር

ኢትዮጵያ አላግባብ ያጣችውን የባሕር በር ለማስመለስ እየሰራች ትገኛለች

## ከአክሳሪነት ወደ አትራፊነት



4

ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

በወንዝ ዳርቻ ልማት አዲስ ገጽታ የተላበሰው የግንፍሌ ወንዝ በከፊል

## ከማዝናናት የሚሻገረው የጥበብ ማዕከላት ሚና

10



ፎቶ- ከገፀ ድር

በቅርቡ የተመረቀው የአዲስ ሲኒማ ኮምፕሌክስ ዘመናዊ የሲኒማ ማዕከል ከፊል ገፅታ

## የኮከብነት ዘውዱን ማን ያጠልቀው ይሆን?

20



ፎቶ- ከገፀ ድር

ኮከብነቱን የማሸነፍ ዕድል የተሰጣቸው ቪክቶር ኦሲሚህን፣ ሞሀመድ ሳላህ እና አሽራፍ ሀኪሚ

# “በ2018 ዓ.ም የሀገራዊ ምክክሩ ቀሪ ስራዎችን ለማጠናቀቅ እቅድ ተይዞ እየተሰራ ነው”

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ሙሉጌታ አጎ



ፎቶ- ከፋይል

ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ሙሉጌታ አጎ

- ሀገራዊ ጉባኤ ማከናወንና በምክክሩ የሚገኙ ምክረ ሀሳቦችን ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ ከቁልፍ ስራዎች መካከል እንደሆኑ ተመላክቷል

**በስንታየሁ ምትኩ**

ኢትዮጵያ በዓለም ጥቁር ህዝቦች ዘንድ ደማቅ ታሪክ ያላት ሀገር ናት፡፡ በተለይም ህዝቦቿ የሀገር ሉዓላዊነትንና ነፃነትን በተጋድሎ አስጠብቀው በማስቀጠል ይታወቃሉ፡፡ ለዚህ ቀደምቶቻችን ካስመዘገቧቸውና ታሪክ እየዘከራቸው ከሚገኙት መካከል የዓድዋ እና የካራማራ ድሎችን እንደ አብነት መጥቀስ ይቻላል። የአሁኑ ትውልድም ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን በማጠናቀቅ በዓባይ ወንዝ ላይ ልማት የማካሄድ የዘመናት ህልምን ወደ ተግባር መቀየር ችሏል፡፡

ኢትዮጵያ እነዚህንና ሌሎች ወርቃማና አኩሪ የታሪክ ውርሶች፣ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥርና ትልቅ

ወደ ገጽ 5 ዞሯል






# ብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድን

- ሲከታተሉ የቆዩ ከ8 ሺህ 800 በላይ የመጨረሻ ዙር ተሳታፊ ወጣቶች ነገ ልምምዳቸውን ያጠናቅቃሉ
- በዓለም ባንክ የጋራ ትብብር ሲፈፀም የቆየውን መርሃ ግብር ተሞክሮ በመውሰድ በራስ አቅም ተፈፃሚ ለማድረግ ታቅዷል

**በደረጀ ታደሰ**

የሠው ልጅ ከህፃንነት እስከ እርጅና ባለው የሕይወት ጉዞ ውስጥ ሲቆይ፤ በሁሉም ምዕራፍ የራሱን ልዩ ለዛ ያገኛል፡፡ ይሁን እንጂ የወጣትነት ዕድሜ ክልልን የመሰለ ልዩ ተፈጥሯዊ ጸጋ የሚላበስበትን ዘመን የመሰለ የለም፡፡ በወጣትነት

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

አድራሻ +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## የወንዝ ዳርቻ ልማቱን መንከባከብ የጋራ ስራን ይጠይቃል!

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እንብርት፣ የዓለም አቀፍ ተቋማት፣ የተለያዩ ሀገራት ኤምባሲዎች፣ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ እና የአፍሪካ ሕብረት ዋና መቀመጫ ናት፡፡ በዚህ ልክ የገዘፈ ኃላፊነት የተሸከመችው ይህች ከተማ ለበርካታ ዓመታት ከስምና ዝናዋ በታች ኖራለች፡፡ እንደ እድሜዋ ያልዘመነች እና ለነዋሪዎች ምቹ ያልሆነች ከተማ እየተባለችም ተተችታለች፡፡

አሁን አሁን ግን መልካም የለውጥ እንቅስቃሴዎች ይታዩባት ጀምሯል። የኮሪደር ልማት ስራው በአጭር ጊዜ ውስጥ ጉስቁልናዋን በማከም እንደስሟ ውብና የምትናፈቅ አበባ እያደረጋት ይገኛል፡፡ በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ዙር የተከናወኑት የኮሪደር ልማት ስራዎች የከተማዋን በርካታ ክፍሎች ገፅታ አሻሽለዋል፤ በተለይ ፒያሳ፣ አራት ኪሎ፣ መገናኛ፣ ሲ.ኤም.ሲ፣ አያት፣ ሜክሲኮ፣ ሳር ቤት፣ ጋርመንት፣ ለቡ፣ ሽሮ ሜዳና ቦሌ መስመርን የመሳሰሉ የከተማዋ ክፍሎች ውብ ገፅታን ተላብሰዋል፡፡ ሳቢና ማራኪም ሆነዋል፡፡

የኮሪደር ልማቱ የፈጠረው ይህ አዲስ ገፅታ በወንዝ ዳርቻ ልማቱ ሲደገፍ የከተማዋን መልክ በእጅጉ ይቀይረዋል፤ ስምና ዝናዋን ያልቀዋል፡፡ አሁን እየተስተዋለ ያለውም ይኸው ነው፡፡ ከእንጦጦ ተራሮች ተነስቶ በከተማዋ በኩል አልፎ አቃቂ ወንዝ ድረስ በሚጓዝና በአጠቃላይ ከ45 ኪሎ ሜትር በላይ በሚሸፍን ትልቅ ወንዝ ላይ የተጀመረው የወንዝ ዳርቻ ልማት ለነዋዎች የዓመታት ጥያቄ ምላሽ የሰጠ ያደርገዋል፡፡

ከእንጦጦ ተራራ በጉለሌ በኩል አፍሪካ ህብረት እንዲሁም ከእንጦጦ በአፍንጮ በር፣ በባንቢስ አድርጎ አቃቂ የውሃ ማጣሪያን በሚሸፍነው ፕሮጀክት በውስጡ 28 የሚደርሱ ድልድዮች፣ ሰው ሰራሽ ሐይቆች፣ አረንጓዴ ቦታዎች፣ የመዝናኛ ማዕከላት፣ የውኃ ትራንስፖርት እና የንግድ ማዕከላት ይገነቡበታል። ለእግር ጉዞና የመሮጫ ትራኮች፣ የብስክሌት መስመሮች፣ ኬብል ካር ትራንስፖርት (የገመድ ላይ መኪና)፣ መዝናኛ ግድቦችን ይይዛል፡፡ ፕሮጀክቱ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ የከተማዋን ነዋሪዎች ደህንነት በማሻሻልና የከተማዋን ሳቢነት ይበልጥ በመለወጥ ረገድ ብዙ ሚና ከመጫወቱ በተጨማሪ የተለያዩ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ መስህቦች እንዲሁም ለጎብኚዎች የእረፍት ጊዜ ማሳለፊያ ስፍራዎችን በማዘጋጀት የውጪ ሀገርና የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ወደ አዲስ አበባ መሳብ ያስችላል፡፡

በተጨማሪም ለከተማዋ ነዋሪዎች ቋሚ የስራ ዕድል መፍጠር፤ የአገልግሎት ዘርፉን በማበረታታት ካፌዎች፣ ምግብ ቤቶች፣ የከተማ አስጎብኚዎችና የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ማመቻቸት፣ የተፋሰስ ወንዞች ዳርቻ እና ፕሮጀክቱ ዳርቻ ያሉና ወደፊት የሚገነቡ የሪል ኢስቴት ፕሮጀክቶችም የዕቅዱ አካል ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ስራዎች ታዲያ ለመዲናዋ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ጉልበት ይሰጣሉ፡፡

በወንዝ ዳርቻ ልማቱ ሳቢያ የፍሳሽ አወጋገድ ስርዓት ይሻሻላል፤ ፅዳት ይረጋገጣል፣ የወንዞች ብክለትና ጎርፍ ችግር በመቃለሉ የድንገተኛ አደጋዎች ስጋት ይቀንሳል፤ ከተማዋ ምቹ የመኖሪያ ከባቢ ትሆናለች፤ በጥቅሉ በወንዞች ብክለት ሳቢያ በነዋሪዎቹ ተደጋግመው ይነሱ የነበሩ የጤና፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በፍጥነትና ዘላቂነት ባለው መልኩ እየተፈቱ ይሄዳሉ፡፡ በመሆኑም የወንዝ ዳርቻ ልማት ከአንድ ከተማ እድገትና ጤናማ የነዋሪዎች ህይወት ወሳኝ እንደመሆኑ የከተማ አስተዳደሩ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራበት ይገኛል፤ የጥረቱ ፍሬም በግልፅ መታየት ጀምሯል፡፡

በተለያየ መንገድ ወንዞችን የሚበክሉ አካላት ማለትም የአምራች ተቋማት፣ የአገልግሎት ሰጭ፣ የግለሰብ መኖሪያ ቤት እና የመንግስት ተቋማት በድምሩ 17 ሺህ 516 አካላት ልየታ ስራ መከናወኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ እነዚህ የተለዩት ተቋማት እና ግለሰቦች ችግሩን የሚያስወግዱበትን መንገድ እንዲያበጁ እየተደረገ ነው። ሁሉም ሊገነዘበው የሚገባው ጉዳይ የወንዝ ዳርቻ ልማቱን መንከባከብ የጋራ ስራን የሚጠይቅ መሆኑን ነው፤ በመሆኑም በከተማ አስተዳደሩ ከሚደረገው ወንዞችን ከብክለት የመጠነቅ ጥረት ባሻገር ሁሉም የከተማዋ ነዋሪ በባለቤትነት መስራት ይገባዋል፡፡

# የእኔ እይታ

**ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።**

## ከግለሰብ የተሻገረው ተፅዕኖ

**በሰናይ ምግባሩ**

የአገልግሎት አሰጣጥ የከተማ ብቻም ሳይሆን የሀገር ፈተና ሆኖ ከቀጠለ ሰነባብቷል፡፡ ተገልጋዮችም ያጋጠሟቸውን ፈተናዎች አብነት በማድረግ መፍትሔ ይበጅለት ዘንድ ሲወተውቱ ይደመጣል፡፡ ሰራተኛው በሰዓቱ ስራ ገበታው ላይ አይገኝም፣ ተገልጋዩ እያለ እና ሰዓትም እያለው አስቀድሞ ወጥቶ ይሄዳል የሚሉት ደግሞ ከሚነሱት ቅሬታዎችና አቤቱታዎች መካከል ናቸው። መንግስትም ይህን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የተለያዩ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ለዚህ ሁነኛ ማሳያ ነው። እነዚህን እና መሰል መፍትሔ አዘል ርምጃዎችን በቀጣይም አጠንክሮ ማስቀጠል ይገባል ብየ አስባለሁ፡፡

ለዚህ መነሻ የሆነኝ ለመንግስት ሰራተኞች በስራ መውጫና መግቢያ ሰዓት የትራንስፖርት አገልግሎት ስለሚሰጡት አውቶቡሶች ጉዳይ ነው፡፡ በተለይ በቅርብ ዓመታት ለተጠቃሚዎች የተላለፉ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ባሉባቸው እንደ ቦሌ አራብሳ ባሉ አካባቢዎች ያለው ነገር ተገቢውን ትኩረት የሚያሻ ነው፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች ከተጠቃሚው ቁጥር ማድግ የተነሳ በአውቶቡሶቹ መቀመጫ ወንበር ለማግኘት ሰዎች ከንጋቱ 10፡20 ሰዓት ጀምሮ ወረፋ ለመያዝ ይሰለፋሉ። ከሰዓት በኋላም እንዲሁ ከቀኑ 10፡00 ሰዓት ጀምሮ ለተመሳሳይ ተግባር ከቢሮ ይወጣሉ። ይህ ግለሰቡን ብቻም ሳይሆን የሚሰራበትን ተቋምም ለችግር ያጋልጣል፡፡

ለዚህ ጽሁፍ ግለሰቡ ላይ ያለውን ተጽዕኖ እንተወውና በተቋም አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት በሁለት መልኩ ለማየት ወደድኩ። አንደኛው ወንበር ለማግኘት ሲል በሌሊት የሚመጣው ሰው ተግባሩን በድግግሞሽ ሲፈጽም ምን ያህል በቂ እረፍት ሊያጣ እንደሚችል ከግምት እናስገባ፡፡ ዘግይቶ በመምጣቱ ረጅም ርቀት ቆሞ ለመሄድ የተገደደውም በተመሳሳይ በአካል የመዳከም ሁኔታ ውስጥ መግባቱ አይቀሬ ነው፡፡ በዚህ ስሜት ውስጥ ሆኖ በተቋሙ ውስጥ አገልግሎት ለመስጠት መሞከር ተነሳሽነትን ይቀንሳል፤ በተገልጋይ ጫማ ቆሞ ለማየትም ሊቸገር ይችላል፡፡ ከሰዓት በኋላም አስቀድሞ እንዲወጣ ገፊ ምክንያት ስለሚሆነው ተገልጋዮችን ለተጨማሪ መንገላታት ይዳርጋል፡፡ ጊዜውን ለዚህ አገልግሎት መድቦ እና የትራንስፓርት ወጪ አውጥቶ ለአገልግሎት የመጣው ባለጉዳይ በተጠቀሰው ምክንያት ለቀጣዩ ቀን እንዲመጣ ቀጠሮ ሲሰጠው የሚፈጥረውን ስሜት መገመት አያዳግትም፡፡

ለአገልግሎት አሰጣጡ አንዱ ወሳኝ ጉዳይ የሰው ኃይል መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ይህን ሀይል ለአገልግሎት ዝግጁ ማድረግ ደግሞ የመንግስት አንድ አካል መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ለዚህ ትራንስፖርቱን የማመቻቸቱ ጉዳይ በጥንካሬ የሚወሰድ ሆኖ አቅርቦቱን በቁጥር ማሳደግ፣ ያሉትንም ቁጥሩን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የድልድል ስራውን በየግዜው እያጠኑ እና እየከለሱ መሄድ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ይህን የሚመለከተው አካል ጉዳዩን በዚህ መነፅር አይቶ ሁነኛ መፍትሔ መስጠት አለበት ብየ አስባለሁ፡፡

ከዚህ ጎን ለጎን በየተቋማቱ በየደረጃው ያሉ ኃላፊዎች ሰራተኞቻቸው በዚህ ሰበብ ከስራ አስቀድመው እንዳይወጡ ተገቢውን ክትትል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በእርግጥ በአንድ ሰሞን እንዲህ ለማድረግ ተሞክሮ ነበር፤ ምንም እንኳን ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ ባይቻልም፡፡ ሰራተኛውም ቢሆን እንጀራ የሚበላበትን ስራ አክብሮ፣ ጊዜውን በአግባቡ በመጠቀም እሱን ፈልገው የሚመጡ ሰዎችን ተቀብሎ በአግባቡ የማስተናገድ ግዴታ እንዳለበት በመረዳት ለተፈጻሚነቱ መትጋት ይኖርበታል ባይ ነኝ፤ እናንተስ ምን ትላላችሁ?

ADDIS MEDIA NETWORK
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜልባ ፕሪንቲንግ ፐብሊሺንግ ኤንድ ፓኬጂንግ ሼር ካምፓኒ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ለይላ መሀመድ
አብርሃም ገብሬ
ፋንታነሽ ተፈራ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
ይግለጡ ጓዴ
ሄለን ጥላሁን

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለሰ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# መጠገን ... ከገጽ 1 የዞረ

የባሕር ድንበራቸውን በስስት እና በመራር ጀግንነት እየተመለከቱ የሀገር ፍቅርን በንግግር ሳይሆን በተግባር እየተረኩ ነጎዱ፤ ያን ክፉ ቋጠሮ ዘመን እስኪገለጠው ትውልድ እስኪፈታው፡፡

አዎን፣ ኢትዮጵያ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን በ1948 ዓመተ ምህረት የተቋቋመና እስከ ደርግ ዘመን ማብቂያ የቆየ የባሕር ኃይል ነበራት፡፡ በቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን የአሜሪካና የሩሲያን መርከቦች ጎን ለጎን ያሰለፈ፣ ጥቂት ግን ውጤታማ ሲል ዓለም የመሰከረለት፣ ከራስ ካሳር እስከ ራስ ዱሜራ ያለውን የውሃ ክልል በልሕቀት ያስከበረ ቆፍጣና የባሕር ኃይል ነበራት፡፡

የቀድሞው የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል መርከበኛ፣ የሕክምና ባለሙያ፣ ገጣሚና ተርጓሚ ሊዲንግ ሲማን አለማሁ ማሞ 'ጥቂቶቹ' በተሰኘ መፅሐፋቸው እንዲህ አሉ፡፡ "መዋኛ ገንዳ ውስጥ ስገባ ይሁን ጀልባና መርከብ ላይ በወጣሁ ቁጥር ባሕረኞች ባልደረቦቼን አጠገቤ እንዳሉ አድርጌ እዘክራቸዋለሁ፡፡"

የቀድሞው የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል ሰራዊት የቃል ኪዳን ሕብረ ዝማሬ በተለያዩ መድረኮች አሊያም በማህበራቸው መታሰቢያ መርሃ ግብሮች 'መልህቅ ዓርማዬ ቀይ ባሕር ቤቴ ጀግንነት ውርሴ ያባት ያያቴ' የሚለው ዝማሬ ሲሰማ ከልብ የፈለቀ የሚያቃጥል ዕምባ እንደ ዥረት ሲወርድ ይታያል፡፡

በእርግጥ በማይገባ መልኩ ከቀይ ባሕር የራቅንበት በተለይም የአሰብ ወደብን ያጣንበት መንገድ በግለሰብ ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገር ሊዘከር ይገባው ነበር። ግን ከለውጡ በፊት በነበረው መንግስት ይህ ፈፅሞ ሊታሰብ ይቅርና አጀንዳውን በተለያዩ መድረኮች ያነሱ ምሁራን ይታሰሩ አሊያም ይሰደዱ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡

የዓለም ሕግና ታሪክ ግን የሚነግረን ከዚህ ባሻገር ያለውን ደማቅ እውነት ነው። ለአብነትም የደቡብ አሜሪካዋ ሀገር ቦሊቪያ፣ እ.ኤ.አ ከ1879 እስከ 1884 በቆየው ፓስፊክ ጦርነት፣ የፓስፊክ የባሕር ዳርቻዋን እና የወደብ ከተማዋን አንቶፋጋስታ በቺሊ ካጣች በኋላ ወደብ አልባ ሀገር ሆነች።

ይህም ታሪካዊ ኪሳራ ብሔራዊ ቁጭት፣ ሰቀቀን እና ትዝታ፣ ትዝታም ብቻ ሳይሆን መልሶ የማግኘት ወኔን በሚቀሰቅስ መልኩ ቦሊቪያውያን ሁሌም መጋቢት 23 ቀን "ዲያ ዴል ማር" ወይም "ብሔራዊ የባሕር ቀን" እያሉ ለ146ኛ ጊዜ ባሕር ያጡበትን ቀን እያከበሩት ነው፡፡ አዎ ቦሊቪያ በደቡብ አሜሪካ የባሕር በር ከሌላቸው ሁለት ሀገራት አንዷ ናት፡፡ ነገር ግን በየዓመቱ መጋቢት 23 ቀን የምታከብረው ይህ በዓል ቺሊ በጦርነት የነጠቀቻትን 250 ማይል የፓስፊክ የባሕር ዳርቻን እያስታወሰች "ታሪካዊ ኢ ፍትሐዊነትን" ትዘክርበታለች፤ ትሞግትበታለች። ዜጎቿንም ተፈጥሮ የለገሰቻቸውን ኢ ፍትሐዊነት የነጠቃቸውን የባሕር በር ለማስመለስ የሚደረገውን ሁለንተናዊ ጥረት እንዲያግዙ ታበረታታበታለች፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር

ኢትዮጵያ አላግባብ ያጣችውን የባሕር በር ለማስመለስ እየሰራች ትገኛለች

ታይም መፅሔት እ.ኤ.አ ጥቅምት 3 ቀን 2018 "ላንድሎክድ ቦሊቪያ ወንትስ ኤ ፓዝ ቱ ዘ ፓሲፊክ" (Landlocked Bolivia Wants a Path to the Pacific) በሚል ርዕስ ባሰፈረችው ሰፋ ያለ ትንታኔ በዚሁ ዓመት ጥቅምት 1 ቀን የተባበሩት መንግስታት ዓለም አቀፍ የፍትህ ፍርድ ቤት (ICJ) ቺሊ ለጎረቤቷ ቦሊቪያ ወደ ባሕር የሚያደርስ መንገድ እንድትሰጥ ለማስገደድ ውሳኔ አስተላልፏል። በዋና ከተማዋ ላ ፓዝ በሚገኙ ትላልቅ የከተማ አደባባዮች ዙሪያ የተሰበሰቡ የቦሊቪያ ነዋሪዎችም እ.ኤ.አ ከ1879 ጀምሮ ባልተገባ መልኩ ያጡት የባሕር በራቸው ብሶት ውስጣቸውን እየለበለበው ቢሆንም ውሳኔውን ልብን በሚፈነቅል የደስታ ስሜት ተመልክተውታል ይላል የታይም ዘገባ፡፡

እናም ፍርደ ገምድል የሆነው ዓለም ፊቱን እስኪያዞር፣ አሊያም ዘመን የወሰደውን ዘመን እስኪመልሰው እና ትውልድ እስኪያድሰው ቦሊቪያ እ.ኤ.አ በ1963 ከአሜሪካ እና ከቻይና የተጣሉ መርከቦችን በመጠቀም "አርማዳ ቦሊቪያና" በሚል ስያሜ የባሕር ኃይሏን መስርታለች፡፡ ከ5 ሺህ በላይ ወታደሮቿም በአማዞን እና በቲቲካካ ሐይቅ ላይ በሚደረጉ ልምምዶች ይሳተፋሉ። እንዲሁም የቦሊቪያን የወንዝ ድንበሮች ከብራዚል፣ ከፓራጓይ እና ከአርጀንቲና ጋር ይጠብቃሉ። እንደ ታይም መፅሔት ዘገባ ቦሊቪያ በዓለም አቀፍ ባሕር ሕግም፣ በጂኦፖለቲካል እሳቤም በታሪክ እና በምጣኔ ሀብታዊ ምልከታም ወደብ የማግኘት መብት አላት፡፡

ኢትዮጵያ ደግሞ ያጣችው በዓለማችን የንግድ፣ የፖለቲካ እና መሰል ጉዳዮች መለኪያ 'የዓለማችን እስትንፋስ አሊያም ጉሮሮ' የሚባለውን ቀይ ባሕርን ነው። ለአብነትም የቀይ ባሕርና አካባቢ የዓለማችን ከ30 በመቶ በላይ የንግድ ልውውጥ የሚደረግበት፣ ኃያላኑ ባለው ጂኦፖለቲካል ፋይዳ የጦር ካምፖቻቸውን የመሰረቱበትና ጦራቸውንም የሚያርመሰምሱበት፣ የሚሻኮቱበት፣ ጡንቻ የሚለካኩበት ነው፡፡

እናም የሀገሬ ሰው "በፍርድ ከሄደች በቅሎዬ፣ ያለፍርድ የሄደች ጭብጦዬ" እንዲል፣ ያለ ፍርድ አሊያም ያለ አግባብ ያጣነውን የባሕር በራችንን መጠየቅ ሕጋዊም፣ ፍትሐዊም መሆኑን የቦሊቪያ ታሪክ ምስክር ነው፡፡ ከሦስት አስርት ዓመታት በላይ የባሕር በር አልባ ሆና የቆየችው ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር በኩል የባሕር መተላለፊያ ማግኘት አለባት የሚል ቆራጥና ትክክለኛ አቋም የያዘው የለውጡ መንግስት በተደጋጋሚ ፍላጎቱን ሲገልጽ ቆይቷል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በ6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ "ኢትዮጵያ የማይናወጥ ብሔራዊ ጥቅም አላት፤ ዓለም ዛሬ ይስማ... የቀይ ባሕር በር ኢትዮጵያ ያስፈልጋታል፤ በማንኛውም ህግ ኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ይገባታል፤ ብዙዎች እኮ ነውር ነው ይላሉ፤ 120 ሚሊዮን ህዝብ ላይ ባሕር እንዳያይ መቆለፍ ትክክል አይደለም፡፡" በማለት ጉዳዩን በአፅንኦት መግለፃቸው የዚሁ ማሳያ ነው፡፡

በቀይ ባሕር ክልል ወሰነ-ሰፊ ይዞታ የነበራት ኢትዮጵያ፣ በየዘመናቱ ህዝቦቿ በከፈሉት መሪር መስዋዕትነት ነፃነቷንና ክብሯን ጠብቃ የኖረች ሀገርም ነች። አዱሊስ፣ ዘይላ እና ምፅዋ ወደቦችም በኢትዮጵያ ግዛት ሥር እንደነበሩ በርካታ የታሪክ ሰነዶች ያረጋግጣሉ። ለአብነትም ያዕቆብ ኃ/ማርያም (ዶ/ር) በመስከረም ወር 2004 ዓ.ም "አሰብ የማን ናት?" በሚል ርዕስ ለህትመት ያበቁትን መጽሐፍ መጥቀስ እንችላለን፡፡

ደራሲው በመጽሐፋቸው እንደ ሀገር ከቀይ ባሕር የተገለልንበት መንገድ ኢ ፍትሐዊ መሆኑን በዓለም አቀፍ ሕግጋትም ተመልሰን የማግኘት ግልፅ መብትና እውነት እንዳለን ገልፀዋል፡፡ በሌላ በኩልም "የኢትዮጵያን የባሕር በር (አሰብን) ማስመለስ የሁሉም የሀገሪቱ ዜጋ ብሔራዊ ግዴታ ነው፤ ይህም እንዲሆን እያንዳንዱ ዜጋ አቅሙ የሚፈቅደውንና የሚችለውን እንዲያደርግ" ሲሉም ይማፀናሉ፡፡

ኢትዮጵያ በታሪኳ ያለፈቻቸው መነሳትና መውደቅ ከባሕር ጋር ከነበራት ቅርበትና ርቀት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው። የባሕር በሮቿ በእጇ በነበሩበት ዘመን የጎለበተችና የበለፀገች ኢትዮጵያን መመስረት ተችሏል። በአንፃሩ የባሕር በሯን በተነጠቀችባቸው ዘመኖች ኢኮኖሚዋ የኮሰሰ፣ ፖለቲካዋ የተናጋ ኢትዮጵያን በተደጋጋሚ አይተናል።

ያዕቆብ ኃ/ማርያም (ዶ/ር) በቀጣናው በህዝብ ብዛት ቁጥር ግዝፈቷና ለባሕር ባላት ቅርበት የመጀመሪያ የሆነችው ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ሀገር መሆን እንደማይገባት ነው በመጽሐፋቸው በብርቱ የሚሟገቱት። የሙግታቸው ዋነኛ ትኩረትና ማነጣጠሪያቸው አሰብ ወደብ ነው። በአልጀርሱ ሥምምነት፣ የአሰብ ወደብ ባለቤትነት መብቷን የምታስከብርበትን መልካም አጋጣሚ መጠቀም አለመቻላችን የሚያስቆጭና በወቅቱ የነበረውን ሴራ የሚያመላክት ስለመሆኑም ጠቁመዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በ6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ይህን ጉዳይ አንስተው አብራርተዋል። በማብራሪያቸውም፣ የኢትዮጵያን የቀይ ባሕር ድንበርተኝነት ያሳጣው ውሳኔ በማን እንደተወሰነ የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ አለመገኘቱን ጠቅሰው፣ ውሳኔው ሕጋዊ እንዳልሆነ አመላክተዋል፡፡

ታድያ እንዲህ ያለው ጉዳይ ከህግ አግባብ እንዴት ይታያል ያልናቸው የህግ ባለሙያው አቶ ኪያ ፀጋዬ፣ በወቅቱ የነበረው የሽግግር መንግስት እንደመሆኑ የባሕር በርን በሚያህል ጂኦ እስትራቴጂካዊ ጉዳይ ላይ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን የለውም፡፡ ስለዚህ ውሳኔው ህጋዊ መሠረት የለውም በማለት ጉዳዩን አብራርተዋል፡፡

የህግ ባለሙያው በማብራሪያቸው፣ እንዲህ ያለውን ውሳኔ ለማሳለፍ የሚችል ህጋዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስት ባልተመሰረተበት ሁኔታ ነው ኢትዮጵያ የባሕር በሯን ያጣችው፤ ተቀባዩም ሆነ ሰጪው ከጫካ የመጡ የጋራ ዓላማ የነበራቸው ናቸው፡፡ ኢትዮጵያዊ ውግንና ቢኖራቸው ኖሮ በሺህ ኪሎ ሜትሮች የሚቆጠር ርዝመት ያለው የባሕር በር ያላትን ሀገር በአንድ ጀንበር ዝግ አያደርጓትም ነበር። ስለዚህ ህዝብ ተወያይቶ ያልደረሰበት ስምምነት እና በህዝብ የተመረጠ መንግስት በሌለበት የተላለፈ ውሳኔ በመሆኑ ህጋዊ መሠረት እንደሚያሳጣውም ጠቅሰዋል፡፡

# ከአክሳሪነት ወደ አትራፊነት

- **በወንዝ ዳርቻ ልማቱ በእንጦጦ አካባቢ ብቻ እስካሁን 438 ሄክታር ቦታ ላይ የተፈጥሮ ጥበቃ ሰራ መሰራቱ ተጠቁሟል**

**በሳህሉ ብርሃኑ**



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል
በወንዝ ዳርቻ ልማት አዲስ ገጽታ የተላበሰው የግንፍሌ ወንዝ በከፊል

ወንዞች ለሰው ልጆች ዋነኞቹ የውኃ ምንጮች እና የአየር ንብረት ለውጥን በመዋጋት ረገድም ወሳኝ አጋሮች ስለመሆናቸው ጣሊያናዊው ደራሲ ፓስኳሌ ደ ማርኮ ‘ዳይቪንግ ኢንቱ ሪቨርስ፡- ዘ ኮምፕሌት ጋይድ ቱ ሪቨር ሄልዝ ኤንድ ሬስቶሬሽን’ (Diving into Rivers: The Complete Guide to River Health and Restoration) በሚል ርዕስ ያሳተሙት መጽሐፍ ያትታል፡፡ ወንዞች ከውሃ ምንጭነት ባሻገር በአግባቡ ከለሙ ያላቸው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳም ከፍተኛ ስለመሆኑ ደራሲው ያስረዳሉ፡፡

የወንዝ ዳርቻቸውን አልምተው የከተማቸውን ገጽታ የቀየሩ ሀገራት ተመክሮውም የሚያረጋግጠው ይህንኑ ሀቅ ነው፡፡ ለዚህ ጉዳይ ማረጋገጫ ፍለጋ በሴኡል እምብርት ወደምትገኘው የቼንግጊቼዮን ወንዝ አቅንተን ማስረጃ እንጥቀስ፡፡ የቼንግጊቼዮን የወንዝ ልማት ወንዙን ከሞት ማስነሳት ብቻ ሳይሆን በከተማዋ ጥቅጥቅ ባለው የአረንጓዴ አካባቢ አማካኝነት የከተማዋን ሥነ-ምህዳራዊ የደም ቧንቧ እንደገና አቋቁሟል ይባልለታል።

እ.ኤ.አ ከ2003 እስከ በ2008 መካከል በተሰራው ስራ አጠቃላይ የብዝሃ ህይወት በ639 በመቶ ጨምሯል። በዚህም በወንዙ ዙሪያ የዕፅዋት ዝርያዎች አይነት ከ62 ወደ 308 ሲያድግ፣ የዓሣ ዝርያዎች ከ4 ወደ 25፣ የወፍ ዝርያዎች እንደዚሁ ከ6 ወደ 36 ከፍ ብሏል። 120 ሚሊዮን ዶላር የወጣበት ይህ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ 100 ሄክታር የሸፈነ አስደናቂ የአካባቢ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን አስገኝቷል፡፡

በተለይም በኢኮኖሚው ረገድ በወንዙ አቅራቢያ ባሉ የመሬት እሴቶች ላይ ከፍተኛ ጭማሪ በማሳየት የኢኮኖሚውን እንቅስቃሴ አነሳስቶ የቼንግጊቼዮን አካባቢን አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አሳድጓል። ለዚህም ሁለት ማሳያዎችን እናንሳ፡፡ አንደኛው ስራው በጠናቀቀ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ብቻ በቼንግጊቼዮን አካባቢ የነበረው የንግድ እንቅስቃሴ በ3 ነጥብ 5 በመቶ የጨመረ ሲሆን፣ በሌላም በኩል በወንዝ ዳርቻ ልማቱ ዙሪያ 50 ሜትር ርቀት ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች የመሬት ዋጋቸው ከልማቱ በኋላ ከ30 እስከ 50 በመቶ ጨምሯል ይላል በጉዳዩ ላይ ጥናት ያደረጉት በደቡብ ካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ ረዳት ፕሮፌሰሩ አሌክሳንደር ሮቢንሰን ግኝት፡፡

በተጨማሪም ፕሮፌሰር አሌክሳንደር በጥናት አረጋግጬዋለሁ ባሉት መሰረት የወንዝ ልማት ስራው በየቀኑ በአማካይ 64 ሺህ ጎብኝዎችን የሚስብ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ 1 ሺህ 408ቱ ደግሞ የውጭ ሀገር ጎብኚዎች ናቸው፡፡ በዚህም በሴኡል ከተማ ኢኮኖሚ ላይ የውጪ ጎብኚዎች እስከ 1 ነጥብ 9 ሚሊዮን ዶላር ድረስ አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው አስችሏል፡፡ በጥቅሉም ወንዙን ወደቀደመ ማንነቱ የመመለስ ስራው ዘላቂ የከተማ መልሶ ማልማት ምልክት ሆኖ በመቆሙም የስነ-ምህዳራዊ መርሆችን ከከተሞች መሠረት ልማት ጋር በማቀናጀት ከተሞችን እንዴት እንደሚያነቃቁ ማሳያ ተደርጎም ይወሰዳል፡፡

አሲሲዮና ገጸ ድር ወንዞችን አስመልክቶ ያወጣው መረጃም የሚያጠናክረው እውነት ወንዞችን ማልማት ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ አለመሆኑን ነው። በዓለም ላይ ከ2 ቢሊዮን በላይ ሰዎች በቀጥታ በወንዞች ላይ በመጠጥ ውሃ ጥገኛ ሲሆኑ፣ 25 በመቶ የዓለም የምግብ ምርት የሚቀርበውም ከወንዞች በሚገኝ ውሃ ነው። እንደዚሁም በዓመት ቢያንስ 12 ሚሊዮን ቶን ዓሳ የሚገኘው ከዚሁ ከወንዝ ነው ይላል የገጸ ድሩ መረጃ፡፡

ወንዞች በአካባቢ ጥበቃ፣ ለተፈጥሮ ሚዛን ማስጠበቂያ፣ መዝናኛ እንደዚሁም ለሰው ልጆች እድገት ያላቸው አበርክቶ ከፍ ያለ ነው፡፡ ይሁንና አዲስ አበባ ለዓመታት በጉያዋ ያቀፈቻቸው ወደ 600 ኪሎ ሜትር የሚሸፍኑት ወንዞች ግን ለዚህ አልታደሉም፡፡ በመዲናዋ የሚገኙት እነዚህ ወንዞች ፍሰታቸው ወቅታዊና ተለዋዋጭ ከመሆኑም በላይ ብዙውን ጊዜ ደረቅ ናቸው፡፡ ለዘመናት ለቀማኛ መደበቂያ፣ የመጥፎ ሽታ መገለጫ፣ የሞቱ እንሰሳት መጣያ ሆነው ቆይተዋል፡፡ በሌላም በኩል በርካታ የጥናት ውጤቶች እንደሚያመለክቱትም የመዲናዋ ወንዞች ከመኖሪያ መንደሮች በሚወጡ ውጋጆችና የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች በተረፈ ምርት በከፍተኛ ሁኔታ የተበከሉ ነበሩ፡፡

በኢትዮጵያ ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት ከተሞች 60 በመቶ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ደግሞ ከ50 በመቶ በላይ ድርሻ እንዳላት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህን ያህል ኢኮኖሚያዊ ድርሻ ያለው ከተማ ደግሞ በውስጡ ያሉ ሁሉንም ሀብቶች ማልማት ግድ ይለዋል፡፡ ከዚህም መነሻነት ለዓመታት ሕይወት አልባ ሆነው የቆዩት እነዚህ የመዲናዋ ወንዞች ‘አዲስ ገጽታ ለአዲስ’ በሚል መርህ የተጀመረው ወንዞቹን የማልማት ስራ ጋር ሲገናኙ አስከፊ ታሪካቸው እየተቀየረ ከአክሳሪነት ወደ የሀብት ምንጭነትና አትራነት እየተቀየሩ ይገኛል፡፡

ከእንጦጦ ተራሮች ተነስተው በከተማዋ በኩል አልፈው አቃቂ ወንዝ ድረስ በሚጓዙና በአጠቃላይ እስከ ከ45 ኪሎ ሜትር በላይ በሚሸፍኑ ትልልቅ ወንዞች ላይ የተጀመረው የወንዝ ዳርቻ ልማት የወንዞችን የዓመታት ጥያቄና የከተማዋ ነዋሪን ምላሽ የሰጡ ስለመሆናቸው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከንቲባ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው አቶ ጥላሁን ወርቁ ከዚህ ቀደም ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት ገልፀዋል፡፡

ከእንጦጦ ተራራ በጉለሌ በኩል አፍሪካ ህብረት እንዲሁም ከእንጦጦ በአፍንጮ በር በባንቢስ አድርጎ አቃቂ የውሃ ማጣሪያን በሚሸፍነው ፕሮጀክት በውስጡ 28 የሚደርሱ ድልድዮች፣ ሰው ሰራሽ ሐይቆች፣ አረንጓዴ ቦታዎች፣ የመዝናኛ ማዕከላት፣ የውኃ ትራንስፖርት እና የንግድ ማዕከላት ይገነቡበታል። ለእግር ጉዞና የመሮጫ ትራኮች፣ የብስክሌት መስመሮች፣ ኬብል ካር ትራንስፖርት (የገመድ ላይ መኪና)፣ መዝናኛ ግድቦችን ይዟል፡፡

ፕሮጀክቱ የከተማዋ ነዋሪዎች ደህንነት በማሻሻልና የከተማዋን እይታ ይበልጥ በመለወጥ ረገድ ብዙ ሚና ከመጫወቱ በተጨማሪ የተለያዩ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ መስህቦች እንዲሁም ለጎብኚዎች የእረፍት ጊዜ ማሳለፊያ ስፍራዎችን በማዘጋጀት የውጪ ሀገርና የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ወደ አዲስ አበባ መሳብ ያስችላል ተብሎለታል፡፡ ለከተማዋ ነዋሪ ተጨማሪ ቋሚ የስራ ዕድል መፍጠር፤ በወንዞች ዳርቻ እና ህዝብ በሚንቀሳቀስባቸው ቦታዎች የአገልግሎት ዘርፉን በማበረታታት ካፌዎች፣ ምግብ ቤቶች፣ የከተማ አስጎብኚዎችና የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ማመቻቸት፤ የተፋሰስ ወንዞች ዳርቻ እና ፕሮጀክቱ ዳርቻ ያሉና ወደፊት የሚገነቡ የሪልስቴት ፕሮጀክቶችም የዕቅዱ አካል ነው፡፡

እነዚህ ሁሉ ስራዎች ታዲያ ለመዲናዋ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ጉልበት እንደሚሰጡ መረዳት ይቻላል።

የአዲስ አበባ የወንዝ ዳርቻ ልማት የከተማዋን ገጽታ በመቀየር እና ወደ ዘመናዊ ከተሜነት በማሳደግ ረገድ ትልቅ ቦታ ያለው ፕሮጀክት ነው፡፡ በኢኮኖሚው እና በማህበራዊው ዘርፍ ያለው ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ልማቱ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅም የአዲስ አበባን ኢኮኖሚ እና የነዋሪዎቿን ኑሮ ደረጃ ከፍ እንደሚያደርግ ይጠበቃል።

በግንባታውና ከዚያ በኋላ በሚሰጡ አገልግሎቶች አማካኝነት ለብዙ ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል። የወንዝ ዳርቻዎች ወደ ማራኪ መዝናኛ እና የቱሪስት መዳረሻዎች በመቀየራቸው የከተማዋን የገቢ ምንጭ ያሰፋል የሚለውም የባለሙያዎች አስተያየት ነው። የምጣኔያዊ ሀብት ተንታኝ የሆኑት አቶ ኪሩቤል ሰለሞን በሰጡን ማብራሪያ ከተሞች በኢኮኖሚያዊ ዕድገት ውስጥ ጉልህ ድርሻ እንደሚኖራቸው አውስተው፣ በከተማዋ እየተከናወነ የሚገኘው የወንዝ ዳርቻ ልማት ይህን አቅም የበለጠ አሟጥጦ የመጠቀም ዕድል እንደሚፈጥር ይገልጻሉ፡፡

‘ዳይቪንግ ኢንቱ ሪቨርስ፡- ዘ ኮምፕሌት ጋይድ ቱ ሪቨር ሄልዝ ኤንድ ሬስቶሬሽን’ (Diving into Rivers: The Complete Guide to River Health and Restoration) የተሰኘው ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ በሰፈረው ማብራሪያ የወንዝ ዳርቻዎች ወደ ውብ የፓርክ፣ የእግረኛ መንገዶች እና መዝናኛ ስፍራዎች ሲለወጡ፣ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ቱሪስቶችን ይስባሉ። ከፓርኮች መግቢያ ክፍያ፣ ከኪራይ ንግዶች (ካፌዎች፣ ሱቆች) እና ከአገልግሎቶች የሚገኝ ገቢ ለከተማዋ እና ለግል ባለሀብቶች የገቢ ምንጭ ይሆናል። በመዝናኛ ስፍራዎችም ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች፣ መናፈሻዎች የሚፈጠሩ የአገልግሎት ዘርፍ የሥራ ዕድሎች ይፈጥራሉ።

በወንዝ ዳር የተሻሻለ አካባቢ፣ የንብረት (ቤትና ሕንፃ) ዋጋ እንዲጨምር ያደርጋል። ውብ እና ማራኪ የሆኑ ወንዝ ዳርቻዎች በከተማ ልማት ዘርፍ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን ለምሳሌ የሪል እስቴት፣ የንግድና የአገልግሎት መስጫ ግንባታዎችን ይስባሉ። በሌላም በኩል የንብረት ዋጋ እና የኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ያድጋል፣ በኪራይ እና በንግድ መልክ የሚሰበሰበው የታክስ ገቢ ይጨምራል፡፡ የውኃ አካላትን ጤንነት መጠበቅ ለወደፊቱ ለተለያዩ አገልግሎቶች ንጹህ የውኃ ምንጭ የመሆን ዕድላቸውን ይጨምራል። በእንጦጦ አካባቢ ብቻ እስካሁን 438 ሄክታር ቦታ ላይ የተፈጥሮ ጥበቃ ሰራ እየተሰራ መሆኑን እዚህ ጋር ማንሳት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

የ‘Water Resources and Economics’ መጽሐፍ ደራሲዎቹ ሮይ ብሩወር እና አሌግ ሸርመት በጉዳዩ ላይ ያቀረቡት መረጃን ዋቢ አድርገን ስንቀጥል ወንዞች እንክብካቤ ከተቸራቸው ምን ያህል ውለታ መላሽ ስለመሆናቸው እንረዳለን፡፡ የወንዝ መስመሮችን በማጽዳትና በማስተካከል እንዲሁም አረንጓዴ ቦታዎችን በመፍጠር የጎርፍ አደጋን ይቀንሳል፤ ይህም በየዓመቱ በንብረት ላይ የሚደርሰውን ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ይከላከላል። የወንዝ መስመሮችን በማጽዳትና በማስተካከል እንዲሁም አረንጓዴ ቦታዎችን በመፍጠር የጎርፍ አደጋን ይቀንሳል፤ ይህም በየዓመቱ በንብረት ላይ የሚደርሰውን ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ይከላከላል።

የቼንግጊቼዮን ወንዝ እንደሆነው ሁሉ የወንዝ ዳርቻ ልማት ስራው የአዲስ አበባን ዘላቂ ልማት በማረጋገጥ ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፤ ይህም የመጪውን ትውልድ ፍላጎት ማሟላት ያስችላል፤ ጤናማና በሚገባ የተጠበቁ የወንዝ ዳርቻዎች የከባቢ ሥርዓትን እና የውሃ ጥራትን እንደሚጠብቁም የአዲስ አበባ ከተማ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ምክትል ስራ አስኪያጅ አቶ አሰግደው ወ/ጊዮርጊስ አስረድተዋል፡፡

የከተማዋን ለጎርፍ ተጋላጭነት በመቀነስ የነዋሪዎችን ደህንነት ያረጋግጣል። ልማቱ የማኅበረሰብን የኑሮ ደህንነት የሚያሻሽሉ እና ከተሞችን ለፈተና አለመበገር የሚያጠናክሩ ደማቅ ሕዝባዊ ሥፍራዎችን በመፍጠር ለዘመናት የሚቆይ የማኅበራዊ ካፒታል ይፈጥራል።

በአጠቃላይ፣ የወንዞች ልማት የአዲስ አበባን የከተማ ገፅታ በማሳመር፣ ኢንቨስትመንትንና ቱሪዝምን በመሳብ፣ እንዲሁም በአካባቢ ጥበቃ እና በጤና ላይ የሚወጣን ወጪ በመቀነስ ትልቅ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አለው። የወንዝ ዳርቻ ልማት ለአዲስ አበባ ከተማ ከተሜነትን፣ ውበትን፣ ጽዳትን እና የኢኮኖሚ ጥንካሬን በማምጣት ተወዳዳሪ እና ለኑሮ ምቹ የሆነች ከተማ እንድትሆን ቁመና እንድትላበስ የሚያደርግ አስኳል ፕሮጀክት ነው ማለት ይቻላል።

## “በ2018 ዓ.ም ... ከገጽ 1 የዞረ

አቅም ያላት ሀገር ብትሆንም መድረስ ከሚገባት ቦታ መድረስ አልቻለችም፡፡ ግጭትና ድህነትም ሌላኛው መገለጫዋ ሆነው ቀጥለዋል፡፡ ለዚህም በየጊዜው እየተንከባለሉ የመጡ፣ በተለያዩ የፖለቲካ ሊሂቃን፣ በመንግስትና ህዝብ እንዲሁም በማህበረሰብ መካከል በተለያዩ ሀገራዊ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ የሚታዩ ልዩነቶችና አለመግባባቶች እንደምክንያት ይነሳሉ፡፡ እነዚህ ለግጭት ምክንያት በመሆን በሰውና ንብረት ላይ ጉዳት ከማድረስም ባለፈ የሀገርን ህልውና አደጋ ውስጥ እየከተቱ መምጣታቸውን ምሁራንና መንግስት በተደጋጋሚ ሲናገሩ መስማት አዲስ አይደለም፡፡

የማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪው ብርሃኑ ሌንጂሶ (ዶ/ር) "ብሔርተኝነት" በተሰፐው መጽሐፈቻው ላይ እንዳሰፈሩት፣ በኢትዮጵያ የፖለቲካና ማህበራዊ ቀውሶች ዋነኛ ምክንያት ዜጎች የተሰማሙብት የጋራ ሀገራዊ ማንነትና መገለጫዎች አለመኖር ነው። የወል ወይም የጋራ ማንነት መገንባት እንደሀገር አብሮ ወደፊት ለመሄድ እጁግ ወሳኝ እርምጃ ነው። ለዚህም ሀገራዊ ምክክር ዋነኛው መፍትሔ ነው።

ርሃኑ ሌንጂሶ (ዶ/ር) “ብሔር-ተኝነት” በተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ እንዳሰፈሩት፣ በኢትዮጵያ የፖለቲካና ማህበራዊ ቀውሶች ዋነኛ ምክንያት ዜጎች የተስማሙበት የጋራ ሀገራዊ ማንነትና መገለጫዎች አለመኖር ነው፡፡ የወል ወይም የጋራ ማንነት መገንባት እንደሀገር አብሮ ወደፊት ለመሄድ እጅግ ወሳኝ እርምጃ ነው፡፡ ለዚህም ሀገራዊ ምክክር ዋነኛው መፍትሔ ነው፡፡

ከሶስት ዓመት በፊትም በመንግስት ተነሳሽነት በኢትዮጵያ መሰረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ያሉ ልዩነቶችና አለመግባባቶች መነሻ ምክንያቶችን በመለየት፣ በተለዩ አጀንዳዎች ላይ ምክክር እንዲካሄድ እንዲሁም የተገኙ ምክረ ሀሳቦችን እንዲተገበሩ በማድረግ ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር ሂደቱን የሚያስተባብር የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን እንዲቋቋም ተደርጓል። ኮሚሽኑ ከተቋቋመ በኋላ ስራውን በሶስት ዓመታት ውስጥ እንዲያጠናቀቅ ቀነ ገደብ ተቀምጦለት የነበረ ቢሆንም ከስራው አዲስነት፣ ሂደቱን አካታችና አሳታፊ ማድረግ ስለሚገባና በአንዳንድ አካባቢዎች ከነበረው የሰላምና ደህንነት ችግር አኳያ በተያዘው ጊዜ ማጠናቀቅ አልተቻለም፡፡ በዚህም የተነሳ ቀሪ ስራዎችን እንዲያጠናቅቅ የኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የስራ ዘመን የካቲት 2017 ዓ.ም ላይ ለተጨማሪ አንድ ዓመት ማራዘሙ ይታወሳል፡፡

### የኮሚሽኑ ቀሪ ስራዎች

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ሙሉጌታ አጎ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት ሀገራዊ ምክክሩን ለማካሄድ የቅድመ-ዝግጅት፣ ዝግጅትና



ፎቶ- ከፋይል

ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬት ሁሉም ባለድርሻ አካል የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅበታል

> “የወል ወይም የጋራ ማንነት መገንባት እንደሀገር አብሮ ወደፊት ለመሄድ እጁግ ወሳኝ እርምጃ ነው። ለዚህም ሀገራዊ ምክክር ዋነኛው መፍትሔ ነው።”

ሂደት ምዕራፍ ስራዎች ረዘም ያለ ጊዜ ወስደዋል፡፡ ምክንያቱም የስራዎቹ በትክክል መከናወንና አለመከናወን በምክክሩ ሂደትና ውጤታማነቱ ላይ የራሱ የሆነ አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖ አላቸው፡፡ በአሁኑ ወቅትም በምክክሩ የሚሳተፉ ባለድርሻ እና ተባባሪ አካላትን በመለየትና ተሳታፊዎችን በመምረጥ የአጀንዳ ሀሳቦችን የማሰባሰብ ስራ ከትግራይ በስተቀር በሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

በ2018 ዓ.ም የሀገራዊ ምክክሩ ቀሪ ስራዎች ለማጠናቀቅ በዕቅድ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ምክክሩ አሳታፊና አካታች እንዲሆን ከሀገር ውስጥ ባለፈ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በማሳተፍ አጀንዳ የማሰባሰብ፣ የትግራይ ክልልን በምክክሩ ሂደት የማሳተፍ፣ በተለያየ ምክንያት ያልተሳተፉ ሀይሎች (የፖለቲካ ፓርቲዎችና የታጠቁ ሀይሎች) በምክክሩ ሂደት ማሳተፍ፣ አጀንዳ መቅረፅ፣ ሀገራዊ ጉባኤ ማከናወንና በምክክሩ የሚገኙ ምክረ ሀሳቦችን ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ የሚሉ ዋና ዋና ቁልፍ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

በቅርቡም ኮሚሽኑ በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን (ዳያስፖራዎች) የአጀንዳ ሀሳብ ማሰባሰብና ተወካዮችን የመምረጥ ተግባር አከናውኗል፡፡

ኮሚሽነር ሙሉጌታም ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን በደቡብ አፍሪካ፣ በሰሜን አሜሪካ እና በካናዳ በተካሄዱ የምክክር መድረኮች ላይ በማስተባበርና በመምራት ተሳትፈዋል፡፡ እሳቸው እንደገለፁት፣ በእነዚህ አገራት በተካሄዱ መድረኮች ከዳያስፖራው ማህበረሰብ አጀንዳ የማሰባሰብ ስራው በስኬት ተከናውኗል። ተሳታፊዎቹ በኢትዮጵያ ለሰላም እጦት ምክንያት ናቸው ያሏቸውን ችግሮች በአጀንዳ ሀሳብነት እንዲያዙ አንስተዋል፡፡ በተጨማሪም በተባበሩት አረብ ኤምሬትስ፣ በእንግሊዝ ለንደን እና በስዊድን ስቶክሆልም ከሚኖሩ ዳያስፖራዎች ጋር በመገናኘት የአጀንዳ ሀሳብ የማሰባሰብና በሀገራዊ ምክክር ጉባኤው ላይ የሚሳተፉ ተወካዮች መረጣ ተከናውኗል፡፡

ሌላውና የዓመቱ ቁልፍ ስራ በትግራይ ክልል የአጀንዳ ሀሳብ ማሰባሰብ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ሰብሳቢ መስፍን አርዓያ (ፕሮፌሰር) በአዲሱ ዓመት መግቢያ ለመገናኛ ብዙሃን በሰጡት ማብራሪያ፣ ኮሚሽኑ በክልሉ የአጀንዳ ሀሳብ ማሰባሰብ ስራዎችን ለመጀመር የተለያዩ ጥረቶች ሲያካሄዱ መቆየቱን ተናግረዋል፡፡ የምክክር ሂደቱን ለመጀመር ኮሚሽኑ ከጊዜያዊ አስተዳደሩ ኃላፊዎች፣ የጊዜያዊ አስተዳደሩ ካቢኒ፣ የተፎካካሪ ፓርቲዎች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የሲቪክ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ኢኮኖሚ

## ብቃት ... ከገጽ 1 የዞረ

ለራስ፣ ለቤተሰብ፣ ለማህበረሰብ፣ ለአገር እና ከዚያም ለሚሻገር በጎ ውጤት የሚሆን ዕምቅ አቅም ይገኛል፡፡ ዕውቀትና ክህሎት ይያዛል፡፡ ለዚህም ነው “ወጣት የነብር ጣት” የሚል አገርኛ አባባል የተነገረው፡፡

በዚህ ፅሑፍም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባለፉት አምስት ዓመታት ሲተገበር ስለቆየው “የብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር” ዳስሰናል፡፡ በተለይ ነገ (ማለትም ጥቅምት 30 ቀን 2018 ዓ.ም.) በይፋ የሚጠናቀቀውን የመርሃ ግብሩን ሂደትና አፈፃፀም እንፈትሻለን፡፡ የሥራ ላይ ልምምዱ ዋነኛ ተሳታፊ የሆኑ ወጣቶችን፣ ዕድሉን የፈጠሩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ሚና እንዳስሳለን፡፡

ወጣት ዮሀንስ ጌትነት፤ ነዋሪነቱ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ ነው። ትምህርቱን እስከ 12ኛ ክፍል ተከታትሏል። በ2016 የትምህርት ዘመን ሀገር አቀፍ ፈተና ወስዶ ውጤት ስላልመጣለት በቤት ውስጥ ለመቀመጥ ተገድዶ ነበር፡፡ አሁን ላይ ግን በእንጨትና ብረታ ብረት ሥራ ብቁ ሙያተኛ ሆኗል። ለዚህም የብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ተሳታፊ መሆኑ ጠቅሞታል፡፡

ለሦስት ወራት ያለትምህርት እና ያለ ሥራ የቆየው ወጣት ዮሀንስ፣ በእነዚህ ጊዜያት ድብርት ውስጥ እስከመግባት ደርሶ እንደነበር በማስታወስ፣ ያንን ጊዜ እና አሁን ያለበትን ሁኔታ እንዲህ ሲል በንፅፅር ያስረዳል፤ “በሦስቱ ወራት ውስጥ ሥራ ለመፈለግ ተንቀሳቅሼ ነበር። አሰሪዎች የሚጠይቁት አንድ ነገር ‘ምን ሙያ አለህ?’ የሚል ነው፡፡ ሥራ ለማግኘት ጉልበት እና ፍላጎት ብቻውን ትርጉም እንደሌለው ተገነዘብኩ፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለሁ ስለ ሥራ ላይ ልምምድ መረጃ ጎረቤቶቼ ሰጡኝ፡፡ በመረጃው መሰረት የሚጠየቁትን መስፈርቶች በማሟላት ተመዘገብኩ፡፡ በእንጨት ሥራ በተሰማራ ድርጅት ውስጥ የሥራ ላይ ልምምድ ማድረግ ከጀመርኩ በኋላ፣ ደስተኛ ሆኛለሁ፡፡ የሥራ ፍቅሬ ጨምሯል፡፡ ገቢ ማግኘት ችያለሁ፡፡”

ወጣት አብርሃም ተስፋዬ እንደ ወጣት ዮሀንስ ሁሉ፤ ከሦስት ዓመት በላይ ያለ ትምህርት እና ሥራ ያሳለፈው ጊዜ ያስቆጨዋል፡፡ እነዚህን ግዜያትም፤ “ትምህርትም ሥራም ስለሌለኝ በጣም የሚያስጨንቅ ጊዜ ነበር ሳሳልፍ የነበርኩት፡፡ በዚህም ሙሉ ትኩረቴን በኦንላይን የሚተላለፉ የቨርቹዋል ጌሞች ላይ አደረግሁ፡፡ በሂደት እኔን መሰል ወጣቶች እንገናኝ ጀመር፡፡ በአቻ ግፊት ተፅዕኖ ወደ ሱስ የምገባበት ሁኔታም ተፈጥሮ ነበር፡፡ በአጠቃላይ በጣም መጥፎ መስመር ውስጥ እየገባሁ ነበር” በማለት ያስታውሳል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

ብቃት የወጣቶች የስራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ሰልጣኞች ብቁ በማድረግ ረገድ ፋይዳው የጎላ ነው

**በአምስት ዓመቱ ብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድን ጥቅል ውጤት በጥናት ለማረጋገጥና በገለልተኛ አካል ለማስጠናት ዕቅድ ተይዟል**

የየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 ነዋሪው ወጣት አብርሃም፣ አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ በብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር አማካኝነት፣ በግርማ፣ ሕይወትና ጓደኞቻቸው የእንጨት እና ብረታ ብረት ሥራ ድርጅት ያገኘው ሙያዊ ክህሎት፣ ልምድና ውጤት ትርጉሙ ከፍተኛ መሆኑን ያነሳል፡፡ ይህንንም፤ “ለሦስት ዓመታት ያክል ያሳለፍኳቸውን አስቸጋሪ ልምዶች፤ ለ6 ወራት የቆየሁበት የሥራ ላይ ልምምድ አክሞልኛል፡፡ በ6 ወራት ውስጥ ትኩረቴ ሁሉ ሥራ ብቻ ሆኗል። አዳዲስ ሙያዎችን ለመልመድ ያለኝ ፍላጎትና ጉጉት ጨምሯል። ከድርጅቱ ባለቤት እና ከሥራ ባልደረቦቼ የማገኛቸው ልምዶች እኔን በጥሩ መልኩ ገንብተውኛል፡፡ የሥራ ግንዛቤዬ ተለውጧል፡፡ በሥራዬ ደስተኛ ሆኛለሁ፡፡ ገቢ ማግኘት፣ ካገኘሁትም ላይ መቆጠብ ጀምሬያለሁ፡፡ ከሰፈሬ አልፌ ወደ ሌሎች ከተሞች በመሄድ በሙያዬ ሠርቼ ከፍተኛ ገቢ ማግኘት ጀምሬያለሁ፡፡ ነገ ከነገ ወዲያ የተሻለ ሕይወት እንደምኖር አምኛለሁ፡፡ ቤተሰቤ በእኔ መለወጥ ደስተኛ ሆኗል፡፡” ሲል አብራርቷል፡፡

አቶ ግርማ አለሸኝ ይባላሉ፡፡ የግርማ፣ ሕይወትና ጓደኞቻቸው የእንጨት እና ብረታ ብረት ሥራ ድርጅት ምክትል ሥራ አስኪያጅ ናቸው፡፡ ድርጅታቸው በ2013 ዓ.ም. በመቋቋም እየሠራ ይገኛል። ምርት ከማምረት ጎን ለጎን ለወጣቶች የሥራ ዕድልን ፈጥሯል፡፡ የሥራ ላይ ልምምድ የሚያደርጉ ወጣቶችንም በመቀበል መሰረታዊ ሙያ እያስጨበጠ ይገኛል፡፡ ወጣት ዮሀንስ ጌትነት እና አብርሃም ተስፋዬን ጨምሮ ስምንት ወጣቶችን በመቀበል በድርጅቱ ውስጥ የሥራ ላይ ልምምድ እያደረጉ ይገኛሉ። ከዚህ በፊት በነበረው መርሃ ግብር 14 ወጣቶችን ተቀብለው የሥራ ላይ ስልጠና መስጠታቸውን አስታውሰዋል፡፡

“የሥራ ላይ ተለማማጆች ወደ ድርጅታችን የሚመጡት ሙያውን ለማወቅና በሙያው ሠርተው ለመለወጥ ፍላጎት ካላቸው ብቻ ነው፡፡ አሁን ላይ ስልጠናቸውን እያጠናቀቁ ያሉት ስምንቱ ወጣቶች ይህንን ሙሉ በሙሉ ያሟሉ ናቸው፡፡ ይህም ባሳለፍናቸው ስድስት ወራት ማረጋገጥ ተችሏል” የሚሉት አቶ ግርማ፣ ከወጣቶቹ ጋር ያሳለፏቸውን ስድስት ወራት እንደሚከተለው በአጭሩ ይተርካሉ፤ “ወጣቶቹን እንዳገኘኋቸው፤ ስለ ፍላጎታቸው ጠይቄ ተረዳሁ፡፡ እርስ በእርስ እንዲተዋወቁ ከእኔም ጋር እንዲቀራረቡ በነፃነት አወያየኋቸው፡፡ ከዚያም ድርጅቱን በአካል አዩ፤ ወደ ሥራ ላይ ልምምድ ገቡ፡፡ የሥራ ላይ ልምምዱ እንዴት መቁረጥ፣ ማሸግ፣ መገጣጠም ... እንደሚችሉ መሰረታዊ ሙያውን በወረቀት ላይ አሳየኋቸው፡፡ ያሳየኋቸውን ስለመረዳታቸው የቤት ሥራ በመስጠትና በማረም ሙያው ውስጥ ዘልቀው እንዲገቡ አደረግሁ፡፡ እንዲህ እንዲህ እያሉ ከማሽኖች፣ ከሙያው፣ ከሥራው ጋር በሚገባ ተዋወቁ፡፡ አሁን ላይ እኔ ባልኖር እንኳን፤ ሥራዎችን ጥንቅቅ አድርገው የሚሠሩ ብቁ ሙያተኞች ሆነዋል፡፡”

ምክትል ሥራ አስኪያጁ አክለው እንዳስረዱት፤ የሥራ ላይ ልምምድ ሲያደርጉ የቆዩት ወጣቶች የሥራ ፍላጎታቸው ጨምሯል፡፡ ሥነ ምግባራቸው ተሻሽሏል፡፡ የሥራ ሰዓትን ያከብራሉ፤ የተሰጣቸውን ሥራ በአግባቡ ይፈፅማሉ፡፡ ቢቀሩ እንኳን አስፈቅደው ነው፡፡ በሳይት ላይ በመውጣት ከነባር ሠራተኞች ያልተናነሰ ሥራ እስከ መሥራት ደርሰዋል፡፡ በሁለት ወር ውስጥ ከ30 ቤት በላይ የኪችን ካቢኔት ገጥመዋል፡፡ ይህ አፈፃፀማቸው ልምድ አለን ከሚሉት ባለሙያዎች በእጥፍ ብልጫ አለው። በዚህ ሥራቸው እያንዳንዳቸው እስከ 30 ሺህ ብር ድረስ ገቢ አግኝተዋል፡፡ በሥራ ያገኙትን ገቢ በመቆጠብ ማሽን እስከመግዛት የደረሱም አሉ፡፡

ዘናጭ ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ማምረቻ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፤ እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እየተሰጠ ባለው የብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ላይ እየተሳተፉ ካሉ የግል ድርጅቶች አንዱ ነው፡፡ በ2009 የተቋቋመው ይህ ድርጅት የስፖርት ትጥቆችን ያመርታል፤ ለነጋዴዎች ያከፋፍላል፡፡ ከ280 በላይ ቋሚ ሠራተኞች ያሉት ድርጅቱ፤ በመጨረሻው ዙር የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር እንዲሳተፉ ከተመለመሉ ወጣቶች መካከል ከየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ አራት 100፣ ከወረዳ ሦስት ደግሞ 15 በድምሩ 115 ወጣቶችን እንደተቀበለ የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ወይዘሪት ትግስት ጥሩነህ ተናግረዋል፡፡

ወደ ዘናጭ ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ማምረቻ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለሥራ ላይ ልምምድ ከገቡት ወጣቶች መካከል፤ የስድስት ወር ስልጠናቸውን አብዛኞቹ ማጠናቀቃቸውን የገለፁት ሥራ አስኪያጇ፤ የተወሰኑት በተለያየ ምክንያት ማቋረጣቸውን አልሸሸጉም፡፡ በሥራ ላይ ልምምዱ በተገቢው ሁኔታ የተሳተፉ እና ያጠናቀቁ ወጣቶች ያገኟቸውን ጥቅሞች በተመለከተም፤ “የሥራ ላይ ልምምዱን የመጀመሪያ አንድ ወር እንዳጠናቀቁ፤ ለአምስት ወራት ያክል ድርጅቱ በየወሩ 1 ሺህ 500 እንዲሁም ተጨማሪ በየሳምንቱ 300 ብር እየከፈላቸው አቆይቷቸዋል። እነዚህ ወጣቶች ጥሩ ስነ ምግባር ያላቸው፣ የሥራ ፍቅርና ተነሳሽነታቸው ጥሩ የሆነ፣ ከነባር የድርጅቱ ሠራተኞች እኩል ምርታማ መሆን የቻሉ ናቸው።

ወደ ገጽ 18 ዞሯል

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# የወንጀል ሕግ ምንነት፣ አላማው እና የወንጀል መከላከያ መንገዶች

## (ክፍል ሁለት)

ይነበብ ታምሩ (ዐቃቤ ህግ)

ባለፈው ዕትማችን በዋናው ርዕስ ስር ስለወንጀል ምንነት፣ የወንጀል ህግ ዓላማ በሚሉትና መሰል ንዑሳን ርዕሶች ላይ መረጃ ማጋራታችን ይታወሳል፡፡ የፅሁፉን ቀጣይ ክፍል እንደሚከተለው አናቀርባለን።



### ሀ) የህዝቡን ሰላምና ደህንነት እንዲሁም ንብረት መጠበቅ

የወንጀል ሕግ ዋነኛ አላማው እና መሰረቱ በአንቀጽ 1 ላይ እንደተቀመጠው የሰውን ሰላም እና ደህንነት ብሎም ያፈራውን ንብረት የሕግ ከለላ በመስጠት ጉዳት እንዳይደርስበት መጠበቅ ነው፡፡ ይህንን ደህንነቱን ማስጠበቅ የሚቻለውም ትክክለኛ እና ዘመኑን የዋጀ የወንጀል ሕግ ሲኖር ነው፡፡ በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 26 ላይ ማንም ሰው የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት እንዳለው ተደንግጎ ይገኛል። ይህም ማለት ማንም ሰው በሰው ህይወት ጣልቃ በመግባት በሕገ መንግስቱ የተሰጠውን መብት በመጋፋት ግላዊነት መብቱን መጋፋት ክልክል እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 ላይ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆን እንደሚችሉ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በዚህ መሰረት ማንኛውም ሰው በህጋዊ መንገድ ያፈራውን ንብረቱን ወይም ከሕግ አግባብ ውጭ የሌላ ሰውን መብት ተላልፎ መገኘት ወንጀል ነው፡፡

በዚህ መሰረት መንግስት ሦስት ግዴታዎች አሉበት፡፡ የመጀመሪያው የመንግስት ግዴታ(obligation to respect) የሀገሪቱ ዜጎች ሕግን ተከትለው ስራቸውን እስከሰሩ ድረስ ከሕግ አግባብ ውጭ በሆነ ነገር ዜጎችን ማንገላታት እና የመብት ጥሰት ከማድረግ መቆጠብ አለበት፡፡ ነገር ግን ከሰው "ስህተት ከብረት ዝገት" እንደሚባለው የሀገራችን ብሂል ሰው ሁልጊዜ ፍጹም ሆነው የሀገሪቱን ሕግ ተከትለው ስራቸውን ላይሰሩ ይችላሉ፡፡ በእነዚህ ሕግ ተላልፈው በሚገኙ አካላት ላይ መንግሰት የሚወስደው እርምጃ ሕገ መንግሰቱን መሰረት ያደረገ እና ከጥፋታቸው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ እና እነሱን ሊያስተምር የሚችል ቅጣት መሆን አለበት፡፡

ሌላውና ሁለተኛው(obligation to protect) ዜጎች በተለያየ ሦስተኛ አካላት ጉዳት እንዳይደርስባቸው መብታቸው ተጠብቆ ስራቸውን የሚሰሩበት እና ሰላማዊ ህይወት እንዲኖራቸው የሚያደርግበት ግዴታ ሲሆን፤ ለዚህም መንግስት እንደ ፖሊስ የመሳሰሉትን የህግ አካላት በማሰማራት ሰዎች በሰላም ወጥተው የሚገቡበት እና ሰዎች እርስ በእርስ ተከባብረው እንዲኖሩ የሚያስችልበት ሁኔታ ነው፡፡

የሦስተኛው የመንግስት ግዴታ (The obligation to fulfill) መንግስት ዘመኑን የዋጀ እና የዜጎችን ሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ሊያስጠብቅ የሚችል ህግ በማውጣት እንዲሁም ዜጎች መብታቸውን እንዲያውቁ መንግስት ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ ከዚህ በተረፈ መንግሰት ዜጎች ትክክለኛ ፍትህ እንዲያገኙ የፍትህ ስርዓቱን ለዜጎች በእኩልነት እና በተቀላጠፈ ሁኔታ አገልግሎቱ ተደራሽ እንዲሁን ይሰራል። ጠቅለል ስናደርገው የወንጀል ሕግ ዋነኛ አላማው የህብረተሰቡን ሰላም እና ደህንነት በማረጋገጥ ዜጎች ከአንድ ቦታ ወደ አንድ ቦታ በመንቀሳቀስ በሰላም ወጥተው የሚገቡበትን ሁኔታ በመፍጠር እና የህግ የበላይነት የሰፈነበት ማድረግ ነው፡፡

### ለ) ወንጀል እንዳይፈጸም መከላከል

የወንጀል ሕግ በዋነኘነት በአንቀጽ አንድ ላይ በግልጽ እንደተጠቀሰው ወንጀል እንዳይፈጸም መከላከል ሲሆን፤ ይህንን የሚያደርገው አስቀድሞ ስለወንጀሎች እና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት እንዲሁም ለሕብረተሰቡ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት አስቀድሞ ወንጀል ከመፈጸሙ በፊት ይከላከላል። ይህ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሚሰሩ ስራዎችን መንግስት አስቀድሞ መስራቱ በህዝብ እና ሀገር ላይ ሊደርስ የሚችልን ጉዳት ለመከላከል ያስችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግን ሰዎች የቅድሚያ ማስጠንቀቂያውን በመተላለፍ ወንጀል ፈፅመው በሚገኙ አካላትን ሌላ ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈጽሙ እና ጉዳት እንዳያደርሱ ተገቢ የሆነ እና ህገ መንግስቱን እና የወንጀል ህጉን መሰረት አድርጎ ተገቢ የሆነ ቅጣት ይጣልበታል። ይህ ቅጣት ሲጣል ግን ዝም ብሎ በዘፈቀደ ሳይሆን በመጀመሪያ አጥፊዎቹ ራሳቸውን ከጥፋታቸው ተምረው ሌላ ጥፋት ወንጀል እንዳይፈጽሙ ማድረግ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ሌላው የህብረተሰብ ክፍል ከሌሎች የወንጀል ጥፋተኞች ቅጣት በመማር ተጨማሪ ወንጀል ከመስራት እንዲቆጠብ ማድረግ ዋነኛ አላማው ነው፡፡

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሚሰሩ ስራዎችን መንግስት አስቀድሞ መስራቱ በህዝብ እና ሀገር ላይ ሊደርስ የሚችልን ጉዳት ለመከላከል ያስችላል

አንባቢዎቻችን ክፍል ሦስትን በሚቀጥለው ሳምንት ይዘን እንቀርባለን።

ኢኮኖሚ

# ብቁ የቱሪዝም ባለሙያዎችን ለማፍራት ምን እየተሰራ ነው?

**“በቱሪዝም ዘርፍ በሙያው የሰለጠነ የሰው ኃይል ከማፍራት አንፃር በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚታየው ዋና ጉድለት ‘ነፍስ እና ስጋ ያለው ስልጠና’ የመስጠት ክፍተት ነው”**

**በጅማ ዩኒቨርሲቲ የቱሪዝም እና የሆቴል ማኔጅመንት መምህር ደመቀ ክብሩ**

**በደረጀ ታደሰ**

ቱሪዝም ለኢኮኖሚ እድገት፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራ እና ለባህል ልውውጥ መሰረት ነው። የአንድ አገር የቱሪዝም ዘርፍ ስኬት በዋናነት የሚመጣው ደግሞ በዘርፉ ባለው የሰው ሀብት ብቃት ነው። ስለዚህ በቱሪዝም ልማት ውስጥ ሙያዊ አቅም እና ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ለማፍራት እና በኢንዱስትሪው ውስጥ ያላቸውን ቁልፍ አስተዋፅኦ እንዲወጡ ማድረግ ይገባል። ለዚህ ደግሞ አገራት የሚጠበቅባቸውን ሥራ መፈፀም ይኖርባቸዋል፡፡

ለዓለም ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋል፤ ቱሪዝም፡፡ በጎርጎሮሳዊያን ዘመን ቀመር 2024 መጨረሻ ላይ የወጣው የWorld Travel & Tourism Council (WTTC) ሪፖርት እንደሚያመላክተው፤ ከዓለም አቀፉ የአገር ውስጥ ምርት 10 ከመቶ የሚሸፍነው ከቱሪዝም ዘርፍ የሚገኘው ነው፡፡ በተጨማሪም በዓለም ዙሪያ ከሚገኙ አስር ሥራዎች አንዱን የሚሸፍነው ይኸው ዘርፍ ነው፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ አገራት ደግሞ ዘርፉ ብዙ ትርጉም ያለው ነው፡፡ ኢትዮጵያ ለቱሪዝም ዘርፍ ዕድገት የሚያግዙ በርካታ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊ፣ ባህላዊና ሰው ሠራሽ ፀጋዎች አሏት፡፡ እነዚህን በአግባቡ መጠቀም ከቻለች ቱሪዝም የኢኮኖሚ ብዝሃነት እና የውጭ ምንዛሪ ገቢ እድልን የመፍጠር አቅሙ ከፍተኛ ነው፡፡ ይህንን አቅም ለመጠቀም ደግሞ፤ የአገልግሎት ጥራትን የሚያረጋግጡ፣ መዳረሻዎችን በብቃት የሚያስተዳድሩ እና የጎብኝዎችን እርካታ የሚያጎለብቱ ብቁና በቂ ባለሙያዎች ማፍራት ይገባል፡፡

ኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፉን አንዱ የኢኮኖሚ ምሰሶ አድርጋ ለመጠቀም እየሠራች ያለችው ሥራ ውጤታማ እንዲሆን በሰው ሃብት ልማት ላይ በትኩረት መሠራት እንደሚገባው ያነጋገርናቸው የዘርፉ ምሁራን ያረጋግጣሉ፡፡ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የቱሪዝም እና የሆቴል ማኔጅመንት ትምህርት ክፍል ኃላፊ እና መምህር የሆኑት ደመቀ ክብሩ በሰጡት ሃሳብ እንደጠቆሙት፤ “ማንኛውም ነገር ትርጉም የሚኖረውም የሚያጣውም በሰው ነው፡፡ ቱሪዝም ለሰው፣ በሰው የሚከወን ተግባር ነው። የቱሪዝም ውጤታማነት የሚወሰነው በሙያው በሰለጠነና ብቃት ባለው በሰው ኃይል ነው። ምክንያቱም በሙያው የሰለጠኑ ሰዎች ዘርፉን ይፈጥሩታል፣ ያስተዳድሩታል፣ ያሳድጉታል። ሥራውን በዕቅድ ይመሩታል።

ይህንን ሃሳብ የሚደግፍ ምሁራዊ ዕይታቸውን ያካፈሉት ከፍተኛ የቱሪዝም ተመራማሪ እና መምህር አያሌው ሲሳይ(ዶ/ር) በበኩላቸው ጉዳዩን ድግስ ካዘጋጀ እና ወደ ድግሱ ከተጠሩ እንግዶች ጋር በማያያዝ በተምሳሌት እንዲህ ገልጸውታል፤ “እንግዳ ጠርተህ በደንብ የሚያስተናግድ ሰው ከሌለ ውጤቱ ጉዳት ነው፡፡ እንግዳ የጠራ አካል በደንብ መዘጋጀት አለበት። ምንም ያክል የተሟላ ድግስ ቢያሰናዳም ያንን በአግባቡ የሚያስተናግድ ሰው ከሌለው በእንግዶቹ የሚደርሰው አሉታዊ ስሜትና እሱን ተከትሎ የሚከሰተው ጉዳት ከፍተኛ ነው። ስለዚህ እንግዶችን ወይም ጎብኝዎችን የሚጠራ የቱሪዝም ሥፍራ የተሟላ መስተንግዶ ለመስጠት ሁሌም የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡ ለዚህ ደግሞ በሙያና በዕውቀት የደረጁ ሙያተኞች ያስፈልጋሉ። እነዚህ ሙያተኞች በስነምግባራቸው እና በአለባበሳቸው የጎብኚዎችን ልብና ቀልብ የሚስቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡”

ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች የአገራት የቱሪዝም ዘርፍ የጀርባ አጥንት ናቸው። ከፖሊሲ ቀረጻ እስከ አገልግሎት አሰጣጥ ድረስ በሁሉም ደረጃዎች አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሙያተኞች የአንድን አገር የቱሪዝም መስህብ፣ መልካም ስም እና ዘላቂነት ለማረጋገጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በቱሪዝም ዘርፍ ከሚያስፈልጉ የሙያ መስኮች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሆቴል አስተዳደር፣ የማርኬቲንግ፣ የታሪክ፣ የሰው ሀብት አስተዳደር፣ የማህበረሰብ ሣይንስ መሆናቸውን የጠቆሙት በጅማ ዩኒቨርሲቲ የቱሪዝም እና የሆቴል ማኔጅመንት መምህሩ ደመቀ ናቸው፡፡

እንደሳቸው ገለጻ፤ የቱሪዝም እና የሆቴል አገልግሎት የማይነጣጠሉ ናቸው። ስለዚህ በሆቴል አስተዳደር እና በቱሪዝም አስተዳደር የሰለጠነ ሙያተኛ ያስፈልጋል። ያሉንን የቱሪዝም ሃብቶች ለጎብኚዎች ማድረስ የምንችለው ስናስተዋውቀው ነው። ለዚህ ደግሞ በማርኬቲንግ የሰለጠነ ሙያተኛ ለኢንዱስትሪው ወሳኝ ነው። ከሰው ኃይል ቅጥር እስከ ስንብት ያለውን ሂደት የሚመራና የሚያስተዳድር የቱሪዝም አስተዳደር ሙያተኛም ያስፈልጋል። በተመሳሳይ፤ የቱሪዝም ሃብቶች በአብዛኛው ከታሪክ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስትያን፣ የአክሱም ሐውልት፣ የጀጎል ግንብ... ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር ጠንካራ ግንኙነት አላቸው፡፡ የገዳ ሥርዓት፣ ጥምቀት፣ መስቀል፣ ጨንባላላ ... ውስጥም ታሪክ አለ፡፡ እነዚህን የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶችን ጨምሮ የኢትዮጵያን የቱሪዝም መዳረሻዎች በአግባቡ ለማስጎብኘት በታሪክ ዕውቀት ያለው ሙያተኛ ማፍራት ይገባል። ባህልን ታሳቢ ያደረገ በማህበረሰብ ሣይንስ (Anthropology) የሰለጠነ፣ ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት ለመስጠት በኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ የሰለጠነ ሙያተኛ ያስፈልጋል። በአስጎብኚነት(Tour and Traveling)፣ በምግብ ዝግጅት፣ በመጠጥ፣ በእንግዳ አቀባባል፣ በቤት አያያዝ፣ በንፅህና አጠባበቅ፣ በቋንቋ የሰለጠኑ ሙያተኞችን ማፍራት ይገባል፡፡

“የቱሪዝም ዘርፍ የማይነካው ሴክተር የለም፡፡ ከከፍተኛው የመንግስት መዋቅር ጀምሮ፣ አስጎብኚ ድርጅቶች፣ ሆቴልና ሪዞርቶች፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች፣ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት የመሳሰሉት ከቱሪዝሙ ዘርፍ ጋር በቀጥታ ግንኙነት አላቸው። በእነዚህ ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ ሙያተኞች በዕውቀት፣ በክህሎት እና በስነ ምግባር የበቁ መሆን አለባቸው” የሚሉት አያሌው ሲሳይ(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ “በቱሪዝም ዘርፍ ላይ ያሉ ሙያተኞች ስለሚጎበኘው አካባቢ በሚገባ የሚገልጡ፣ መንገድን በአግባቡ የሚያመላክቱ መሆን እንዳለባቸው ጠቁመዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በስፋት እየለሙ ያሉት የቱሪዝም መዳረሻዎች ውጤታማ እንዲሆኑ በዘርፉ ብቁና በቂ ሙያተኞች እንደሚያስፈልጉም አንስተዋል። በአሁኑ ወቅት እንደአገር እየተሠራ ያለው ይህንን ታሳቢ ያደረገ መሆኑንም ገልጸው፤ የቱሪዝም መዳረሻ ልማት እና የሰው ሀብት ልማት ተያይዘው የሚሄዱ ተግባራት ናቸው ብለዋል፡፡

በቱሪዝም ዘርፍ በዕውቀትና ክህሎት የዳበሩ ሙያተኞችን በማፍራት ረገድ እንደአገር ከዓመት ዓመት መሻሻሎች እየታዩ ስለመሆናቸው ያነጋገርናቸው ምሁራን ይመሰክራሉ፡፡ መንግስት ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ፤ ለቱሪዝሙ ዘርፍ ራሱን የቻለ የትምህርትና ስልጠና መርሃግብር(ካሪኩለም) ተዘጋጅቶለታል። አሁን ላይ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት(ዩኒቨርሲቲ እና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛዎች) በተለያዩ የሙያ ዘርፎች

ወደ ገጽ 18 ዞሯል









ፎቶ ከፋይል

የቱሪዝም ዘርፉን ከፍ ካደረጉ መዳረሻ ስፍራዎች በከፊል

# የመዲናዋ ኪነ ጥበባዊ መረጃዎች

በአብርሃም ገብሬ

ባሳለፍነው ሳምንት በአዲስ አበባ የተለያዩ የኪነ ጥበብ ስራዎች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መሰናዶዎች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የመጻሕፍት ምረቃ፣ የሥዕል አውደ ርዕይ፣ ጥበባዊ ውይይቶችና የቴአትር መርሃ ግብሮች ይገኙበታል። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## መጻሕፍት

የቀድሞ ሙዚቀኛና የአሁኗ ዘማሪት ዘሪቱ ከበደ ከወር በፊት 'ከልጅነት እስከ ልጅነት' በሚል ርዕስ የራሷን ግለ ታሪክ መጽሐፍ እንዳሳተመች ይታወቃል። ይኸን መጽሐፍ መነሻ በማድረግ ዛሬ ከ8፡00 ሰዓት ጀምሮ በዛጎል የመጻሕፍት ባንክ አሰናጅነት ውይይት ይደረጋል። የውይይቱ አዘጋጅና አቅራቢ ደራሲ እንዳለጌታ ከበደ ሲሆን የመጽሐፉ ደራሲ ዘሪቱ ከበደ ተጋባዥ እንግዳ በመሆን በመድረኩ ትገኛለች፡፡ የውይይቱ ቦታው የካቶሊክ ኪዳነ ምሕረት ትምህርት ቤት ፊት ለፊት፣ ባማ ሕንጻ አጠገብ በሚገኘው ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (FSS.) አዳራሽ ውስጥ ነው፡፡

በሌላ መረጃ 'የተረክ ኃይል' (The Power of Myth) በሚል ርዕስ ውይይት ይደረጋል፡፡ በዐውደ ፋጎስ የውይይት ክበብ የተሰናዳው ይሄ መሰናዶ ነገ ከቀኑ 8:00 ሰዓት ጀምሮ ይደረጋል፡፡ የውይይቱን መነሻ ጽሑፍ የሚያቀርበው መምህር ፀጋው ማሞ ሲሆን፣ ውይይቱ የሚካሄድበት ቦታ ደግሞ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት (ወመዘክር) አዳራሽ ውስጥ ነው።

## ሙዚቃ

የድምፃዊ ሀይሉ አመርጋ 'አሁን' የተሰኘው አዲስ የሙዚቃ አልበም በመደመጥ ላይ ይገኛል፡፡ ሙዚቀኛው በራሱ የዩቲዩብ ቻናል እና በዓለም አቀፍ የሙዚቃ ማሰራጫ መተግበሪያዎች በኩል ነው ለሙዚቃ አፍቃሪያን ያቀረበው። በአልበም ስራው ላይ ሚካኤል ሀይሉ (ሚኪ ጃኖ)፣ ብ ሩ ክ አፈወርቅ፣ በረከት ተስፋአፅቂ፣ ኤርሚያስ ሞላ፣ አበጋዝ ክብረወርቅ ሽዎታ እና ሮቤል ዳኜ፣ አክሊሉ ገ/መድህንና ወንደሰን ይሁብ በግጥም፣ በዜማና በሙዚቃ ቅንብር ተሳትፈዋል። ሀይሉ አመርጋ የታዋቂው የጃኖ ባንድ መስራች ከሆኑ ድምጻውያን መካከል አንዱ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ከዚህ ቀደም በባንዱ አማካኝነት ተወዳጅ ሙዚቃዎችን ለአድማጭ በማቅረብ ዕውቅና ያገኘ ሙዚቀኛም ነው፡፡ ይሄን የሙዚቃ አልበም ግን ከባንዱ ውጪ ለብቻው የሰራው የመጀመሪያ የሙዚቃ አልበሙ ነው፡፡

## ሥዕል

'አብሮነት' የሥዕል አውደ ርዕይ የፊታችን ረዕቡ ህዳር 3 ቀን 2018 ዓ.ም በፈንደቃ የባህል ማዕከል ውስጥ በይፋ ይከፈታል፡፡ አውደ ርዕዩ ሰዓሊያን በቡድን ሆነው ያሰናዱትና አብሮነትና ህብረትን የሚያሳዩ የሥዕል ስራዎች የሚቀርቡበት ነው፡፡ በአውደ ርዕዩ ላይ የሥዕል ሥራዎቻቸውን ከሚያቀርቡ መካከል ብሩ ወርቁ፣ ያሬድ ወንድወሰንና ዘውዱ ገብረሚካኤል ይገኙበታል፡፡ የስዕል አውደ ርዕዩ እስከ መጪው ህዳር 29 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ ለተመልካች ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር

በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## የቴአትር መርሃግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ፡፡ ቅዳሜ 8:30 ሰዓት 12ቱ እንግዶች፣ 11፡30 ሰዓት ደግሞ ባሎችና ሚስቶች እንዲሁም እሁድ በ8፡30 ሰዓት ንጉሥ አርማህ፣ እንዲሁም 11፡30 ሰዓት እምዬ ብረቷ የተሰኙ ቴአትሮች በብሔራዊ ቴአትር ይታያሉ። በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ደግሞ እሁድ በ8:00 ሰዓት በዓሉ ግርማ ቤርሙዳ የተሰኘው ቴአትር ይታያል፡፡

በተጨማሪም ማክሰኞ በ11፡30 ሰዓት ሶስቱ አይጦች፣ ረዕቡ በ11፡30 ሰዓት የቅርብ ሩቅ፣ ሐሙስ 11:30 ሰዓት ሽምጋይ እንዲሁም አርብ በ11፡30 ሰዓት የሕይወት ታሪክ በብሔራዊ ቴአትር ለጥበብ አፍቃሪያን ለዕይታ ይቀርባሉ፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡ በቀላሉ መልሱን ለማግኘት በቀኝ በኩል በታችኛው ረድፍ ያለውን ቁጥር በራሱ ቁጥር እናባዛዋለን፡፡ አባዝተን የምናገኘው ውጤት በግራ በኩል ከላይና ከታች የተቀመጡትን ቁጥሮች ደምረን ከምናገኘው ውጤት ጋር እኩል መሆን ይኖርበታል፡፡ በሌላ በኩል በግራ በኩል ከላይና ከታች የተቀመጡትን ቁጥሮች ደምረን የምናገኘው ውጤት በግራ በኩል ባለው ቁጥር ብናካፍለው ራሱ ቁጥሩ ይመጣል፡፡ ለአብነትም የመጀመሪያው ክብ አሰራሩ የሚከተለው ነው፡፡ 4 X 4 = 16 ይሆናል፡፡ 5 + 11 = 16 ይሆናል፡፡ 16 ÷ 4 = 4 ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት የጥያቄው ትክክለኛ መልስ 4 ይሆናል፡፡ አሰራሩም እንደሚከተለው ነው፤ 3 X 3 = 9 ሲሆን በግራ በኩል ከላይና ከታች ሲደመሩ ወይም 7 + 2 = 9 ይሆናል፡፡ 9 ÷ 3 = 3 ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት የጥያቄው መልስ 3 ይሆናል፡፡




## የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት ዕትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# ከማዝናናት የሚሻገረው የጥበብ ማዕከላት ሚና

**በአብርሃም ገብሬ**

ዛህራ አል-ዛድጃሊ የኪነ ጥበብ ሥራዎችና የጥበብ መድረኮች ከባህል እሴቶች ጋር ያላቸውን ተዛምዶ ያጠኑ ምሁር ናቸው፡፡ “The Significance of Art in Revealing a Culture's Identity and Multiculturalism” በሚል ርዕስ በፈረንጆቹ በጥር 2024 ያሳተሙት ጥናታዊ ጽሑፍ ይህንኑ ጭብጥ በስፋት ይዳስሳል፡፡ በዚህ ጥናት ላይ እንደሰፈረው፣ ጥበባዊ የፈጠራ ሥራዎችና ክዋኔዎች የባህልን ማንነት አጉልቶ በማሳያነትና በመጠበቅ ረገድ ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ ከእነዚህ ሚናዎች መካከል የህብረተሰቡን አተያይ በመቅረጽ፣ የጋራ ማንነትን በመፍጠርና ማኅበራዊ ትስስርን በማጎልበት ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አላቸው የሚለው አንዱ ነው፡፡ በተለይ የክውን ጥበባት በጋራ የሚደረጉ ልምምዶች በመሆናቸው ህብረትንና የጋራ ርዕይን የመቅረጽ አቅም አላቸው። ምክንያቱም ሰዎች በአንድነት ሆነው ትርዒት ሲመለከቱና በትርዒቱ ሲሳተፉ የጋራ ስሜታዊ ተሞክሮ ይፈጥራሉ፡፡ ይህ ደግሞ የኅብረተሰብ ስሜትን፣ አብሮነትን እና የጋራ ማንነትን እንደሚያጠናክር ምሁሯ በጥናታቸው አስፍረዋል፡፡

ኢትዮጵያ ደግሞ ጥንታዊ ስልጣኔና ረዥም የመንግስትነት ታሪክ ካላቸው ጥቂት ሀገራት መካከል አንዷ ነች፡፡ ከዚህ ጥንታዊ ሥልጣኔና ታሪክ የወረስናቸው መልከ-ብዙ ቅርሰ-ውርሶች (legacies) ደግሞ ኢትዮጵያን አድምቀዋታል። እነዚህን ቅርሰ-ውርሶች ኢትዮጵያን ባለ-ብዙ ባህል፣ ሀይማኖት፣ ቋንቋ፣ ሙዚቃ፣ ጭፈራ... ባለቤት እንድትሆንም አስችሏታል፡፡ ዛሬ ላይ የምናያቸው መልከ ብዙ ትውን ጥበባትና ክዋኔዎች የታሪካችን ቅርሰ-ውርሶች ናቸው፡፡

በተለይ እንደ ጭፈራና ሙዚቃ ያሉ ጥበባዊ ክዋኔዎች የማህበረሰቡ አካል ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም። በገጠሪቱ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ጭፈራ፣ በክዋኔ የታጀቡ የወል ዘፈኖችና የሙዚቃ መሳሪያዎችን መጫወት የባህል ልምምድ እንጂ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብተው የሚማሩት ነገር አይደለም፡፡ እነዚህ ክዋኔ ጥበባት የማህበረሰቡ አካል በመሆን አባላቱን ለዘመናት ያስተሳሰሩ እሴቶች ናቸው፡፡ በዚህ አጭር ዓምድም በመዲናችን አዲስ አበባ የተገነቡ ቴአትር ቤቶችና የጥበብ ማዕከላት ትውን ጥበባትና ልዩ ልዩ ማህበረሰባዊ የጥበብ ክዋኔዎች ይበልጥ ጎልተው እንዲወጡ፣ እንዲያድጉና የአስተሳሳሪነት ሚናቸው እንዲጎለብት በማድረግ ረገድ ያላቸው ሚና ምን እንደሚመስል በጨረፍታ ዳስሰናል፡፡


ፎቶ- ከገፀ ድር
በቅርቡ የተመረቀው የአዲስ ሲኒማ ኮምፕሌክስ ዘመናዊ የሲኒማ ማዕከል ከፊል ገፅታ

## ባህል፣ እሴት፣ ጥበባዊ ክዋኔዎች እና ጥበባዊ መድረኮች

ኢትዮጵያ ብዝሃ ማህበረሰብና ባህሎች ያሉባት ሀገር ነች፡፡ በዚሁ ልክ መልከ-ብዙ ጭፈራዎች፣ ባህላዊ ሙዚቃዎችና ክውን ጥበባት ያሏት ሀገር ነች፡፡ ለአብነትም የሙዚቃ ዝግጅት ከሚደረግባቸው የባህል ምሽቶች ውስጥ የሀገራችን መልከ-ብዙ ጭፈራዎችና በክዋኔዎች የታጀቡ የባህል ሙዚቃዎች መመልከት ብዙም እንግዳ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያውያንም በእነዚህ ክዋኔዎች ላይ ተሳትፎ በማድረግ ሲዝናኑ መመልከት የተለመደ ነው። ነገር ግን ተሳትፎው ከመዝናናት ወይም በክዋኔዎቹ ከመታደም የተሻገረ ጥልቅ አስተሳሳሪ የወል ማንነትን እንደሚፈጥሩ የባህል (ፎክለር) እና ኪነ ጥበባዊ ጉዳዮች ተመራማሪ ወሰን ባዩ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት አብራርተዋል፡፡ ክውን ጥበባት መድረክ ላይ በሚቀርቡበት የጥበብ መድረክ ላይ ስንታደም ከሌሎች ባህሎች፣ ልምዶች እና ታሪኮች መማር ብቻ ሳይሆን ዕሴትንም የመጋራት ዕድል ይፈጥርልናል፡፡ በዚህ ምክንያት በተለያዩ ባህሎች እና አመለካከቶች መካከል የእሴቶች መወራረስና የጋራ ማንነት እንዲፈጠር ያደርጋሉ፡፡ ይህ ሚና ብዙሃኑን ከማዝናናት ባሻገር ስለ ራሳችን በጥልቀት እንድናውቅ፣ በልዩነት ውስጥ የጋራ ማንነት እንዳለን እንድንገነዘብና በሀገራዊ ጉዳይ ላይ አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንድናደርግ ትልቅ መነሳሳትን እንደሚፈጥር ምሁሩ አጫውተውናል፡፡

እነዚህ መልከ-ብዙ ክውን ጥበባት ትልቅ የሆነ አስተሳሳሪ ሚና እና ማንነታችንን ይበልጥ እንድንገነዘብ የሚያስችሉን እሴቶች በመሆናቸው፣ ዘመኑን የዋጁ መድረኮች ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ የባህሎችና እሴቶች መወራረስ እንዲፈጠር የሚያደርጉትም ዜጎች የሚሰባሰቡባቸው ምቹ መድረኮች ሲኖሩ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በመዲናዋ የተገነቡ ቴአትር ቤቶችና የጥበብ ማዕከላት እነዚህን እሴቶች ጎልተው እንዲወጡ በማስቻል ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አላቸው ብለዋል፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በመዲናችን አዲስ አበባ ነባር የቴአትር ቤቶችን በዘመናዊ መልክ ከማደስ ጎን ለጎን አዳዲስ ዘመናዊ ቴአትር ቤቶችና የጥበብ ማዕከላት ተገንብተው ተመርቀዋል፡፡ ለአብነትም በቅርቡ እንኳን የህፃናትና ወጣቶች ቴአትርና ሲኒማ ኮምፕሌክስን ጨምሮ፤ እጅግ ዘመናዊ እንደሆኑ የተመሰከረላቸው አዳዲስ ሲኒማ ኮምፕሌክስ ህንፃዎች ተመርቀዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ከሳምንት በፊት የተመረቀው የአዲስ ሲኒማ ኮምፕሌክስ ህንፃን አስመልክተው በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባጋሩት መረጃ፣ አዲሱ ሲኒማ ኮምፕሌክስ ህንፃ፣ ባለ 15 ወለል ነው። የህንፃው አጠቃላይ ስፋት 24 ሺህ ካ.ሜ ሆኖ ባለ አራት ወለል የመኪና ማቆሚያ የያዘ ነው። 592 ህፃናትንና 887 አዋቂዎችን የመያዝ አቅም ያላቸው ሁለት የሲኒማ አዳራሾችን ጨምሮ በቂ የሆነ የድምፅ ማስተላለፊያ ሲስተም፣ ዘመናዊ የመብራት ስርጭት፣ የአየር መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን አካትቷል። በተጨማሪም፤ ለቢሮዎች፣ ለስቱዲዮ፣ ለሥዕል እና አርት ጋለሪ፣ ለቤተ መጻሕፍት እና ለተለያዩ ተያያዥ አገልግሎቶች የሚውሉ ክፍሎችን ማሟላቱን ባጋሩት መረጃ ይፋ አድርገዋል፡፡

በመዲናዋ የተገነቡ እነዚህ ዘመናዊ ቴአትር ቤቶችና የጥበብ ማዕከላት ትልቁ ዓላማቸው ኪነ ጥበባዊ የፈጠራ ሥራዎች እንዲጎለብቱ ማገዝ ነው፡፡ ጥበባዊ የፈጠራ ሥራዎች ደግሞ በአንድም ሆነ በሌላ ከማህበረሰቡ ባህልና እሴት የሚመነጩ ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት የአንድ ሀገር ጥበባዊ የፈጠራ ሥራዎች ማደግ በማህበረሰቡ ውስጥ መልከ-ብዙ አስተዋጽኦ እንዳለው ጥናቶች ያሳያሉ። በመዲናዋ የተገነቡ ቴአትር ቤቶችና የጥበብ ማዕከላት በዜጎች ላይ የሚፈጥሩት አዎንታዊ ተጽዕኖ ትውልድን ከማነጽ ተለይቶ የሚታይ አይደለም፡፡ ትውልዱ ከማንነቱ ጋር ይበልጥ እንዲተዋወቅ፣ እሴቶቹን እንዲያከብርና ለቀጣይ ትውልድ እንዲያስተላልፍ መደላድል ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ትውን ጥበባትና ክዋኔዎች መድረክ እንዲገኙና ይበልጥ እንዲጎለብቱ ትልቅ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡

መሐመድ አልዶጋን የተባሉ ተመራማሪ፣ በፈረንጆቹ በሰኔ 2025 በሪሰርች ጌት ገጸ-ድር ላይ “Performing Arts and Audience Satisfaction” በሚል ርዕስ ባሳተሙት ጥናታዊ ጽሑፍ ክውን ጥበባት ምቹ መድረክ አግኝተው ለሕዝቡ ሲቀርቡ ህብረተሰቡን ከማዝናናት ያለፈ ሚና እንዳላቸው አስፍረዋል፡፡ ክውን ጥበባት ማህበረሰባዊ እሴቶችን አጉልቶ ማሳየት ብቻም ሳይሆን በክውን ጥበባት አማካኝነት ማህበረሰቡን የመሄስ አቅም አላቸው። ማህበረሰቡ ራሱን እንዲመለከት ያደርጋሉ፡፡ ተመልካቾችም የተለያዩ አመለካከቶችን እንዲያዳምጡና መልከ-ብዙ እሴቶችን እንዲያውቁ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ። እነዚህን ጥበባዊ ተግባራት ዕውን ለማድረግ የጥበብ ማዕከላትና መድረኮች ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት የመዲናዋ አዳዲስ ቴአትር ቤቶችና የጥበብ ማዕከላት ጉልህ ሚና እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡

ጥበባዊ የፈጠራ ሥራዎችና ክውን ጥበባት የማህበረሰቡ እሴቶች መሆናቸውን ያጫወተን ደራሲና ሃያሲ ዋለልኝ አየለ፣ እነዚህን ጥበባዊ እሴቶች ጠብቆ ለማቆየትና ይበልጥ እንዲጎለብቱ አመቺ ሁኔታ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በከተማዋ የተገነቡ ቴአትር ቤቶችና የጥበብ ማዕከላት በዚህ ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ እነዚህ ዘመናዊ ቴአትር ቤቶችና የጥበብ ማዕከላት ባህልን ያሳድጋሉ፤ እሴቶችን ጠብቀው ለትውልድ ለማቆየትም ቁልፍ ሚና አላቸው። በተለይ ብዙም ትኩረት ያላገኙና በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ የሚገኙ ክውን ጥበባት ይበልጥ መድረክ እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ ብሎ እንደሚጠብቅ አጫውቶናል፡፡

የሀገራት ተሞክሮን ስንመለከት ምቹ የጥበብ ሥፍራዎችና በስፍራዎቹ ላይ የሚከይኑ ኹነኛ ባለሙያዎች መኖር ለአንድ ሀገር ሃያልነት ትልቅ ሚና እንዳለው መረዳት አይከብድም፡፡ ለዚህ ጥሩ አብነት አሜሪካ ነች፡፡ ዛሬ ላይ አሜሪካ ልዕለ ሃያል ሀገር እንድትሆንና ተጽዕኖዋ መላው ዓለም እንዲዳረስ ካደረጉ ተቋማት መካከል ዋነኞቹ የባህልና የጥበብ ተቋሞቿ እንደሆኑ ይታወቃል። ለዚህ ጥሩ ማሳያው ሆሊውድ ነው፡፡ ሆሊውድ ከ1920ዎቹ ጀምሮ የአሜሪካ የፊልም ኢንዱስትሪ (Cinema) እና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ዋና ማዕከል በመሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቅ ስም ነው። “ሆሊውድ” የሚለው ስም ራሱ በብዙ መልኩ የአሜሪካን የፊልም እና የመዝናኛ ኢንዱስትሪ በጠቅላላ የሚወክል ሆኗል። ይህ ኢንዱስትሪ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር የሚንቀሳቀስበት ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ ተመልካችን ለመሳብ የተበጁ ዘመናዊ እና ግዙፍ ፊልሞችን በማምረት ይታወቃል።

ጥናቶች እንደሚያሳዩት የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ተጽዕኖ ከሆሊውድ ጋር ያለው ትስስር ጥልቅ እና ውስብስብ ነው። ሆሊውድ ለአሜሪካ “ለስላሳ ኃይል” (Soft Power) ከሚባሉት ዋና መሳሪያዎች መካከል አንዱ ነው። ከዚህ አንጻር አሜሪካ የባህል ማስፋፋት (Cultural Diffusion) የምትከውንበት ዋነኛ መሳሪያዋ ነው። ሆሊውድ በአሜሪካ የአኗኗር ዘይቤ፣ ልማድ፣ እሴቶች እና ፋሽን ወደ ሌላ ዓለም በማሰራጨት ረገድ ትልቅ ተጽዕኖ አለው። ፊልሞች እና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች የአሜሪካን ባህልና የአስተሳሰብ ዘይቤ ወደተለያዩ የዓለም ክፍሎች በሰፊው ያሰራጫሉ፡፡ ይህም የአሜሪካን ምርቶች እና አገልግሎቶች ተቀባይነት እንዲያገኙ ያግዛል። ምንም እንኳን የመዝናኛ ዓላማ ቢኖራቸውም፣ የሆሊውድ ፊልሞች ብዙውን ጊዜ የአሜሪካን የፖለቲካ አስተሳሰቦች፣ ጀግንነት እና ልዕለ-ሃያልነትን ያንፀባርቃሉ። እነዚህ መልዕክቶች በዓለም አቀፍ ተመልካቾች ዘንድ ስለ አሜሪካ አዎንታዊ ግንዛቤ እንዲፈጠር አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። መዘንጋት የሌለበት አንዱ ቁልፍ ጉዳይ ግን የዚህ ሁሉ ምንጭ አሜሪካ የገነባችው እጅግ ዘመናዊ የፊልም ማምረቻ መንደርና ለዚህ ግዙፍ የሲኒማ መንደር የሰጠችው ትኩረት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የተገነቡ ቴአትር ቤቶችና የጥበብ ማዕከላት የማህበረሰቡን የክውን ጥበባት እሴቶችን ከመጠበቅ ባሻገር፣ የአፍሪካ መዲና ለሆነችው አዲስ አበባም ሆነ ኢትዮጵያ ተጽዕኖዋ ይበልጥ እንዲጎላም ያስችላሉ፡፡

በአጠቃላይ በመዲናዋ የተገነቡ የጥበብ ማዕከላትና ዘመናዊ ቴአትር ቤቶች ትውልድን በማነጽና ነባር እሴቶችን ወደ ቀጣዩ ትውልድ በማሻገር ሂደት ውስጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡ የፈጠራ ስራዎች እንዲዳብሩ፣ እንደ ክውን ጥበባት ያሉ ባህላዊ እሴቶች መድረክ እንዲያገኙና የወል ማንነት እንዲገነባ ምቹ መደላድል ይፈጥራሉ፡፡ ከዚህ አንጻር የመዲናዋ አዳዲስ ቴአትር ቤቶችና የጥበብ ማዕከላት ዘመን ተሻጋሪ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡

# የከተማ ግብርና አብነቶች

• የሚመረተው የጓሮ አትክልት ትኩስና ንፁህ መሆኑ ለጤናቸው አዎንታዊ አስተዋፅኦ ማድረጉን ተጠቃሚዎች ገልፀዋል።

**በፋንታነሽ ተፈራ**

የከተማ ግብርና በሰፊም ይሁን በአነስተኛ ቦታ፣ ለምግብነትና ለገቢ ምንጭነት ሊውሉ የሚችሉ እፅዋትን የማልማት፣ እንስሳትን የማርባት፣ የግብርና ምርት ውጤቶችን ከማምረት ባሻገር የማቀነባበር እና ለተጠቃሚዎች የማቅረብ ስራን የሚያካትት ነው። ብዙዎች በዚህ ዘርፍ በመሰማራት ተጠቃሚ በመሆን ላይ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ትጉህ፣ መስራት ከማይታክታቸው ከራሳቸው ይልቅ የማህበረሰቡን ጥቅም ካስቀደሙ ጠንካራ አባቶች አቶ ጥላሁን ያለው አንዱ ናቸው፡፡

አቶ ጥላሁን የከተማ ግብርናን የጀመሩት በመኖሪያ ቤታቸው ቅጥር ግቢ ውስጥ አጥራቸው አጠገብ ጎመን፣ ቆስጣ፣ ሰላጣና መሰል የጓሮ አትክልቶችን በማልማት ነበር። ስራ ወዳድነታቸው፣ ጠንካራና ታታሪነታቸው እንዲሁም ከራሳቸው አልፈው ማህበረሰቡንም ይጠቅማሉ በማለት የጉለሌ ክፍለ ከተማ እና የወረዳ 10 አስተዳደር 700 ካሬ ቦታ ላይ የከተማ ግብርና የሚሰሩበትን እንዲያለሙ እንደሰጧቸው ነግረውናል። ቦታው ሲሰጣቸው የቆሻሻ መድፊያ የነበረ በመሆኑ ለስራው ምቹ ለማድረግ ከፍተኛ ወጪ በማውጣት አስተካክለውት ስራ ጀምረዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት የዶሮ እርባታ እና የጓሮ አትክልት ስራዎችን በስፋት እየሰሩበት ነው፡፡

በከተማ ግብርናው ተግባር የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችን አምርቶ ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ ዓላማቸው ያደረጉት አቶ ጥላሁን፤ ከሚያለሟቸው ልማቶች ለምግብነት ከሚያገለግሉ አትክልቶች መካከል ጎመን፣ ሰላጣ፣ ቀይ ስር፣ ስፒናች፣ ካሮት፣ ነጭ ሽንኩርት፣ በሶብላ፣ ኮሰረት፣ የስጋ መጥበሻ፣ ጤናዳም የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ሌሎች ከምግብነት ውጭ የወይን ተክል፣ ጌሾ፣ ቡና፣ እንሰትና መሰል ተክሎችን በቦታው ላይ እያለሙ ይገኛሉ፡፡

እንደ ጎመን፣ ቆስጣ እና ሰላጣ የመሳሰሉት የጓሮ አትክልቶች ለማህበረሰቡ ትኩስ፣ በመጠንም ውጭ ላይ ከሚሸጠው ብዛት ያለው እና ዋጋውም በግማሽ በሚቀንስ እንደሚሸጡ ገልፀው፤ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ትኩስ የጓሮ አትክልታቸው ተቋዳሽ እንዲሆኑ ለማድረግ ለአንድ ግለሰብ ከአንድ እስር በላይ ጎመንም ይሁን ቆስጣ እንደማይሸጡ ነግረውናል፡፡

አትክልት ስለምወድ በመኖሪያ ቤቴ አጥር አጠገብ፣ በተለያዩ እቃዎች ላይ ሳይቀር ጎመን፣ ቆስጣ፣ ሰላጣ፣ ስፒናች እና የመሳሰሉትን የጓሮ አትክልቶች አለማለሁ፤ የራሴንም ፍጆታ እሸፍናለሁ የሚሉት አቶ ጥላሁን፤ ብዙ ወጭ አውጥቼበት የምሰራበት ይህ ቦታ ሰዎች ጥቅም ላይ የማይውሉ የሚመስሏቸው ነገሮች ጥቅም ላይ ሲውል እያዩ እንዲማሩበት፣ ትኩስና ጤናማ ምግብ ማግኘት እንዲችሉ እንዲሁም ጊዜያቸውን ያለ አግባብ የሚያባክኑና አልባሌ ቦታ የሚያሳልፉ የማህበረሰብ ክፍሎች በሚኖሩበት ቦታ ማልማት እንዲችሉ ለማስተማር ያግዛል ይላሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት የክረምቱ በረዶ የጓሮ አትክልታቸውን አበላሽቶባቸው ለገበያ



ፎቶ በገነት ወንድሙ

የከተማ ግብርናን በስፋት በመስራት በጉለሌ ክ/ከተማ ተምሳሌት የሆኑት አቶ ጥላሁን ያለው

የሚቀርብ የጓሮ አትክልት ባይኖርም ከዚህ በፊት በቀን ከ200 እስከ 300 የሚሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች ተሰልፈው ይገዟቸው እንደነበር አስታውሰው "ይህ ለእኔ ደስታ ነው፤ ከዚህ በላይ የሚያስደስተኝ ምንም ነገር የለም። ለምግብ የደረሰውን የጓሮ አትክልት ከመሸጥ ባለፈ ሰዎች በመኖሪያ ቤታቸው እቃ ላይም ቢሆን እዲያለሙና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከምዘራው ዘር እሰጣቸዋለሁ" የሚሉት አቶ ጥላሁን ማህበረሰቡ ሲጠቀም የሚደሰቱ መሆናቸውን ነግረውናል፡፡

በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚኖሩት የማህበረሰብ ክፍሎች ገንዘብ ጨምሬ እና መጠን ቀንሼ ከምሸጥ በተመጣጠነ ዋጋ ትኩስ አትክልት በማቅረብ ደስታዬን እመርጣለሁ የሚሉት አቶ ጥላሁን፤ በዶሮ እርባታ ስራው ላይ ወደፊት የገቢ ምንጭ ይሆናሉ በማለት 350 ዶሮዎችን እያረቡ ይገኛሉ፡፡ ምርት መስጠት የጀመሩት ዶሮዎች በቀን እስከ 150 እንቁላል ይጥላሉ፡፡ ወደፊትም የተሻለ ገቢ እንደሚያስገኙ ተስፋን ሰንቀው እየሰሩ እንደሚገኙ ነው የነገሩን፡፡

በመዲናዋ የተጀመረው የከተማ ግብርና ነዋሪዎች ከጓሯቸው አትክልትና ፍራፍሬዎችን እንዲሁም የወተት ተዋፅኦዎችን እንዲያገኙ እያደረገ ነው። እኔም ወደፊት እንቁላሉን በመሸጥ ተጠቃሚ የምሆንበት ጊዜ ሩቅ አይደለም።

አቶ ጥላሁን ከስራ ወዳድነታቸው፣ እንደ እሳቸው ሰዎችም እንዲሰሩ ለማበረታታት ሁሉም በየደጃፉ የጓሮ አትክልት አልምቶ ተጠቃሚ እንዲሆን ከመፈለጋቸው የተነሳ "አንድ ወር እና ሁለት ወር በኋላ ለእናንተ ጎመን አልሸጥም ደጃፋችሁ ላይ አልሙ ከእናንተ አልፎ ለሌሎችም ትተርፉላችሁ" ብለው መክረው እደንሚሸኟቸው ነግረውናል፡፡

የጓሮ አትክልት ማልማት የመንግስት ሰራተኞች ከስራ ሲመለሱ በተለይ ወንዶቹ ገንዘብና ጊዜያቸውን እንዳያባክኑ ከማገዙም በተጨማሪ ትኩስና ጤናው የተጠበቀ ተመጣጣኝ ምግብ እንዲመገቡ ያደርጋቸዋል፡፡ የጓሮ አትክልት በተለያዩ ቆሻሻ ፍሳሾች ሳይሆን በንፁህ ውሃ ስለሚመረት፣ እንዲሁም ወዲያውኑ ተቆርጦ ጥቅም ላይ ስለሚውል በሽታ አምጭ ሳይሆን በሽታ ተከላካይና ለጤና ወሳኝነት ያለው መሆኑን ከራሳቸው ተሞክሮ በመነሳት ይናገራሉ፡፡

የከተማ ግብርናውን ስራ ውጤታማ ለማድረግ ዋጋው እየጨመረ የመጣውን የዶሮዎች መኖ ለራሳቸውም ሆነ ለሚፈልጉ ሌሎች አካላት አምርተው ለማቅረብ እቅድ እንዳላቸው ገልፀው፤ ይህም ሲሆን ማህበረሰቡ በቅናሽ በመግዛት ዶሮ እርባታ ስራ ላይ እንዲሰማራ የሚያግዘው ነው የሚሆነው ይላሉ፡፡

በከተማ ግብርና ላይ እየታየ ያለው መሻሻልና ተሞክሮ የሚደነቅ ነው፤ መንግስት ለእያንዳንዱ ሰው ዶሮዎችን እየገዛ ሲሰጥና ተጠቃሚ ሲያደርግ እየተመለከትኩ ነው፡፡ ይህ ተግባር የአንድ ወቅት ስራ ብቻ ሳይሆን ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ባይ ነኝ ይላሉ፡፡

ለአቶ ጥላሁን የስራ ታታሪነትና ስራ ወዳድነት እንዲሁም ጤናማ የጓሮ አትክልቶችን አምርቶ ለማህበረሰቡ ተጠቃሚ ማድረጋቸውን ወይዘሮ ብልጫ አምዲሁን ይመሰክራሉ፡፡ የሽጎሌ መንደር 7 አካባቢ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮዋ፤ አቶ ጥላሁን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የሚሰሩ ናቸው። የሚመረተው የጓሮ አትክልት በሚደርስበት ወቅት በተመጣጠነ ዋጋ እና በመጠንም ገበያ ላይ ከሚሸጠው የተሻለ እገዛለሁ፡፡ ትኩስና ንፁህ በመሆኑ ለጤና ተመራጭ ነው፡፡ በዚህ ስራ ከተሰማሩ ጀምሮ የጓሮ አትክልቶቹ ሲደርሱ ተጠቃሚ ነኝ" ሲሉ ደስተኛ መሆናቸውን ነግረውናል፡፡

ከአቶ ጥላሁን የተማርኩት ሸጠው ገንዘብ ስለማግኘት ሳይሆን ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ መሆኑን እና ሰዎች በቤታቸው ተክለው እንዲጠቀሙ ማበረታታቸውን ነው ሲሉም በራሳቸው ለራሳቸው ማልማት እንዳለባቸው መማራቸውን ነው የነገሩን፡፡

ሌላኛው የአቶ ጥላሁንን የደረሰ የጓሮ አትክልት ገዝተው ከሚጠቀሙ አካላት ውስጥ አንዱ ነኝ የሚሉት ደግሞ አቶ ኤሊያስ ገብረወልድ ናቸው፡፡ "እንክብካቤ ሲደረግለት የምመለከተውና ለእይታ የሚማርከው ጎመኑም ሆነ ቆስጣው እስከሚደርስ በጉጉት ነው የምጠብቀው፤ በዋጋም ሆነ በመጠን ገበያ ላይ ከሚሸጠው ጋር ይለያያል። ጣዕሙም ቢሆን ጣፋጭ ነው፡፡ ገበያ ላይ ከ50 እስከ 60 ብር የሚሸጠውን አትክልት አቶ ጥላሁን ጋር የምንገዛው 30 ብር ነው" ሲሉ ተጠቃሚ መሆናቸውን ነው የነገሩን፡፡

ወረፋ ስለሚሆን ተሰልፎ መግዛት በማልችልበት ወቅት እንዲያስቀምጡልኝ ደውዬ እነግራቸዋለሁ የሚሉት አቶ ኤሊያስ፤ ከአቶ ጥላሁን ከራስ ይልቅ ሌሎችን ማስቀደም ደስተኛ እንደሚያደርግ ተምሬያለሁ ይላሉ፡፡

አቶ ጥላሁንን በስራ የሚያግዛቸው ወጣት ብርሃኑ ባበይ "እኔ በሰለጠንኩት የዶሮ እርባታ እንክብካቤ መሰረት ዶሮዎችን የመንከባከብ ስራ እሰራለሁ። የሚያስፈልጋቸውን ምግብም ሆነ ውሃ እንዲሁም የፅዳት ስራዎችን አከናውናለሁ፡፡ ጊዜ ሲኖረኝም የጓሮ አትክልቱን በመንከባከብ አግዛለሁ፡፡ ትኩስ አትክልቶችን ከዚሁ እጠቀማለሁ፤ ስራ ያልነበረኝን ስራ እንዲኖረኝ አድርገውኛል፡፡ በስራቸውም ታታሪ በመሆናቸው እኔም ጠንክሬ እንድሰራ አቅም ሆነውኛል ሲል ነው የአቶ ጥላሁንን ስራ ወዳድነት እንዲሁም ለማህበረሰቡ አሳቢነት የነገረን፡፡

በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ፅህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ቸርነት ሽፈራው በበኩላቸው፤ ወረዳውና ክፍለ ከተማው ቦታ ሰጥቷቸው ከተማ ግብርናን በማልማት አቶ ጥላሁን ሞዴል መሆናቸውን አንስተው፤ አቶ ጥላሁን የከተማ ግብርናን ለመስራት ካላቸው ፍላጎትና ተነሳሽነት የመነጨ የቆሻሻ መጣያ የነበረውን ቦታ ብዙ ወጪ አውጥተው ለልማት አውለውታል። በዚህም ማህበረሰቡ ንፁህና ጤናው የተጠበቀ አትክልት እንዲያገኝ ሆኗል። በቅርብ ጊዜም እንቁላል ጣይ ዶሮዎችን በመግዛት ማህበረሰቡን የእንቁላል ተጠቃሚ እያደረጉ ይገኛሉ። ማህበረሰቡም እሳቸውን በማየት እየተነሳሳና እንቁላል ጣይ ዶሮዎች እንዲሰጡት እየጠየቀ ነው ይላሉ፡፡

ሙያዊ ድጋፍ እና የዘር አቅርቦት ከመደገፍ ውጭ ሌሎች ነገሮችን ከራሳቸው በማውጣት እየሰሩ ማህበረሰቡን በቅናሽ ዋጋ እና ትኩስ ምርቶችን በማቅረብ ተጠቃሚ እያደረጉ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ለወረዳውም ሞዴል መሆን ችለዋል፡፡

እንደ ከተማ የሌማት ትሩፋትን ተግባራዊ ለማድረግ ከመስከረም 1 እስከ ታህሳስ 30 2018 ዓ.ም የሚቆይ ንቅናቄ እየተደረገ ይገኛል፡፡

በዘርፉ የተሰማሩ ተሳታፊዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ የተለያዩ የግንዛቤ ፈጠራ፣ ሙያዊ ድጋፍ፣ የዘር አቅርቦት ስራ እየተሰራ እንደሚገኝ የገለፁት አቶ ቸርነት ወደ ፊትም ትኩረት ተሰጥቶበት እንደሚሰራ ነው የነገሩን፡፡

# የጤና መድህን ውለታ እስከምን?

በፋንታነሽ ተፈራ

ወይዘሮ ዙቤዳ ሃይረዲን የተክለ ሃይማኖት አካባቢ ነዋሪ ናቸው፡፡ የዝግጅት ክፍላችን ያገኛቸው በልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ጤና ፅህፈት ቤት በተክለሃይማኖት ጤና ጣቢያ የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ሊያሳድሱ መጥተው ነው፡፡ ከአገልግሎቱ ጋር ያላቸውን ቁርኝት፣ "ክፍያው 80 ብር በነበረበት ጊዜ ጀምሮ ተጠቃሚ ነኝ" ሲሉ ገልጸውታል፡፡ የጤና መድህን ተጠቃሚ መሆን መቻላቸው እንዳስደሰታቸውም አክለዋል፡፡

ወይዘሮ ዙቤዳ በአስተያየታቸው፣ "የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን በተለይ እንደ እኔ በዝቅተኛ ኑሮ ደረጃ ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ ብዙ ጊዜ የህመም ስሜት ሲሰማኝ ቶሎ ብዬ ደብተሬን ይዤ ወደ ጤና ጣቢያ እሄዳለሁ፡፡ በምርመራው መሰረትም የሚታዘዝልኝን መድሃኒት በመውሰድ ጤናዬን እጠብቃለሁ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የህመም ስሜት ባይሰማኝም ጤናዬ ያለበትን ሁኔታ ለማወቅ ምርመራ አደርጋለሁ፡፡" ሲሉ አብራርተዋል፡፡

"የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ተጠቃሚ መሆናቸው የስኳር ህመም ታካሚ ባለቤቴን ከሞት ታድጎልኛል፡፡ በየጊዜው መድሃኒት ይወስዳል፡፡ ለዚህም የሚወጣው ወጭ ከአቅማችን ጋር አብሮ ስለማይሄድ ክትትል ላናደርግ እንችል ነበር፡፡ አሁን ግን የኢኮኖሚ ችግራችን በዚህ ጤና መድህን ተፈትቷል፡፡ አጠቃላይ ቤተሰቡ ጤናችንን ለመጠበቅ አስችሎናል" ሲሉም አክለዋል፡፡

"ጤና መድህን የጤናችን ዋስትና ነው፤ ለህክምና ጨርቅ አንጥፎ ከመለመን የሚገላግል፣ ወገን ለሌለው ወገን የሚሆን እንዲሁም ገመና ሸፋኝ ነው" ሲሉ የእሳቸውም ሆነ የቤተሰባቸው ጤና ተጠብቆ እንዲኖሩ እንዳስቻላቸው ተናግረዋል፡፡

ሌላኛው በጤና ጣቢያው የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ተጠቃሚ የሆኑት አቶ ወንድይፍራው ታደሰ ይባላሉ፡፡ "እኔና ቤተሰቦቼ ቅድመ ምርመራም ይሁን ህክምና የምናደርገው በጤና መድህናችን ነው፡፡ 'ገንዘብ የለኝም እንጂ የጤናዬን ጉዳይ ማወቅ እፈልግ ነበር' ብለን በሃሳብ ብቻ አንቀርም፡፡ የደም ግፊትም ሆነ የስኳር ምርመራ እናደርጋለን" ሲሉ ነው ጤና መድህኑን በመጠቀም ጤናቸውን እየተከታተሉ እንዳሉ የገለጹልን፡፡

"እግሬን ያመኛል፤ ይህን ለመታከም ስሄድ እንደ ስኳር፣ ደም ግፊት፣ የደም መርጋት የመሳሰሉትን ምርመራዎች አደርጋለሁ፤ በዚህም ጤነኛ መሆኔን አረጋግጣለሁ" የሚሉት አቶ ወንድይፍራው፤ የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ተጠቃሚ መሆናቸው ጤናቸውን ቀድመው ለመጠበቅ እንዳገዛቸው ገልፀዋል፡፡

በጤና ጣቢያው ጠቅላላ ሃኪም የሆኑት ዶክተር ቤተልሔም ወንድወሰን በበኩላቸው፣ የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን እያንዳንዱ ግለሰብ ወይም ቤተሰብ በዓመት አንድ ጊዜ በሚከፍለው





ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

በተክለ ሃይማኖት ጤና ጣቢያ የጤና መድህን ተጠቃሚዎች እድሳትና አዲስ ምዝገባ ሲያካሂዱ

ክፍያ ዓመቱን ሙሉ ህክምና የሚያገኙበት እና ጤናቸውን ለመጠበቅ የሚያግዝ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ወደ ህክምና ሲመጡ ምርመራውም ሆነ መድሃኒቱ በነፃ በመሆኑ ማህበረሰቡ ቅድመ ምርመራ የማድረግና ህመሙንም በመከታተል ጤናውን በመጠበቁ ረገድ ትልቅ ለውጥ እንዳለው አክለዋል፡፡

ዶክተር ቤተልሔም አያይዘው፤ በገንዘብ ምክንያት ምርመራ ያለማድረግም ሆነ መድሃኒት የማቋረጥ እንዲሁም ተስፋ የመቁረጥ ችግሮችን በመቅረፍ ጤናው ላይ ትኩረት የሚሰጥ ማህበረሰብ ተፈጥሯል፡፡ ይህንንም በጤና ጣቢያው ቅድመ ምርመራ ከሚያደርጉና ህክምናቸውን ከሚከታተሉ የማህበረሰብ ክፍሎች መመልከት መቻላቸውን ገልጸው፤ ማንኛውም የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ተጠቃሚ መንግስት ባመቻቸለት እድል ተጠቅሞ ጤናውን መጠበቅ እንዳለበት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ጤና ፅህፈት ቤት የተክለሃይማኖት ጤና ጣቢያ ሜዲካል ምክትል ዳይሬክተርና በጤና ጣቢያው የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን አገልግሎት አስተባባሪ አቶ ተመሰለው ቸርነት በበኩላቸው፤ የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ሲባል ዜጎች ጤናማ በሚሆኑበት ወቅት በሚከፍሉት አነስተኛ መዋጮ የጤና እክል በሚያጋጥማቸው ወቅት ከመድህን ቋቱ ወጪ በማድረግ የጤና ወጪያቸው የሚሸፈንበት ነው፡፡ ይህም የመደጋገፍ ባህልን ተቋማዊ ቅርፅ እንዲኖረው፣ በአባላት መካከል የእርስ በርስ መደጋገፍ እንዲፈጠር አድርጓል። የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ በመሆናቸው አኗኗራቸውም ጭምር ለበሽታ የሚያጋልጥ ነው። ይህንን በሽታ ከፍሎ የመታከምና መድሃኒት ገዝቶ የመጠቀም አቅማቸው ስለማይፈቅድ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆኑ የሚፈልገውን ምርመራ አድርጎ ጤናው ያለበትን ሁኔታ እንዲያውቁ፣ ከታመሙ ደግሞ የህክምና ክትትል በማድረግ ጤናቸው እንዲመለስ የማድረግን እድል የሚፈጥር ነው፡፡

በተለይ ደግሞ እንደ ስኳር፣ የደም ግፊት የመሳሰሉ ህመሞች ያሉባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ተጠቃሚ ሆነው ህክምና ባያደርጉ ኖሮ ከዓይነ ስውርነት እስከ ድንገተኛ ሞት ይዳረጉ ነበር። ይህ እንዳይሆን በጠዋቱ በሽታው ተለይቶ እንዲታከሙ፣ ጤናቸውን እንዲከታተሉና ህመማቸውም ቶሎ መፍትሄ እንዲያገኝ ያደርጋቸዋል ሲሉ ያለውን የጤና ጠቀሜታ ገልፀዋል፡፡

በተክለሃይማኖት ጤና ጣቢያ አዳዲስና ነባር አባላት እንዳሉ የሚናገሩት አቶ ተመሰለው ይህ መረጃ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ወረዳ አምስት 1 ሺህ 655 እና ወረዳ ሰባት 1 ሺህ 291 ነባር የጤና መድህን አባላት እድሳት አድርገዋል። ከዚህ ጎን ለጎን በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አማካኝነት የግንዛቤ ፈጠራ ስራ እና ቤት ለቤት በመዞር ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ነግረውናል፡፡

አቶ ማሙሽ ደበሬን ያገኘናቸው ሌላኛው ቅኝት ባደረግንበት ማይጨው ጤና ጣቢያ አዲስ የጤና መድህን ለመመዝገብ በመጡበት ወቅት ነው፡፡ "የምኖረው ኑሮና ለህክምና የማወጣው ወጪ ባለመመጣጠኑ የጤና መድህን ተጠቃሚ መሆንን መርጫለሁ" ይላሉ፡፡

የአቶ ማሙሽን ሃሳብ የሚጋሩት ወይዘሮ ሰላማዊት ጌታቸው የጤና መድህን ተጠቃሚ በመሆናቸው ሲያማቸው ያለስጋት ለመታከም እና ጤናቸውን ለመጠበቅ እንዳገዛቸው ነግረውናል፡፡

በማይጨው ጤና ጣቢያ ከ32 ሺህ በላይ የማህበረሰብ ክፍሎች የህክምና አገልግሎት እንደሚያገኙ የሚናገሩት ደግሞ የጤና ጣቢያው ምክትል ሜዲካል ዳይሬክተር አቶ አበበ ሳህሌ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ 92 በመቶ የሚሆኑት የጤና መድህን ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ በ2017 ዓ.ም ከ1 ሺህ 800 በላይ አባወራና እማወራ የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ተጠቃሚ ሲሆኑ በ2018 ደግሞ 2 ሺህ 500 የሚሆኑ ነባርና አዳዲስ አባላትን ተጠቃሚ የማድረግ እቅድ እንዳላቸው ነው የነገሩን፡፡

የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን በዝቅተኛ ኑሮ የሚኖረው የማህበረሰብ ክፍል የአቅሙን በማዋጣት ዓመቱን ሙሉ የሚታከምበት ስርዓት ነው፡፡ እነዚህ አካላት በማንኛውም ወቅት የጤና እክል ሲገጥማቸው ህክምና የሚያገኙበት እንዲሁም ቅድመ ምርመራ የሚያደርጉበት በመሆኑ ጤናቸውን በመጠበቁ ረገድ ፋይዳው ከፍ ያለ ነው ይላሉ፡፡ በቤተሰብ ጤና ቡድን ማህበረሰቡ ድረስ በመውረድ በሽታ የመከላከል፣ የማከም እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን እየሰሩ እንደሚገኙም አክለዋል፡፡

ማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን በኢ መደበኛ ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ ተሰማርተው የሚኖሩ ዜጎችን የሚያካትትና ማህበረሰቡን ለማገልገል የቆመ አንዱ የጤና መድህን አይነት መሆኑን ለዝግጅት ክፍላችን የነገሩን ደግሞ በኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት የአዲስ አበባ የክላስተር ፅህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ብርሃኑ አይካ ናቸው፡፡

የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን አገልግሎት ተጠቃሚዎች የሚያገኙት የጤና አገልግሎት ዓይነቶችም የተኝቶ ህክምና፣ የተመላላሽ ህክም፣ ቀዶ ህክምና፣ የላቦራቶሪና ሌሎች በህክምና ባለሙያዎች የታዘዙ ማንኛውንም ምርመራ አገልግሎቶችን ሲሆን፤ ነገር ግን በሌሎች ህጎች ሽፋን የተሰጣቸው አደጋዎች፣ ለረጅም ጊዜ የሚሰጡ የኩላሊት እጥበት ህክምና፣ የዓይን መነፅር መግዛትና ሰው ሰራሽ ጥርስ ማስተካከልና ማናቸውም ሩት ካናል(ድድ ስር የሚቆስል) ህክምናዎች በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን (ማዐጤመ) የማይሸፈኑ የህክምና አገልግሎቶች ናቸው፡፡

ዓመታዊ ክፍያውን ራሳቸው የሚከፍሉ እና በራሳቸው መክፈል የማይችሉ በሶስተኛ ወገን የሚሸፈንላቸው የቀጥታ ተጠቃሚ የማህበረሰብ ክፍሎች አሉ የሚሉት አቶ ብርሃኑ፤ የቀጥታ ተጠቃሚዎች ያሉበት የኑሮ ደረጃ በቅርብ አካላት እየተተቸ የሚመረጡና በከተማ አስተዳደሩ ክፍያው የሚሸፈንላቸው ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት በአጠቃላይ ከ2 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ተጠቃሚዎች መሆናቸውንም ነግረውናል፡፡

በማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን የማህበረሰቡን ንቃተ ህሊና ከፍ ለማድረግና ጤናው የተጠበቀ ማህበረሰብ ለመፍጠር ከጤና ቢሮ፣ ከጤና ተቋማት እንዲሁም መድኃኒት አቅርቦት ድርጅት ጋር በቅንጅት ስራዎች ይሰራሉ፡፡ በዚህ ጤና መድህን ውስጥ ተጠቃሚ የሆኑ አካላት በየዓመቱ በሚያዋጡት መዋጮ ወይም ክፍያ የጤና እክል ባጋጠማቸው ወቅት ካልታሰበ ከፍተኛ ወጪ የሚጠበቁበት አንዱ ስርዓት ነው። ይህ ሲሆን በቤተሰባቸውም ሆነ በራሳቸው ላይ የሚደርሰውን የጤና ችግር ታክሞ ለመዳን እና በሚፈልጉት ወቅት የሚፈልጉትን ምርመራ አድርገው ጤናቸው ያለበትን ሁኔታ እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ በሽታው ሳይባባስ ከተደረሰበት ቶሎ ታክሞ ለመዳን እና ጤናን ለመጠበቅ አጋዥ ነው ይላሉ፡፡

ህብረተሰቡ አንድ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ቢኖር አባላት ወደ ምዝገባ ሲሄዱ መሟላት የሚገባቸውን በሙሉ ሟሟላት እንዳለባቸው ነው፡፡ ይህም የምዝገባና እድሳት ሂደቱን የተቀላጠፈ በማድረግ የአገልግሎት ፈላጊዎችን ጊዜ ገንዘብና አቅም እንደሚያተርፍ መረዳት ይገባል፡፡

የከተማዋ ነዋሪዎች ዛሬ ነገ ሳይል የምዝገባ ጊዜው አጭር መሆኑን ተረድቶ የምዝገባ ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት አገልግሎት በሚያገኙበት ወይም በሚቀርባቸው ጤና ጣቢያ እስከ ህዳር 30 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ ነባር አባላት እድሳት እና አዲስ አባላት ምዝገባ በማድረግ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑም በዚሁ አጋጣሚ ጥሪ ለማቅረብ እወዳለሁ ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

# ልጆች፤ ስለግል ንፅህና አጠባበቅ ምን ያህል ታውቃላችሁ?



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ከአለም ማያ የመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በከፊል

**በለይላ መሃመድ**

ልጆች የግል ንጽህና አጠባበቅ ምን ማለት እንደሆነ፣ የግል ንጽህናን መጠበቅ ምን ጥቅም እንዳለው ታውቃላችሁ? አዎ እንደምትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ:: የግል ንፅህና አጠባበቅ እጅን መታጠብ፣ ጥርስን መቦረሽ፣ ፀጉርን መንከባከብ፣ ገላን መታጠብ የሚሉትንና ሌሎችንም ያካትታል። ልጆች የግል ንጽህናን መጠበቅ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት:: አንዱና ዋነኛው ጤናማ እንድንሆን ያደርገናል። በተለይም በተላላፊ በሽታዎች በቀላሉ እንዳንያዝ ያደርገናል:: ሌላው የግል ንጽህናን መጠበቅ በራስ የመተማመን ስሜት እንዲኖረን ያደርጋል።

ልጆች ታዲያ በየትኛውም ቦታ እና ጊዜ ሁሉ የግል ንጽህናችሁን መጠበቅ እንዳለባችሁ መዘንጋት የለባችሁም::

ዛሬ ትምህርት ቤት ስለምሄድ ንጽህናዬን ልጠብቅ፣ ወይም ትምህርት ቤት ስለማልሄድ ባልጠብቅም ችግር የለም የሚል አመለካከት ሊኖር አይገባም:: ይህን መነሻ በማድረግ በዛሬው ዝግጅታችን ምንጊዜም የግል ንጽህናቸውን የሚጠብቁ ልጆችን ልምድና ተሞክሮ ልናካፍላችሁ ወደድን::

ዳናይት ገዛኸኝ እባላለሁ:: እድሜዬ 12 ዓመት ነው:: የአለም ማያ የመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ነኝ:: የግል ንፅህና ገላዬንና ጸጉሬን በመታጠብ፣ ጥፍሬን በመቁረጥና ጥርሴን በመቦረሽ እንዲሁም ንጹህ ልብስ በመልበስ እጠብቃለሁ:: ይህንን የማደርገው ትምህርት ቤት ስሄድ ብቻም ሳይሆን በእረፍት ቀናትም ጭምር ነው። ንጹህ ልብስ የምለብሰው ትምህርት ቤት ስሄድ ብቻም ሳይሆን ከትምህርት ቤት ስመለስም ነው:: የቤት ውስጥ ስራ ከሰራሁ በኋላም ሆነ ከጨዋታ መልስ እጄን በውሃና በሳሙና እታጠባለሁ:: ትምህርት ቤት በማልሄድበት የእረፍት ቀኔ ለምሳሌ እሁድ ጠዋትም ጭምር ጥርሴን እቦርሻለሁ::

ስሜ በጸጋ ተከተል ይባላል:: የምማረው የአለም ማያ የመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። የግል ንጽህናችንን መጠበቅ ስንችል ራሳችንን ከተለያዩ በሽታዎች መከላከል እንችላለን:: በየትኛውም ጊዜና ቦታ በትምህርት ቤትም ይሁን በቤት ውስጥ እጄን በሳሙናና በውሃ የመታጠብ ልምድ አለኝ:: ቤቴም ልሁን ትምህርት ቤት እጄን ሳልታጠብ ምግብ አልበላም። የሰውነቴንና የልብሴን ንጽህናም እጠብቃለሁ:: ከትምህርት ቤት ውጪ ሰፈር በምውልበት ቀን ልክ ትምህርት ቤት ስሄድ ንጹህ ልብስ እንደምለብሰው ሁሉ ለጫወታም ቢሆን ንጹህ ልብስ ለብሼ ነው የምወጣው:: በሳምንት አንድ ጊዜ ጥፍሬንና ጸጉሬን እቆርጣለሁ። ሁልጊዜ ንጹህ መሆን ነው የምፈልገው። በንጽህና ጉድለት አንድ ቀን ታምሜ ከትምህርት ቤት ቀርቼ አውቃለሁ:: ስለሆነም ሁላችሁም ንጽናችሁን መጠበቅ ያለባችሁ ትምህርት ቤት ስትሄዱ ብቻም ሳይሆን በቤታችሁ ውስጥም መሆን አለበት::

ቃለአብ ደርጉ እባላለሁ:: የአለም ማያ የመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ነኝ:: የግል ንጽህናዬን የምጠብቀው በሁሉም ቦታ ነው:: በትምህርት ሰዓትም ይሁን ትምህርት ቤት በማልሄድበት ጊዜ ከመኝታዬ እንደተነሳሁ መጸዳጃ ቤት እገባለሁ:: ከመጸዳጃ ቤት መልስ እጄን እና ፊቴን በውሃና ሳሙና እታጠባለሁ:: ቤትም ይሁን ትምህርት ቤት ሳልታጠብ ተመግቤ አላውቅም:: ከትምህርት ቤት ስመለስም ዩኒፎርሜን አውልቄ ንጹህ የቤት ውስጥ ልብስ እለብሳለሁ:: ማታ ወደ መኝታዬ ስሄድም ንጹህ የሌሊት ልብስ እለብሳለሁ:: ይህንን እውቀት ያገኘሁት በሳይንስ ትምህርት ነው:: እናትና አባቴም ስለግል ንጽህና አጠባበቅ ሁልጊዜ ያስተምሩኛል::

እንግዲህ ልጆች የግል ንጽህናን አለመጠበቅ ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች በማጋለጥ ጤናችሁን ሊያሳጣችሁ፣ ከትምህርት ገበታችሁ ሊያስተጓጉል ከመቻሉም በላይ በራስ የመተማመን ብቃትን ስለሚያሳጣ በየትኛውም ጊዜና ቦታ ሁልጊዜ የግል ንጽህናን የመጠበቅ ጉዳይ የሁልጊዜ ተግባራችሁ ሊሆን ይገባል እንላለን::

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ዞሮ ዞሮ እግሩን የማይታጠብ**

**መልስ፦** ሐ. ዶላ

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ስታበላ እንደ እናት ፤ ስትቆጣ እንደ እንጀራ እናት**

ሀ. እናት

ለ. ድመት

ሐ. ንብ

መ. ሰራተኛ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ::**

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ**

# የወንዝ ዳርቻ ልማቱ ፍሬ

- በካይ ተብለው ከተለዩት የግለሰብ መኖሪያ ቤት እና የመንግስት ተቋማት መካከል ከ11 ሺህ 670 በላይ በሚሆኑት ብክለትን የማስቆም ስራ እንደተሰራ ተጠቁሟል



ፎቶ ከፋይል
የአዲስ አበባን ገፅታ ከቀየሩ የወንዝ ዳርቻ ልማቶች መካከል አንዱ

**በለይላ መሀመድ**

እምየ ኢትዮጵያ ይመርልሽ ሰብሉ
አውድማው ጎተራው ይሁንልሽ ሙሉ
በቸር ውሎ ይደር ጋራ ሸንተረርሽ
ወንዛ ወንዝሽ ሁሉ
ያደግኩበት ወንዝሽ የተራጨሁበት
ክፉም አልሰማ ክፉም አልይበት
ሰላም ደምኖ ሰላም ይዝነብበት

ኢትዮጵያ የብዙ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት ስለመሆኗ ከላይ የተጠቀሰውን ጨምሮ በተለያየ ጊዜ ተዚሞላታል፤ ተነግሮላታል፡፡ ሀገሪቷ ከመልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ ጀምሮ የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት ናት፡፡ ምቹ የአየር ጸባይ፣ ብርቅየ የዱር እንስሳትና አዕዋፍት፣ ዓመቱን ሙሉ የማይነጥፉ ወንዞች... ባለቤት ናት፡፡ ይሁን እንጂ ከከተሞች መስፋፋት፣ ከሕዝብ መጨመር ጋር በተያያዘ ተጠብቀው በቆዩና ለአካባቢያዊ ጥበቃ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ባላቸው የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ጉዳት እየደረሰ ይገኛል። ለጉዳት ሰለባ ከሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶች መካከል ወንዞች ይጠቀሳሉ። ደኖች እየተመነጠሩ ወደመኖሪያነት መቀየራቸውና የደኖች መመናመን ለወንዞች መድረቅ ተጽዕኖው ከፍተኛ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የከተሞች መስፋፋትም ወንዞች በበካይ ኬሚካሎች እንዲበከሉ የራሱን አሉታዊ አስተወጽኦ እያደረገ ነው፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገሪቱ በተለይም በአዲስ አበባ የወንዝ እና የወንዝ ዳርቻ ልማት የከተማ ገጽታ ማሻሻያ አካል ሆኗል፡፡ በዚህም መነሻነት የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን ተፈጻሚ እያደረገው ባለው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀጽ 95 መሰረት “የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017” በሚል ስያሜ አውጥቶ ወደ ተግባር ከተገባ ውሎ አድሯል፡፡ በዛሬው ዕትማችን የደንቡ ተፈፃሚነት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ በተመለከተ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ብክለት ጥናት ከፍተኛ ባለሙያ አቶ ሙላቱ ወሰኑን በማነጋገር እንዲሁም ከደንቡ መሰረታዊ ነጥቦችን በማካተት በሚከተለው መልኩ ዳስሰነዋል፡፡

ከፍተኛ ባለሙያው አቶ ሙላቱ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት፤ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባርን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 545/2016 አንቀጽ 2 (2) ላይ ከአካባቢ ጥበቃ ጋር የተያያዙ መሰረታዊ ነጥቦች ተቀምጠዋል። በደንቡ ላይ እንደተመላከተው፤ “የአካባቢ ጥበቃ ማለት፡- የሰው ልጅን ጨምሮ የማንኛውም አካል ሕይወት እና እድገት የሚወስኑ የመሬት፣ የውሃ፣ የአየር፣ የአየር ንብረት ሥርዓት፣ ሌሎች የአካባቢ ሀብቶች፣ ክስተቶችና ሁኔታዎችን በመጠበቅ የአሁኑን ትውልድ ፍላጎት የማርካቱ ሂደት የመጪውን ትውልድ ዕድል ሳያሰናክል እንዲሟላ ማስቻል ነው” በማለት ይበይነዋል፡፡ ከዚህ ትርጉም መረዳት እንደሚቻለው የአሁኑ ትውልድ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም የመጪውን ትውልድ በተፈጥሮ ሀብት የመጠቀም መብት በማይጎዳ መልኩ ሊሆን ይገባል። ይህንን ቁልፍ እሳቤ መተግበር የሚረዱ የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎች በተግባር ላይ ውለዋል። ከእነዚህ መካከል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2016 አንዱ ነው፡፡

## የደንቡ አስፈላጊነት

በ2017 በጀት ዓመት ወጥቶ ወደ ሥራ የገባው የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017 የወጣበት ዓላማና አስፈላጊነት በተመለከተ የባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ የአካባቢ ብክለት ጥናት ከፍተኛ ባለሙያ አቶ ሙላቱ፤ “የአካባቢ ብክለትን በመከላከል ከተማውን የተፈጥሮ ሚዛኑን ለመጠበቅ፣ ጽዱ፣ አረንጓዴና ምቹ ለማድረግ ነው። ለዚህም በከተማው ውስጥ የሚገኙ ወንዞችና ዳርቻዎቻቸው ንጹሕና ጤናማ አካባቢ እንዲሆኑ ማድረግ ቅድሚያ የተሰጠው ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በመዲናዋ በሚገኙ ወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች ልማት ላይ የመጣው ለውጥ ህያው ምስክር ነው” ብለዋል፡፡

የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017 ለአዲስ አበባ ከተማ ምን ያክል አስፈላጊ እንደሆነ የመጣውን ተጨባጭ ለውጥ መመልከት ይበቃል፡፡ የወንዝ እና የወንዝ ዳርቻ ልማት፣ የኮሪደር ልማት ውጤት የዚህን ደንብ ወሳኝነት በገሃድ ያሳያሉ፡፡ ምክንያቱም ደንቡ መሰረታዊ ጉዳዮችን መሬት እንዲነኩ ያስቻለ በመሆኑ ነው። በደንቡ የተካተቱ አንዳንድ ቃላት እና ሀረጋት ለዚህ ሁነኛ አስረጂ ናቸው። ደንቡ፤ “የወንዝ ዳርቻ” የሚለውን፤ ለወንዝ ዳርቻ መጠበቂያ ቢያንስ ከወንዙ ጠርዝ ግራና ቀኝ ዝቅተኛው 30 ሜትር ሆኖ እንደአካባቢው ሁኔታ አስተዳደሩ በሚወስነው መሠረት ስፋቱ ሊጨምር የሚችል ሲሆን ለማንኛውም ዓይነት ግንባታ ወይም አገልግሎት እንዲውል የማይፈቀድ ቦታ እና በወንዙ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ሥፍራን እንደሚያጠቃልል ይደነግጋል። “የወንዝና ወንዝ ዳርቻ ኮሪደር ልማት” የሚለውን ሀረግ ደግሞ፤ ከወንዙ ተፋሰስ መነሻ ጀምሮ የሥነ-ምህዳር ጥበቃ፣ አረንጓዴ ልማት፣ መዝናኛ ቦታዎችን እና ተያያዥ አገልግሎቶችን ከወንዙ ኩታ-ገጠም የሆኑ አካባቢዎች ማልማት ሆኖ ወሰኑና የመሬት አጠቃቀሙ በጥናት የሚወሰን መሆኑን ደንግጓል።

በተጨማሪ፤ “የወንዝ ብክለት” የከተማዋ ወንዞች ከማንኛውም ግለሰብ፤ መኖሪያ ቤት፣ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በሚመነጩ የተለያዩ በካይ ነገሮች ምክንያት የወንዝን ተፈጥሯዊ ባህሪ መቀየርን የሚያመለክት መሆኑን ያብራራል፡፡ “የወንዝ ሥርዓተ-ምህዳር” ማለት ደግሞ፤ በወንዝና በወንዝ ዳርቻ ያሉ ማናቸውም ሕይወት ያላቸው ነገሮች ከራሳቸው ጋርም ሆነ ሕይወት ከሌላቸው ነገሮች እንዲሁም ከአካባቢያቸው ጋር የሚያደርጉትን ያልተቋረጠ ተፈጥሮአዊ መስተጋብር የሚያሳይ ሥርዓት እንደሆነ አስፍሯል፡፡

የወንዝና ወንዝ ዳርቻ ልማት በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ህጎችን ዓላማ ያሳካል፡፡ የህገ-ወጥ ቆሻሻ አወጋገድን ያስቀራል፡፡ እንዲሁም ለዘላቂ የመሬት አጠቃቀም ድጋፍ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። የወንዝና ወንዝ ዳርቻ ልማት ለዘላቂ የመሬት አጠቃቀም ድጋፍ ሲባል የወንዝ ዳር ኮሪደር ልማት የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል የሚያስችሉ እፅዋትን ለመትከል፣ የግንባታ መዋቅሮችን ለማበጀት እና የውሃ ፍሰትን ለማስተካከል ይረዳል። ይህ በረጅም ጊዜ ለአፈርና ውሃ ሀብት ዘላቂ አስተዳደር ወሳኝ ነው። የአፈር መሸርሸርን መቆጣጠር የመሬት ጥራት እንዲጠበቅ ከማድረጉም በላይ፣ የወንዙን የውሃ ፍሰት መደበኛነት እንዲያገኝ ያግዛል፡፡ ይህም የመሬት ይዞታ ህጎችን በተዘዋዋሪ ይደግፋል።

የኮሪደር ልማቱን የበለጠ ዘላቂነት ባለው መልኩ ተንከባክቦ ለመያዝ ፋይዳው የጎላ ከመሆኑም ባሻገር በከተማ “ስማርት ከባቢ” ለመፍጠር የወንዙን ንጽህና መጠበቅና ለተለያዩ ስርዓተ ምህዳራዊ አገልግሎት እንዲውል ማድረግ ፋይዳው የጎላ ነው።

በተለያየ መንገድ ወንዙን ለሚበክሉ አካላት ማለትም የአምራች ተቋማት፣ የአገልግሎት ሰጭ፣ የግለሰብ መኖሪያ ቤት እና የመንግስት ተቋማት በድምሩ ለ17 ሺህ 516 የልየታ (Mapping) ስራ ተከናውኗል፡፡ እነዚህ የተለዩት ግለሰቦች እና የተለያዩ ተቋማት ችግሩን የሚያስወግዱበትን መንገድ እንዲያበጁ እየተደረገ ነው።

የወንዙን የብክለት ደረጃ በጥናትና በላቦራቶሪ በመለየት ረገድም ሰፊ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ የወንዙን የብክለት ምንጮች ለመቀነስ በከተማው የፍሳሽ ማጣሪያ በመገንባት፣ ከወንዝ የተገናኘ ቱቦ በመቁረጥ፣ የፍሳሽ ሴፕቲክ ታንክ (ፍሳሽ እስከሚወገድ ድረስ በጊዜያዊነት የሚጠራቀምበት) በማዘጋጀት እና በቋሚና በሳይንሳዊ የማስመጠጫ ስርዓት በማከናወን ከየካቲት 24 ቀን 2017 ዓ.ም እስከ መስከረም 30 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ በካይ ተብለው ልየታ ከተደረገባቸው 17 ሺህ 516 የግለሰብ መኖሪያ ቤት እና የመንግስት ተቋማት መካከል ከ11 ሺህ 670 በላይ በሚሆኑት ብክለትን የማስቆም ስራ ተሰርቷል።

**ከአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ**

# የአካዳሚው አበርክቶ ሲቃኝ

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**

አዲስ አበባ የበርካታ ዓለም አቀፍ ተቋማት፣ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ እና የአፍሪካ ህብረት ዋና መስሪያ ቤት መቀመጫ ናት፤ ለበርካታ ዓመታት ይህን ክብሯን በማይመጥን ልክ የተለያዩ ችግሮች ተጋርጠውባት ቆይታለች፤ ይህን ችግር ለመፍታት ቀላል የማይባሉ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በተለይ በኮሪደር እና በወንዝ ዳርቻ ልማት እንዲሁም በግዙፍ ሜጋ ፕሮጀክቶች ግንባታ ሳቢያ ስሟንና ክብሯን ወደሚመጥን ደረጃ ከፍ እንድትል ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በተለያዩ ጥናቶችና ምርምሮች የተደገፉ ስራዎችን መስራትም ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡

ከተማዋን በዘላቂ እድገት ለመምራት በተለያዩ ዘርፎች ጥናቶች እና ምርምሮችን ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ጥርጥር የለውም። የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ የተቋቋመበት ዋና ዓላማም ይኸው ነው፡፡ ይህ ተቋም በዋናነት የስልጠና፣ የማማከር፣ የጥናትና ምርምር አገልግሎቶችን ይሰጣል።

በአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ የእቅድ ዝግጅትና ግምገማ ዳይሬክተር አቶ ሽመልስ ጉራራ እንደሚሉት አካዳሚው ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የከተማዋን ችግሮች በዋናነት የሚፈቱ በስራ እድል ፈጠራ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ እና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ በርካታ የስልጠና፣ የምርምርና የማማከር አገልግሎቶች እየሰጠ ይገኛል፡፡

በተለይ የከተማ አስተዳደሩ ሪፎርም ካደረገበት ጊዜ ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 84/2016 በተለየ መልኩ ተልዕኮ ተሰጥቶታል ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ዋና ተልዕኮውም በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ የሚገኙ በመንግስትና በግል ተቋማት ለሚሰሩ አመራሮችና ባለሙያዎች በጥናትና ምርምር ግኝት ላይ የተመሰረተ ስልጠና በመስጠት ማማከርና የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት የመፈፀም አቅማቸውን ማሳደግ ነው ብለዋል፡፡

ይህን መነሻ በማድረግም በ2017 ዓ.ም በተለይ ከስልጠና፣ ከማማከር፣ ከጥናትና ምርምር ስራዎች አንፃር በርካታ ተግባራት መከናወናቸውን ነው የተናገሩት፡፡ በአካዳሚው ስልጠና ላይ ጥናትና ምርምር ላይ የከተማ አመራር ልማት ዳይሬክቶሬት፣ የስራ አመራር ልማት ዳይሬክቶሬት፣ የጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት እና የማማከርና የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የተሰኙ አራት ዘርፎች አሉ፡፡

የስልጠና መርሃ ግብሮችም ለተሿሚ አመራሮች፣ ለዳይሬክተሮች፣ ለቡድን መሪዎች እና ባለሙያዎች ተብለው የሚከናወኑ ሲሆን፣ በዚህ መሰረት ባለፈው በጀት ዓመት በተለይ የከተማ አመራር ልማት ዳይሬክቶሬት በከተማዋ ላሉ 5 ሺህ ተሿሚ አመራሮች ስልጠና ለመስጠት አቅዶ 5 ሺህ 689 አሰልጥኗል፤ በተመሳሳይ 5 ሺህ 834 ዳይሬክተሮች እና ቡድን መሪዎችን ለማሰልጠን አቅዶ 5 ሺህ 343 ማሰልጠን ችሏል፡፡ በተጨማሪም 2 ሺህ 708 ባለሙያዎችን ለማሰልጠን አቅዶ 2 ሺህ 683 በማሰልጠን በአጠቃላይ በሁለቱ ዳይሬክቶሬቶች 13 ሺህ 542 ለሚጠጉ ከተሿሚ አመራር እስከ ባለሙያ ላሉ ስልጠና ለመስጠት አቅዶ 13 ሺህ 715 በማሰልጠን የእቅዱን 101 በመቶ ማከናወን ችሏል፡፡

ከጥናትና ምርምር ጋር ተያይዞም 14 ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ለመስራት ታቅዶ 16 የተከናወነበት፣ ከማማከር አገልግሎት ጋርም ተያይዞ 6 የማማከር አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 6ቱም የተከናወነበትና 4 የማህበረሰብ አገልግሎት ለመስጠት በታቀደው መሰረት እቅዱን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡

ከዚህ አንፃር የ2017 የአካዳሚውን እቅድ አፈፃፀም ስንመለከት የተሻለ አፈፃፀም የተመዘገበበት ወቅት መሆኑን ነው ያመላከቱት፡፡ በዘንድሮው 2018 በጀት ዓመትም አካዳሚው እቅድ ሲያዘጋጅ በዋናነት መነሻ ያደረገው የአካዳሚው የ5 ዓመት፣ የ10 ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ እና የ2017 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀምን መነሻ በማድረግ ነው፡፡

እቅዱን ሲያዘጋጅም በየደረጃው ያሉ ስትራቴጂክ አመራሮች እስከ ጠቅላላ ሰራተኞች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ጋር መግባባት ተፈጥሮ ነው ወደ ስራ የተገባው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም በዋናነት አካዳሚው የከተማ አስተዳደሩ የሰጠው ተልዕኮ ስልጠና፣ ጥናትና ምርምር ማማከርና ከማህበረሰብ አገልግሎት ጋር ተያይዞ በመሆኑ የ2018 እቅድም በዓበይት ተግባራት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

ከዚህ አኳያ በያዝነው በጀት ዓመት በከተማ አስተዳደሩ ከወረዳ እስከ ማዕከል ላሉ 6 ሺህ 500 ተሿሚ አመራሮች ስልጠና ለመስጠት የታቀደ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ሩብ ዓመት 1 ሺህ 184 ለሚሆኑት ለመስጠት ታቅዶ 500 ለሚሆኑ ተሿሚ አመራሮች መስጠት ተችሏል፡፡ ይህም የእቅዱን 42 ነጥብ 3 በመቶ መከናወኑን ያመላክታል፡፡

ከስራ አመራር ዳይሬክቶሬት አኳያም በበጀት ዓመቱ 8 ሺህ 500 ለሚሆኑ ከቡድን መሪ እስከ ዳይሬክተር ያሉ ባለሙያዎች በተለያየ ዘርፍ ስልጠና ለመስጠት የታቀደ ሲሆን፣ በዚህ ዘርፍም በሩብ ዓመቱ ወደ 850 ለሚሆኑት ለመስጠት ታቅዶ 623 የሚሆኑት ስልጠናውን ማግኘታቸው ነው የተገለፀው፡፡

ከባለሙያ ጋር ተያይዞም በበጀት ዓመቱ 3 ሺህ 386 ባለሙያ ለማሰልጠን ታቅዷል፡፡ ከዚህ ውስጥ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 338 ባለሙያዎችን ለማሰልጠን የታቀደ ሲሆን፣ ከዚህም 558 የሚሆኑትን በማሰልጠን ከእቅድ በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡

አቶ ሽመልስ ለስልጠና ግብዓት የሚሆኑ ነገሮችን ከማቅረብ ጋር ተያይዞም ሰፊ ስራዎች እንደሚሰሩ ሳይጠቅሱ አላለፉም፡፡ ለስልጠና አስፈላጊ የሆኑ ሞጁሎችን ከማዘጋጀት አኳያ በተለይ በያዝነው በጀት ዓመት ለተሿሚ አመራሮች አራት ሞጁሎችን ለማዘጋጀት እቅድ ከመያዙም ሌላ በስራ አመራር ዳይሬክቶሬትም አምስት ሞጁሎችን ለማዘጋጀት መታቀዱን ነው ያመላከቱት።፡

የማሰልጠኛ ሞጁሎች በሚዘጋጁበት ጊዜ መነሻ የሚደረገው በከተማ ደረጃ ያለው የስልጠና ፍላጎት ነው። ለማዘጋጀት የታቀዱት ሞጁሎች መነሻም ከዚህ የሚመነጭ ሲሆን፣ ሁለቱ የስራ ክፍሎችም ከዚህ አንፃር ዝግጅት አድርገው ወደ ስራ መግባታቸውን ተናግረዋል፡፡

ከጥናትና ምርምር ጋር ተያይዞ በበጀት ዓመቱ ወደ 15 እንዲሁም በተያዘው ሩብ ዓመት 4 የጥናት እና ምርምር ስራዎችን ለመስራት ታቅዶ፣ ስድስት ማከናወን ተችሏል፡፡ ይህን ለማከናወን ቅድሚያ ፕሮፖዛል ተሰርቶ በሚመለከተው አካል ከፀደቀ በኋላ ወደ ዋናው ጥናት የሚገባ ይሆናል፡፡ በሩብ ዓመቱ የጥናትና ምርምር ውጤት ለማጠናቀቅ በእቅድ ደረጃ ባይያዝም 3 የጥናትና ምርምር ስራዎች ተጠናቅቀው ለግምገማ ዝግጁ ሆነዋል፡፡

እነዚህን የጥናትና ምርምር ስራዎች በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ያሉ በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ለማፀደቅም ኮንፍረንስ እንደሚዘጋጅ ያመላከቱት ዳይሬክተሩ፣ በአንደኛው ሩብ ዓመት 2 ኮንፈረንሶችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 3 በማዘጋጀት ከእቅድ በላይ ማከናወን መቻሉን ጠቁመዋል፡፡ ከማማከርና ከማህበረሰብ አገልግሎት ጋር ተያይዞ የሚሰጡ ስልጠናዎችም ተቋማት ላይ ትኩረት የሚደረግ ነው፡፡ ለአብነትም ተቋማት ምን አይነት የማማከር አገልግሎት ይፈልጋሉ? የሚለውን መሰረት አድርጎ የሚኬድበት ይሆናል፡፡

ይህንንም በተመለከተ ለተቋማት ደብዳቤ ቢፃፍም በወቅቱ ምላሽ የሚሰጡ ብዙ አይደሉም፡፡ ሆኖም ግን በበጀት ዓመቱ 7 የማማከር አገልግሎት ለመስጠት እቅድ ተይዞ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 2 የማማከር ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ለማዘጋጀት ታቅዶ ፍላጎቱ በወቅቱ መምጣት ባለመቻሉ ማከናወን አልተቻለም፡፡

አካዳሚው ይህን ችግር ለመፍታት ከዚህ በፊት ያደረጋቸውን የጥናትና ምርምር ስራዎችን መነሻ በማድረግ የጥናትና ምርምሩ ምክረ ሃሳብ ምንድን ነው? የሚለውን ታሳቢ አድርጎ የማማከር አገልግሎት ለመስጠት ዝግጅት እያደረገ ነው፡፡ ከማህበረሰብ አገልግሎት ጋር ተያይዞም ማህበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት ማህበረሰቡ ጋር ድረስ በመሄድ እየተሰራ ነው፡፡ ለአብነትም በ2017 በጀት ዓመት 'ለነገዋ' የሴቶች ተሃድሶ እና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል፣ የአዲስ አበባ አረጋዊያን ማህበር እንዲሁም ተማሪዎች ጋር ተያይዞ ብዙ የማህበረሰብ አገልግሎቶች ተሰርተዋል፡፡

የከተማ አስተዳደሩ የዝግጅት ምዕራፍን የተግባር ምዕራፍ መሆን አለበት ባለው መሰረት ሳምንቱን ሙሉ ቀንና ሌሊት (7/24) ስራዎች እየተከናወኑ ነው፡፡ እንደ አካዳሚው ከዚህ በፊት ባልነበረ የዝግጅት ምዕራፉ ወደ ተግባር የተገባበት ሁኔታ መኖሩን ጠቅሰው፣ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ከተያዘው እቅድ አኳያ ችግሮች ቢኖሩም አፈፃፀሙ የተሻለ መሆኑ የተገመገመበት ነው፡፡

በግምገማው በመሰረታዊነት ከተለዩ ችግሮችም ዋነኛው የሰው ኃይል ችግር ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፣ የኢንስቲትዩቱ መዋቅር የሚፈቅደው የሰው ኃይል 325 ሲሆን፣ መያዝ አለበት የሚባለው ደግሞ 250 ነው፡፡ አካዳሚው በእነዚህ መደቦች ላይ እስከ አሁን ያለው የሰው ኃይል ቁጥር ግን 124 ብቻ ነው፡፡ ይህም ካለው አጠቃላይ የሰው ኃይል ድርሻ 34 ነጥብ 5 በመቶ ብቻ መሟላቱን ያሳያል፡፡

በተለይ ዓላማ አስፈፃሚ በሚባሉት ስልጠና፣ ምርምር፣ ማማከርና ማህበረሰብ አገልግሎት የስራ ክፍሎች ጋር ተያይዞ ባለሙያ የሆኑ ሰዎችን ይፈልጋል ከዚህ አኳያ ያሉ ክፍተቶችን ለመሸፈን አካዳሚው ከፐብሊክ ሰርቪስ ቢሮ ጋር በመነጋገር ባለሙያዎችን የማሟላት ስራ እየሰራ በመሆኑ ከ22 በመቶ ወደ 34 በመቶ ማደግ ችሏል፡፡

በተጨማሪም ተቋሙ ተባባሪ አካላትን በማስታወቂያ በመጋበዝ ስራዎችን እየሰራ እንደሆነ አመልክተው በዚህም በተለይ የአሰልጣኞች ተባባሪ አካላትን እና የምርምር ተባባሪ አካላትን የመመልመል ስራዎችን እንደሚሰራ ተናግረዋል። ቅንጅታዊ አሰራሮችን ተግባራዊ በማድረግ ችግሮችን የመፍታት አካሄድም ሌላው አሰራር ሲሆን ከዚህም ጋር ተያይዞ በቡድን የመስራት ባህል እየጎለበተ መጥቷል፡፡

ሌላው እንደተቋም የተለየው መሰረታዊ ችግር ተቋሙ የሚገኘው ለአስፓልት ቅርብ በሆነ የኪራይ ህንፃ ላይ እንደመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የማሰልጠኛ ቦታ እጦት አለበት፡፡ የማሰልጠኛ ክፍሎች ማነስና መጥበብ ብቻ ሳይሆን መንገድ ዳር በመሆኑ የድምፅ ብክለት ያሉት አምስት የማሰልጠኛ ክፍሎችም የድምፅ መከላከያ ስላልተገጠመላቸው ከአንዱ ማሰልጠኛ ክፍል የሚወጣው ድምፅ ሌላውን የሚረብሽ መሆኑ በራሱ ችግር የሚፈጥር ነው፡፡

ተቋሙ ጎሮ አካባቢ የራሱን ህንፃ እያስገነባ መሆኑ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ያስችላል፡፡ የህንፃው ግንባታ እስኪጠናቀቅም ችግሩን ለመፍታት ከሌሎች ተቋማት ጋር ትስስር ተፈጥሯል። በበጀት ዓመቱ 10 ተቋማት የተለዩ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ ከዘጠኙ ጋር አካዳሚው ተፈራርሞ ወደ ስራ ገብቷል። ከእነዚህም የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢኒስቲትዩት እንዲሁም የአፍሪካ ልህቀት ማዕከል ተጠቃሾች ናቸው፡፡



ፎቶ ከፋይል
በአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ የእቅድ ዝግጅትና ግምገማ ዳይሬክተር አቶ ሽመልስ ጉራራ

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ማርን በከተማ

• በየካ ክፍለ ከተማ 221 አካላት በንብ ማነብ ስራ የተሰማሩ ሲሆኑ፣ በተያዘው ወር መጨረሻ 27 ሺህ 525 ኪሎ ግራም ምርት እንደሚሰበሰብ ተገልጿል

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**



ፎቶ- ከገፀ ድር

በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 በተለምዶ ጂፋራ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ የሚገኝ የንብ ማነቢያ ስፍራ በከፊል

ከተሞች የኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሞተር ናቸው፤ በርሚንግሃም ዩኒቨርሲቲ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2023 ያወጣው ጥናታዊ ፅሑፍም ይህንኑ ያመላክታል። ተቋሙ ከተሞች በማህበራዊ፣ በኮኖሚያዊ እና በከባቢያዊ ስርዓቶቻችን ውስጥ ምን ድርሻ አላቸው? (What are Cities and What Role do They Play in our Social, Economic, and Environmental Systems?) በሚል ርዕስ ያስነበበው ጥናታዊ ፅሑፍ እንደሚያትተው ከሆነ ከተሞች የንግድ፣ የሥራ ዕድል እና የቴክኖሎጂ ፈጠራ ማዕከል በመሆን ለሀገራት ሁለንተናዊ ዕድገት ከፍተኛ ሚና ያበረክታሉ፡፡ በዓለም ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ውስጥም የ85 በመቶ ድርሻ አላቸው።

በአብዛኛው ተዝናኖታዊ ቅኝት ያላቸው የስራ እንቅስቃሴዎች እንደሚዘወተርባቸው የሚገመተው ከተሞች ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ግብርናንም እንደ አንድ የኢኮኖሚ ምንጭ መጠቀም ጀምረዋል። አይግሮው ኒውስ፣ ‘ምግባቸውን የሚያመርቱ ከተሞች’ በሚል ርዕስ ያዘጋጀው ፅሑፍ፣ የከተማ ግብርና በውስን ቦታ ላይ ትርጉም ባለው ደረጃ የከተማ ነዋሪዎችን አኗኗር እያሻሻለ እንደሚገኝ አስነብቧል፡፡ እንደ ሲንጋፖር፣ ዲትሮይት፣ አትላንታ፣ ሚያሚ፣ ለንደን፣ ኒው ዮርክ እና ፓሪስ ያሉ ከተሞች በአነስተኛ ቦታዎች ላይ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የተለያዩ የግብርና ስራዎችን በመስራት ነዋሪዎቻቸውን ተጠቃሚ አድርገዋል፡፡ በዶሮ፣ በወተት፣ በዓሣ፣ በአትክልትና በፍራፍሬ ምርቶች እንዲሁም በተፈጥሮ ሀብት ልማት ረገድ ቀላል የማይባል ውጤት አግኝተዋል፡፡ ምርቶቹን ለቤት ውስጥ ፍጆታ ከማዋል ባሻገር አቀነባብረው ለሽያጭ በማዋልም ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ፈጥረዋል፡፡

ሲንጋፖር ከተማ 10 በመቶ ያህሉን የምግብ ፍጆታዋን በከተማ ግብርና ለመሸፈን በቅታለች፡፡ ከተማዋ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2030 ከሚያስፈልጋት የግብርና ምርት ውስጥ 30 በመቶውን በራሷ ለመሸፈን በመስራት ላይም ትገኛለች። ለዚህም ‘30 በ30 ጎል’ የተሰኘ መርሃ ግብ ነድፋ እየሰራች ሲሆን፣ በከተማ ግብርና ዙሪያ ፈጠራን ለማበረታታት 60 ቢሊዮን ዶላር መመደቧን የዓለም ኢኮኖሚክ ፎረም “የከተማ ግብርና እና የምግብ ዋስትና በሲንጋፖር” (Urban Farms And Food Security In Singapore) በሚል ርዕስ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2021 ያወጣው ፅሑፍ ያትታል፡፡

አዲስ አበባ ውስጥም የከተማ ግብርና ስራ በስፋት የሚተገበር ሆኗል፤ በተለይ በሰብልና በጓሮ አትክልት፣ ንብ በማነብ፣ በዓሳ ምርት፣ በዶሮና እንቁላል እንዲሁም በወተትና በወተት ተዋፅኦ ምርቶች ላይ በርካቶች ተሰማርተዋል። በከተማዋ የከተማ ግበርና ልምምድ እለት ከእለት እያደገ መጥቶ ነዋሪዎችም በጓሯቸው በበረንዳቸው፣ በቤቶቻቸው ጣርያና ግድግዳ አትክልቶችን በማብቀል ብቻ ሳይሆን ዘመናዊ የንብ ቀፎዎችን በመጠቀም የማር ምርት ተጠቃሚ መሆን ጀምረዋል፡፡

የሌማት ትሩፋት መርሃ ግብር እንደሀገር ተግባራዊ ከሆነ ወዲህ የከተማ ግብርና በከተሞች በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ መነቃቃትና ለውጥ ማሳየቱ የሚካድ አይደለም። የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 በተለምዶ አንቆርጫ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ንብ በማነብ ስራ የተሰማሩት አቶ መስፍን ሰይፉ አንድ አብነት ናቸው። ቀደም ሲል በባህላዊ ቀፎ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ንብ የማነብ ስራን የጀመሩት ተጠቃሚው በተጠናከረ መንገድ መስራት የጀመሩት ግን ከሦስት ዓመት ወዲህ እንደሆነ ይናገራሉ። አሁን ከ20 በላይ ዘመናዊ ቀፎ ያላቸው አቶ መስፍን በማር ምርት ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ንብ ማነብ ገጠር፣ ከተማ፣ ሰፊና ጠባብ ቦታ ሳይባል በየትኛውም ሁኔታና አካባቢ እንደሚቻልና ጠንክሮ ከተሰራ ከቤተሰብ ፍጆታ ባለፈ በኢኮኖሚ ረገድም ተጠቃሚ ያደርጋል የሚሉት አቶ መስፍን፣ ባለፈው ዓመት ግንቦት ወር ብቻ ወደ 200 ሺህ ብር የሚጠጋ ገቢ ከማር ምርት ማግኘታቸውን ተናግረዋል፡ ፡ በዚህ ዓመትም ከአምናው በተሻለ መልኩ ማር ለመሰብሰብ አቅደዋል፡፡

ንብ የማነብን ስራ ቀደም ሲል በባህላዊ መንገድ ከቤተሰባቸው ጋር ሲያከናውኑ እንደነበርና አሁን ላይ ግን በግላቸው ስለዘርፉ ለማወቅና አስፋፍተው ለመስራት ባደረጉት ጥረት ከ20 በላይ ዘመናዊ ቀፎችን አዘጋጅተው ከእርሳቸው በተጨማሪ ለሁለት ሰዎች የስራ እድል በመፍጠር ስራቸውን እየሰሩ ይገኛሉ። በንብ ማነብ የተሻለ የማር ምርት ተጠቃሚ ለመሆን ለንቦቹ በቂ ውሃና ምግብ ከማቅረብ በተጨማሪ አስፈላጊ

> **ንብ ማነብ ገጠር፣ ከተማ፣ ሰፊና ጠባብ ቦታ ሳይባል በየትኛውም ሁኔታና አካባቢ እንደሚቻልና ጠንክሮ ከተሰራ ከቤተሰብ ፍጆታ ባለፈ በኢኮኖሚ ረገድም ተጠቃሚ ያደርጋል**

የሆኑ ነገሮችን ማሟላት ከምንም በላይ ደግሞ የራስ ተነሳሽነትን ይጠይቃልም ብለዋል፡፡

እንደ አቶ መስፍን ገለፃ፣ በተለይ አሁን በምንገኝበት በዚህ ወቅት አበቦች የሚፈኩበት እንደመሆኑ ለስራው አመቺና የተሻለ የማር ምርት የሚገኝበት ነው፡፡ ንቦች አብዛኛውን ጊዜ የተለያዩ ዛፎች አበባዎችን በመቅሰም እራሳቸውን ይመግባሉ። በራሳቸው ከሚመገቡት በተጨማሪ የተለያየ አበባዎችን በመትከል መመገብና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ውጤታማ ያደርጋል፡፡

ቀፎ ብቻ በማስቀመጥ በዓመት የማር ምርት ተጠቃሚ መሆን እንደማይቻል አቶ መስፍን ገልጸው፣ የንብ መንጋውን ጠብቆ መያዝና አስፈላጊውን እንክብካቤ በማድረግ በዓመት ጥራትና ብዛት ያለው የማር ምርት ማግኘት ይቻላል ባይ ናቸው። ከሚደረግላቸው እንክብካቤና ጥንቃቄ መካከልም ተባይ እንዳይገባባቸው፣ በሸረሪት ድር እንዳይጎዱ እንዲሁም የተለያየ በሽታ እንዳያጠቃቸው በተቻለ መጠን የቀፎዎችን ንጽህና እና የአካባቢያቸውን ጽዳት መጠበቅ ዋንኞቹ ናቸው፡፡

ለንብ ማነብ የተለየ ስሜት እና ፍቅር እንዳላቸው የጠቆሙት አቶ መስፍን፣ በዓመት ሶስት ጊዜ ጥቅምት፣ ታህሳስ እና ግንቦት ላይ የማር ምርት እንደሚሰበሰብ ተናግረዋል፡፡ በከተማዋ በንብ እርባታ ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻል ገልፀው፣ በአካባቢያቸው ላሉ ለሌሎች ነዋሪዎች ልምዳቸውን በማካፈል ወደ ዘርፉ እንዲቀላቀሉ ምክንያት መሆናቸውንም ነግረውናል፡፡

በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 አርሶ አደርና የከተማ ግብርና ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ያደታ ዋቁማ፣ አካባቢው በደን የተሸፈነ በመሆኑ ለንብ ማነብ ስራ አመቺ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ንብ ማነብ ተፈጥሯዊ አካባቢን እንደሚፈልግ ገልጸው፣ ወረዳው ለዚህ ስራ ተስማሚ አካባቢ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በወረዳው በተለይም ጂፋራ ተብሎ በሚጠራው አከባቢ የሚኖሩ 40 አርሶ አደሮች ከሌሎች የከተማ ግብርና ስራዎች ጎን ለጎን ንብ በማነብ ዘርፍ መሰማራታቸውን ጠቅሰው፣ በ70 ዘመናዊ ቀፎዎች የንብ ማነብ ስራን እያከናወኑ ያሉት አንድ አርሶ አደር ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች የስራ እድል መፍጠራቸው በማር ምርት ረገድ ትልቅ ተስፋ መኖሩን የሚያሳይ ነው ብለዋል፡፡

ከነዚህ በተጨማሪም በወንዝ ዳርቻዎች አካባቢ ከ20 መቶ የሚበልጥ ዘመናዊ ቀፎ በመጠቀም ንብ በማነብ የተሰማሩ 15 አባላት ያሏቸው ሶስት ማህበራትና ግለሰቦች መኖራቸውን አውስተው፣ ከእነዚህም ከባለፈው በጀት ዓመት የተሻለ የማር ምርት እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

ጂፋራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የውሃ ዕጥረት ችግር እንደሚያጋጥማቸው ገልፀው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ችግሩን ለማቃለል ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ዘርፉን የግብዓት እና የሙያ ድጋፍ በመስጠት ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ በትኩረት እየተሰራ መሆኑንም በመግለፅ፡፡

ክፍለ ከተማው ከሌሎች አንፃር ሲታይ ንብ ለማነብ ምቹና የተሻለ መሆኑን ገልጸው፣ በዘርፉ የተሰማሩ አካላት በብዛትና በጥራት ማምረት እንዲችሉ፣ ምርታቸውን እንዴት ማሳዳግ እንደሚችሉ፣ አንድ ቀፎ ወስደው ሁለትና ከዚያ በላይ የማድረግ ወይም የማባዛት ስልጠና እንዲሁም በባለሙያ የተደገፈ የቴክኒክ ስልጠና እንደሚሰጣቸው ጠቁመዋል፡፡

በየካ ክፍለ ከተማ 221 አካላት በግልና በማህበር ተደራጅተው በንብ ማነብ ስራ የተሰማሩ ሲሆኑ፣ አሁን ባለው መረጃ እንደ ክፍለ ከተማ 1 ሺህ 101 ቀፎዎች እንደሚገኙ ገልጸዋል፤ ከእነዚህም 943 ዘመናዊ ቀፎዎች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ባህላዊ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

በዓመት ከእያንዳንዱ የማር ቀፎ 25 ኪሎ ግራም ማር ማግኘት ይቻላል፡፡ እንደ የካ ክፍለ ከተማም በተያዘው ወር መጨረሻ አካባቢ 27 ሺህ 525 ኪሎ ግራም ማር ይሰበሰባል ተብሎ ይጠበቃል፤ ይህም ንብ የማነብ ስራ በትኩረት ከተሰራበት ተጠቃሚ የሚያደርግ የስራ ዘርፍ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

## “በ2018 ዓ.ም ... ከገጽ 5 የዞረ

ማህበራትና ምሁራን ጋር ውይይቶችን አድርጓል፡፡ በቅርቡም ኮሚሽኑ በክልሉ ከሚገኙ የሚዲያ ባለሙያዎች ጋር የውይይት መድረክ አድርጓል፡፡

“ይህን እያደረግን ያለነው ‘ነገ ወይም ወዲያውኑ ሀገራዊ ምክክሩን ወደእናንተ እናምጣው፤ አጀንዳ እንሰብሰብ’ በሚል ሁኔታ ውስጥ አይደለም፡፡ በአሁኑ ሰዓት በትግራይ እያደረግን ያለነው መተማመንን የመፍጠር (Confidence Building) ተግባር ነው፡፡ በክልሉ በነበረው ጦርነት ክልሉ እና የፌዴራል መንግስት አይገናኙም ነበር፡፡” ያሉት መስፍን (ፕሮፌሰር) ባለድርሻ አካላት የኮሚሽኑን ዓላማውንና ተአማኒነቱን እንዲረዱ፣ ሀገራዊ ምክክር የትግራይንም ሆነ የሌሎች ኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄዎች መፍታት የሚያስችል ሂደት መሆኑን እንዲገነዘቡ የማድረግ ስራ መሰራቱን አንስተዋል፡፡ በትግራይ ክልል የምክክሩን ሂደት ለመጀመር መተማመን በመፍጠር ረገድ የተሻለ ስራ ተሰርቷል፡፡ ወደ ምክክር ሂደቱ ከተገባ በክልሉ ያሉ 94 ወረዳዎችን በሁለት ሳምንት ውስጥ መድረስ እንደሚቻል አክለዋል፡፡

ሌላው ኮሚሽኑ በቀሪ ጊዜያት የሚያከናውነው ተግባር በተለያየ ምክንያት በምክክር ሂደቱ እየተሳተፉ የማይገኙ አካላት ወደ ምክክሩ እንዲገቡና የአጀንዳ ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ ረገድ አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምክክሩ እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡ ኮሚሽነር ሙሉጌታ እንደሚሉት፣ ጥቂት የፖለቲካ ፓርቲዎች በኮሚሽኑ ተአማኒነት፣ የሀገራዊ ምክክሩ ሂደትና ውጤታማነት ላይ ጥያቄ በማንሳት በሂደቱ እየተሳተፉ አይደለም። እነዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምክክሩ ሂደት እንዲሳተፉ ኮሚሽኑ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በሚገኙበት መድረክ እና በተናጠል ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በኮሚሽኑ ገለልተኝነት ላይ ጥርጣሬ ያላቸው ወገኖችም ቀረብ ብለው ጥያቄ እንዲያቀርቡ፤ የተሳታፊዎች ልየታና የአጀንዳ አሰባሰብ ላይም ክፍተት አለ ካሉ በሂደቱ በመሳተፍ መገምገም እንደሚችሉ ኮሚሽኑ አሳውቋል፡፡ ከዚህ ውጪ ኮሚሽኑ “ተፅዕኖ ይደረግበታል” የሚል ግምት በመያዝ ወደኋላ መቅረት ተገቢነት የለውም፡፡ “ገዥውም ሆነ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ወደ ስልጣን መምጣት የሚችሉት ሀገር ሲኖር ብቻ ነው፡፡ የሰላም እጦት፤ እርስ በእርስ መተማመን በጠፋበት፤ በየትኛውም ሁኔታ ስልጣን ላይ የሚወጣ አካል ሀገርን መምራት አይችልም፡፡” ሲሉ ኮሚሽነር ሙሉጌታ አንስተዋል፡፡

በምክክሩ ሂደቱ የታጠቁ ሀይሎች እንዲሳተፉ በተደጋጋሚ ጥሪ ሲተላለፍ መቆየቱን ኮሚሽነር ሙሉጌታ ያነሳሉ። ኮሚሽኑ እነዚህ ሀይሎች ወደ ግጭትና ጦርነት ያስገባቸው ምክንያት ምን እንደሆነ እንዲያነሱና ምክክር ተደርጎባቸው እና ለሚመለከታቸው አካላት ቀርበው ይፈቱ ዘንድ የአጀንዳ ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ ከመንግስትና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት (የሰላም ኮሚቴዎች) ጋር በመነጋገር ሲሰራ ቆይቷል፡፡ የሚቀርቡ የተሳተፉ ጥሪዎች የማይፈፀሙ ሳይሆኑ የሚተገበሩ፤ በታሪክ ማህደር ውስጥ የሚመዘገቡ፣ ነገ የኢትዮጵያ ህዝብ አይቶ ፍርድ የሚሰጥበት በመሆኑ እነዚህ ሀይሎች አጀንዳቸውን ቢያቀርቡ ለሀገራዊ ችግሮች መፍትሔ የሚመጣበት ሁኔታ እንደሚኖር ኮሚሽነር ሙሉጌታ አስገንዝበዋል፡፡

“ኮሚሽኑ የአጀንዳ ሀሳብ እንዲቀርብ ለሁሉም በሩን ክፍት አድርጎ እየሰራ ነው፡፡ ስልጣን ላይ ያለ አካል ወይም በምርጫ ወደ ስልጣን ለመምጣት የሚፈልግ አካል በሀገር ጉዳይ ላይ ለመነጋገር በማኩረፍ ወደኋላ መቅረት የለበትም፡፡ አንዳንድ አካላት በምክክሩ ሂደትና የሚቀርቡ መፍትሔዎች ትግበራ ላይ ጥርጣሬ ኖሯቸው ወደኋላ ሊሉ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ስለሀገር በሚሰራ ስራ ላይ ‘አትሳተፉም’ ቢባል እንኳን ታግሎ መሳተፍ ያስፈልጋል፡፡ በምክክሩ ሂደት አለመሳተፍ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል፡፡” ሲሉ በሂደቱ እየተሳተፉ የማይገኙ አካላት እንዲሳተፉ ኮሚሽነር ሙሉጌታ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

እስከአሁን ባለው ሂደት ኮሚሽኑ ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎችና ከዳያስፖራዎች እንዲሁም በጥናት የአጀንዳ ሀሳቦችን በማሰባሰብ እያጠናቀቀ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ምክክር የሚደረግባቸው እጅግ መሰረታዊና ሀገራዊ ያለ መግባባት ምክንያት የሆኑ አጀንዳዎችን የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ምክር ቤት ከሚደግፏቸው አካላት ጋር በመሆን ይለያሉ፡፡ ከዚህ አኳያ አጀንዳ ለመቅረፅ ባለሙያዎች የተሰበሰቡትን አጀንዳዎች እየተመለከቱ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡

አጀንዳው ተቀርፆ ለህዝብ ይፋ ከተደረገ በኋላ የሚቀጥለው ተግባር ሀገራዊ የምክክር ጉባኤ ማካሄድ ሲሆን በጉባኤው ከ4 ሺህ 500 በላይ ተወካዮች ይሳተፋሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች፣ ሊሂቃንና ፖለቲከኞችን ያካተተ እንደሚሆን ከኮሚሽኑ ያገኘነው መረጃ ያሳያል፡፡

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ሰብሳቢ መስፍን አርዓያ (ፕሮፌሰር) በቅርቡ ለመገናኛ ብዙሃን እንደገለፁት፣ ኮሚሽኑ ስራውን እንዲያጠናቅቅ በአዋጅ የተፈቀደለት ጊዜ ከአምስት ወይም ስድስት ወር የማይበልጥ ሲሆን በቀረው ጊዜ ሀገራዊ የምክክር ጉባኤው ተካሂዶ በምክክሩ የሚቀርቡ ምክረ ሀሳቦችን በማቅረብ ስራውን አጠናቅቆ ይጨርሳል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ ምክንያቱም ምክክር ይጀመራል እንጂ አያልቅም፤ በአንዳንድ አጀንዳዎች ላይ መግባባት ለመድረስ ወራትን ብቻም ሳይሆን ዓመታትን ሊወስድ ይችላል፡፡ የሀገረ መንግስት ግንባታው ላይ የሚታዩ የበዙ ችግሮችን በትክክልና በምክንያት በሚገባ በመወያየት ወደ አንድ ደረጃ ለማድረስ ጊዜ ሊወስድ ይችላል፡፡

ሌላኛው አስተያየት ሰጪ በአዲስ አበባ የቦሌ አራብሣ ነዋሪ አቶ ታደሰ ጸጋዬ ለዝግጅት ክፍላችን እንደተናገሩት፣ እንደሀገር ልዩነቶችንና አለመግባባቶችን ከውይይት ይልቅ ሀይልን በመጠቀም ለመፍታት ስንሞክር ቆይተናል፡፡ ይህ አካሄድ የምንፈልገውን ቀጣይነት ያለው ሰላም፣ መረጋጋትና ልማት አላመጣልንም። የማያግባቡ ችግሮችን ለመፍታት ሀገራዊ ምክክሩ መልካም አጋጣሚ መሆኑን ያነሱት አቶ ታደሰ፣ ሁላችንም የአንድ ሀገር ወንድማማችና እህትማማች ህዝቦች እንደመሆናችን ልዩነቶቻችንን በምክክር ለመፍታት መስራት እንዳለብን ተናግረዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ስድስት ኪሎ አካባቢ ያገኘናቸው በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ጎለልቻ ወረዳ ነዋሪ የሆኑት ሼህ መሀመድ ሼህ ሀቢብ ኢትዮጵያ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ጨምሮ የተለያዩ ልማቶችን በማጠናቀቅ በለውጥ ጎዳና ውስጥ ትገኛለች፡፡ በልማቱ እየተገኘ ያለው ውጤት አስደሳች ነው፡፡ ይህንን ድል ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት በማምጣት ለመድገም አለመግባባቶችን ወደ ጠረጴዛ በማምጣት በውይይትና በምክክር መፍታትን መለማመድ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ ሼህ መሀመድ፤ በኦሮሚያ ክልል አዳማ ከተማ በተከናወነው የአጀንዳ ሀሳብ ማሰባሰቢያ መድረክ የሚኖሩበትን ወረዳ ወክለው መሳተፋቸውንና በሀገራችን ለሰላም እጦት ምክንያት የሆኑ ችግሮችን ማንሳታቸውንም አክለዋል፡፡

ኮሚሽነር ሙሉጌታ እንደተናገሩት ሀገራዊ ምክክሩ ውጤታማ እንዲሆን መንግስትና ህዝብ ከፍተኛ ድጋፍ እያደረጉ ነው፡፡ ኮሚሽኑ በተንቀሳቀሰባቸው አካባቢዎች ሁሉ ህዝቡ ያለምንም ገደብ በነፃነት ሀሳቡን በመስጠት እየተሳተፈ ይገኛል፡፡ ግጭት በነበረባቸው አካባቢዎች ሳይቀር የፀጥታ ስጋት ሳይበግረው በሂደቱ ከፍተኛ ተሳትፎ አድርጓል፤ ለዚህም ምስጋና ይገባዋል፡፡ ህዝቡ የሂደቱ ባለቤት እንደመሆኑ በቀጣይም የምክክሩን ሁኔታ በመከታተል፣ የሚጎድለውን በማመላከትና እንዲሟላ በማድረግ ድጋፉን አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። መገናኛ ብዙሃንም ስለሂደቱ መረጃ ለህብረተሰቡ በመስጠትና በማስተማር፣ ክፍተቶችን በመጠቆምና መፍትሔዎችን በማመላከት የሚያደርጉትን ተሳትፎ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ አቅርበዋል።

## የሀገራዊ ምክክር ምክረ ሀሳቦችና አተገባበር

- የሀገራዊ ምክክር ምክረ ሀሳቦችና አተገባበር ላይ የሀገራዊ ምክክር ውጤቶችን በአግባቡ መረዳት፣ የተገኙ ውጤቶች ተግባራዊ የሚሆኑበትን ዝርዝር ዕቅድ ማዘጋጀትና ስልቶችን መንደፍ እንዲሁም ለትግበራው ምዕራፍ ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮችን በመለየት አተገባበሩን መከታተል ትኩረት የሚሰጣቸው አንኳር ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነዚህም
- ሀገራዊ ምክክር ትልቅ የሽግግር ፍኖተ ካርታ አካል ሆኖ በኢኮኖሚ፣ በመዋቅራዊ፣ በፖለቲካ እና በፍትህ ማሻሻያ ሂደቶች መታጀብ አለበት። ሀገራዊ ምክክሮች በራሳቸው ፍጻሜ ሳይሆኑ የተቀናጀና አሳታፊ የለውጥ ሂደት ጅምር መሆናቸው መታወቅ አለበት።
- የምክክር ሂደት የመጨረሻው ምዕራፍ በምክክሩ መግባባት የተደረሰባቸውን ምክረ-ሀሳቦች ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ እንደ ምክረ-ሀሳቦቹ ባህርይ ተግባራዊነታቸው በአጭር፣ በመካከለኛ ወይም በረዥም ጊዜ ተፈጻሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የሚተገበሩበት ፍጥነትና ስፋት እንደ ምክረ-ሀሳቦቹ ባህርይ ብቻም ሳይሆን ለተግባራዊነቱ ባለድርሻ የሆኑ አካላት እንደሚያደርጉት ጥረትና እንደሚኖራቸው ቁርጠኝነትም ሊለያይ ይችላል፡፡
- የሚደረገው ጥረትና የሚኖረው ቁርጠኝነት ከፍተኛ ሲሆን፡ በአጠረ ጊዜና በምልዓት ተግባራዊ የመሆን ዕድሉ ሰፊ ነው፡፡ የተግባራዊነቱን ስፋትና ፍጥነትን የመወሰን አቅም ያላቸው በርካታ ጉዳዮች ቢኖሩም በዋናነት ግን መግባባት ላይ የተደረሰበት መንገድ፣ አሳታፊነቱ፣ አካታችነቱና ግልጸኝነቱ ወሳኝ መነሻዎች ናቸው፡፡
- በሌላ አነጋገር ሂደቱ ቅቡልነት ያለውና መሠረተ ሰፊ የሆነ መግባባት ላይ ከተደረሰ አተገባበሩ ሰፊና ፈጣን የመሆን ዕድሉ ከፍተኛ ነው፡፡ የአስፈጻሚውን አካል የቤት ስራም ቀላል ያደርገዋል፡፡ በሌላ መልኩ አስፈጻሚው አካል የሕዝቡን ፍላጎት ተረድቶና አክብሮ ተግባራዊ እንዲያደርግ ተጽእኖ የመፍጠርን ጉልበት ያገኛል፡ ፡ ይህም በመሆኑ ነው በሀገራዊ ምክክር ላይ ከውጤቱ ይልቅ ሂደቱ ጤናማ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት መደረግ ያለበት፡፡
- ሀገራዊ ምክክሮች ከመመካከር ሂደት ባሻገር በተግባር ላይ በሚውሉ መርሆች ላይ ተመስርተው የሚመቻቹ ሂደቶች ናቸው። የትግበራው ምዕራፍ የተለያዩ ተግዳሮቶችን እና ዕድሎችን ይዞ የሚመጣ ነው፡፡ በምክክር ሂደት ላይ መሳተፍ በራሱ የሚያመጣቸው ማህበራዊ በጎ ልምምዶች እንደተጠበቁ ሆነው መግባባት ላይ የተደረሰባቸው ሀሳቦች ወደ ተግባር ተለውጠው መታየት ይኖርባቸዋል፡፡
- በወቅቱ ከተፈጠሩና መሰረታዊ ልዩነቶች ናቸው ተብለው በምክክር ሂደት መግባባት ከተደረሳባቸው አጀንዳዎች በተጨማሪ ቀሪ ጉዳዮችን ወይም በቀጣይ ሊፈጠሩ የሚችሉ አዳዲስ የልዩነት ሀሳቦችን ቀጣይነት ባለው የምክክር ሂደት ለመፍታት እንዲቻል ለቀደመው ሀገራዊ ምክክር ተገቢውን ዋጋና ክብር በመስጠት የተደረሰባቸው መግባባቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ መደረግ አለበት፡፡

**የመረጃ ምንጭ - የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ገጸ ድር**

## ብቃት ...

ከገጽ 6 የዞረ

በዚህ ሂደት ውስጥ ያለፉት በሙሉ በአሁኑ ወቅት ከድርጅቱ ጋር በቋሚ ሠራተኛነት ለመቀጠል ውል በመፈራረም ላይ እንገኛለን” በማለት ያስረዳሉ፡፡

ወይዘሮ መርያ ሀሰን እና ወጣት ስብሀት ግርማ ዘናጭ ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ማምረቻ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የሥራ ልምምድ እያደረጉ ከሚገኙ ወጣቶች መካከል ናቸው፡፡ ባነጋገርናቸው ጊዜ እንዳስረዱት ከሆነ፤ የሥራ ላይ ልምምዱ በሥራ አጥነት ያሳለፏቸውን አሰልቺ እና ተስፋ አስቆራጭ ጊዜያት በማስረሳት ራስን በመቻል እና ለታላቅ ስኬት በመዘጋጀት ሃሳብ ውስጥ እንዲገኙ እንዳስቻላቸው አልሸሸጉም፡፡

ከ10ኛ ክፍል ትምህርቷን አቋርጣ እና ትዳር መስርታ ትኖር እንደነበር የገለጸችው ወይዘሮ መርያ ሀሰን፣ ይህንን ዕድል በማግኘቷ ተጠቃሚ እንደሆነች፤ “የሥራ ላይ ልምምድ ከመጀመሬ በፊት ሕጻን ልጄን በመንከባከብና በማሳደግ በቤት ውስጥ ባሉ ስራዎች ብቻ አተኩር ነበር፡፡ ወደዚህ ድርጅት ከገባሁ በኋላ ከጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ጋር በተያያዘ መሰረታዊ ሙያዎችን አግኝቻለሁ። ከነባር ሠራተኞች ጋር ተወዳዳሪ የሚያደርግ ብቃትን ይዣለሁ፡፡ በዚህም በድርጅቱ በቋሚ ሠራተኛነት ለመቀጠር ችያለሁ፡፡ ለእኔና ለቤተሰቤ የሚሆን ገቢ ፈጥሬያለሁ፡፡ በቀጣይ የተሻለ ደረጃ መድረስ እንደምችል ተስፋ ሰንቄያለሁ” በማለት ታስረዳለች፡፡

“ትምህርቴን ከ10ኛ ክፍል በማቆም፤ ያለ ሥራ ተቀምጬ ነበር፡፡ ይህ መሆኑ ብዙ ጫና ፈጥሮብኝ ነበር፡፡ ከቤተሰብ ጋር እስከመጋጨት ደርሼም አውቃለሁ። የሥራ ላይ ልምምድ ከጀመርኩ በኋላ በራስ መተማመኔ አድጓል፡፡ ከሰው ጥገኝነት ወጥቻለሁ፡፡ ለቤተሰቦቼ ዳቦ ገዝቼ መግባት ችያለሁ፡፡ ወደፊት ከራሴ አልፌ ከጓደኞቼ ጋር በመደራጀት ለሌሎች የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችል ድርጅት ለማቋቋም አልማለው፡፡ ለእኛ የተመቻቸው ዕድል ለሌሎችም ወጣቶች መመቻቸት አለበት” የሚለውን ሃሳብ ያጋራን ደግሞ ወጣት ስብሀት ግርማ ነው።

ብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 25 ዓመት፣ የትምህርት ደረጃቸው 12ኛ እና ከዚያ በታች፣ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆኑ ወጣቶች በተለያዩ የሙያ መስኮች ሰልጥነው ወደ ሥራ የሚገቡበትን ዕድልን ማመቻቸት ዓላማ አድርጎ ሲተገበር የቆየ መሆኑን ያነሱት ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራና ክህሎት ቢሮ የሥራ ስምሪት አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ ሰብሀዲን ሱልጣን፤ በመርሃ ግብሩ ከሚሳተፉት ወጣቶች መካከል 60 ከመቶው ድርሻ የሴቶች መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በተመሳሳይ የሥራ ላይ ልምምድ እንዲያደረግባቸው የሚመረጡ ድርጅቶች የተቀመጠላቸውን መስፈርት ያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡ እነዚህ ድርጅቶች፡

- ሕጋዊ ፍቃድ ያላቸው፣ ቢያንስ 6 ቋሚ ሠራተኞችን የቀጠሩ፣ 4 የሥራ ላይ ተለማማጆችን የሚቀበሉ መሆን አለባቸው፡፡ የተሰማሩባቸው ዘርፎችም፡
- ማኑፋክቸሪንግ፣ አገልግሎት፣ የከተማ ግብርና መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ የሥራ ከባቢ ምቹ ማድረግ አለባቸው፡፡

እንደ አቶ ሰብሀዲን ገለጻ፤ መርሃ ግብሩ በኢትዮጵያ መንግስት እና በዓለም ባንክ ትብብር የሚከናወን ነው፡፡ በ2014 ዓ.ም. የተጀመረው መርሃ ግብሩ በአምስት ዓመቱ ውስጥ 49 ሺህ ወጣቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ በማቀድ የተገበረ ሲሆን፤ የአምስት ዓመታት ቆይታውን ነገ (ጥቅምት 30/2018 ዓ.ም.) ያጠናቅቃል፡፡ ነገ በሚጠናቀቀው የመጨረሻው ምዕራፍ የሥራ ላይ ልምምድ ላይ 15 ሺህ ወጣቶች ተሳትፈዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 9 ሺህ 615ቱ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ወጣቶች ሲሆኑ፤ ቀሪዎቹ ከውጭ ሀገር የተመለሱ ኢትዮጵያዊያን ናቸው፡፡

ከ9 ሺህ 615ቱ የመጨረሻ ዙር የሥራ ላይ ልምምድ ተሳታፊ የአዲስ አበባ ነዋሪ ወጣቶች መካከል 8 ሺህ 884 ያህሉ ነገ ልምምዳቸውን ያጠናንቃሉ ሲሉም አክለዋል፡፡

በብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር የሚሳተፉ ወጣቶች የሚያገኟቸውን ጥቅሞች በተመለከተ አቶ ሰብሀዲን በሰጡት ማብራሪያ እንደጠቆሙት፤ ወጣቶች ወደ ሥራ ላይ ልምምድ ከመግባታቸው አስቀድሞ ፍላጎታቸው ይጠየቃል፣ የድርጅቶች/ተቋማት የሥራ ባህል ይነገራቸዋል፡፡ በዚህ ላይ በግልፅ በመወያየት አሠሪ ድርጅቶች እና የሥራ ላይ ተለማማጅ ወጣቶች እንዲወስኑ ይደረጋል፡፡ ከዚያም ወደ ሥራ ላይ ልምምዱ ይገባሉ፡፡ የስድስት ወር የሥራ ላይ ልምምዳቸውን እንደጨረሱ የቆዩባቸው ድርጅቶች የስድስት ወራት የሥራ ልምድ ይጽፉላቸዋል፡፡ የምስክር ወረቀትም ይሰጣቸዋል፡፡ በቆይታቸው ለትራንስፖርት ወጪ የሚሆን በቀን 133 ብር ወይም በወር 2 ሺህ 926 ብር ይከፈላቸዋል፡፡ ልጅ ያላቸው ወጣት ሴቶች በተለየ ሁኔታ ለልጆቻቸው እንክብካቤ የሚሆን ተጨማሪ 945 ብር በየወሩ ይሰጣቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለሦስት ወራት ለሥራ ማፈላለጊያ የሚሆን የትራንስፖርት ወጪ በቀን 133 ብር ታስቦ ይከፈላቸዋል፡፡

ዳይሬክተሩ አክለው እንዳብራሩት፤ ወጣቶቹ ከሙያዊ ስልጠና በተጨማሪ ለ12 ቀናት የሚቆይ የሕይወት ክህሎት ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡ በየሦስት ወሩ ደግሞ መሰረታዊ የኮምፒውዩተር ስልጠና ይወስዳሉ፡፡ በየወሩ የአቻ ለአቻ ውይይት ያደርጋሉ፡፡ ስለ ተቋማት የሥራ ባህል፣ ስለ ሥራ ላይ ችግርና መፍትሄ የመሳሰሉትን እንዲገነዘቡ ይደረጋል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ያለፉ ሙያዊ ክህሎት ያላቸው፣ የሥራ ልምድ ያካበቱ፣ ዕውቅና ካላቸው ድርጅቶች የሥራ ልምድ የተሰጣቸው ዜጎችን ደግሞ ገበያው ይፈልጋቸዋል፡፡ በዚህ መልኩ ካለፉ ወጣቶች አብዛኞቹ ቋሚ የሥራ ዕድል አግኝተዋል፡፡ የራሳቸውን ሥራ በግልና በቡድን በመሥራት ላይ የሚገኙም አሉ። በቅጥር እየሠሩ ያሉት ወጣቶች ከ5 ሺህ እስከ 34 ሺህ ብር ድረስ ወርሃዊ ገቢ ማግኘት ችለዋል፡፡

በአምስት ዓመቱ ብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድን ጥቅል ውጤት በጥናት ለማረጋገጥና በገለልተኛ አካል ለማስጠናት ዕቅድ መያዙን የጠቆሙት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራና ክህሎት ቢሮ የሥራ ስምሪት አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ ሰብሀዲን ሱልጣን፤ ይህም ሆኖ አብዛኛው የሥራ ላይ ልምምድ ያደረገ ወጣት ሥራ ላይ መሆኑን በሥራና ክህሎት ቢሮ መዋቅር የተሰበሰበ መረጃ እንደሚያመላክት ጠቅሰዋል፡፡

በመንግስት እና በዓለም ባንክ የጋራ ትብብር ሲፈፀም የቆየውን ብቃት የወጣቶች የሥራ ላይ ልምምድ መርሃ ግብር ተሞክሮ በመውሰድ በራስ አቅም ተፈፃሚ ለማድረግ ዕቅድ መያዙን አቶ ሰብሀዲን ተናግረዋል፡፡ እንደሳቸው ገለፃ፤ መርሃ ግብሩ ሕዳር አጋማሽ 2018 ዓ.ም. በይፋ ይጀመራል፡፡ ከሁሉም ክፍለ ከተሞች በተመረጡ 20 ወረዳዎች ላይ ለሚጀመረው መርሃ ግብር እንደ ከተማ አስተዳደር 145 ሚሊዮን ብር የተመደበ ሲሆን፤ 3 ሺህ ወጣቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ወጣቶቹ የሥራ ላይ ልምምዳቸውን የሚያደርጉባቸው 1 ሺህ 100 ድርጅቶችም ተለይተዋል፡፡

## ብቁ ...

ከገጽ 8 የዞረ

አንስተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት እንደአገር እየተሠራ ያለው ይህንን ታሳቢ ያደረገ መሆኑንም ገልጸው፤ የቱሪዝም መዳረሻ ልማት እና የሰው ሀብት ልማት ተያይዘው የሚሄዱ ተግባራት ናቸው ብለዋል፡፡

በቱሪዝም ዘርፍ በዕውቀትና ክህሎት የዳበሩ ሙያተኞችን በማፍራት ረገድ እንደአገር ከዓመት ዓመት መሻሻሎች እየታዩ ስለመሆናቸው ያነጋገርናቸው ምሁራን ይመሰክራሉ፡፡ መንግስት ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ፤ ለቱሪዝሙ ዘርፍ ራሱን የቻለ የትምህርትና ስልጠና መርሃግብር(ካሪኩለም) ተዘጋጅቶለታል። አሁን ላይ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት(ዩኒቨርሲቲ እና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛዎች) በተለያዩ የሙያ ዘርፎች

የረጅም እና የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች በስፋት እና በብዛት በመስጠት ላይ ናቸው፡፡

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የቱሪዝም እና የሆቴል ማኔጅመንት ትምህርት ክፍል ኃላፊ እና መምህር የሆኑት ደመቀ ክብሩ የሚሠሩበትን ዩኒቨርሲቲ ተሞክሮ በማንሳት የቱሪዝምን ዘርፍ በሙያተኞች ለመደገፍ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እየሠሩት ስላለው ተግባር አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ እሳቸው እንዳብራሩት፤ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንደአገር ሦስት መሰረታዊ ተልዕኮዎችን ይዘው ነው የሚሠሩት፡፡ እነዚህም ተልዕኮዎች ማስተማር፣ ምርምር፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ናቸው፡፡ የጅማ ዩኒቨርሲቲም እነዚህን ተልዕኮዎች ለማሳካት እየሠራ ይገኛል፡፡ በቱሪዝም ዘርፍ ላይ ያተኮሩ የሙያ መስኮችን ከ2007 የትምህርት ዘመን ጀምሮ በመጀመሪያ ድግሪ እና በሁለተኛ ድግሪ ለሰልጣኞች እየሰጠ ሙያተኞችን እያፈራ ይገኛል፡፡ ወደፊትም ይህንን አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በዘርፉ ለአገራቸው የሚጠቅሙ ሙያተኞችን ማፍራታችንን እንቀጥላለን፡፡ ተማሪዎች ሲመረቁ የተለያዩ የጥናት እና ምርምር ሥራዎችን ይሠራሉ። ደረጃቸውን የጠበቁ የጥናትና ምርምር ጽሑፎች እንዲታተሙና ለአንባቢያን እንዲደርሱ ይደረጋል፡፡ በመምህራንም ጥናቶች እና ፕሮጀክቶች ይሠራሉ፡፡ Development team training program DTTP የተሰኘ መርሃግብር እንደ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይህ መርሃግብር የሁለተኛ ድግሪ ተማሪዎች በመጨረሻ የመመረቂያ ዓመታቸው ላይ በቡድን በመሆን የአካባቢውን ማህበረሰብ ችግር በመለየት በጥናት ላይ የተመሰረተ ተግባራዊ መፍትሄ የሚሰጡበት አማራጭ ነው፡፡ በተቻለ አቅም ለሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ላሉ ሙያተኞች በዩኒቨርሲቲው ስልጠና ይሰጣል፡፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ከሆቴሎች ጋር በቅርበት እና በቅንጅት ይሠራል፡፡

“በቱሪዝም ዘርፍ በሙያው የሰለጠነ የሰው ኃይል ከማፍራት አንፃር በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚታየው ዋና ጉድለት ‘ነፍስ እና ስጋ ያለው ስልጠና’ የመስጠት ክፍተት ነው” የሚሉት በጅማ ዩኒቨርሲቲ የቱሪዝም እና የሆቴል ማኔጅመንት መምህሩ ደመቀ፤ “ተማሪዎች ወይም ሙያተኞች በንድፈ ሃሳብ የወሰዱትን ትምህርትና ስልጠና ወደ ነባራዊው ዓለም ወስዶ የመተግበር ክፍተት አለባቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ አብዛኞቹ ትምህርትና ስልጠናዎች በንድፈ ሃሳብ ላይ ብቻ ያተኮሩ መሆናቸው ነው። ስለዚህ ስልጠናዎች የንድፈ ሃሳብ እና የተግባር ቅንጅት ያለባቸው መሆን ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ የሆቴልና ቱሪዝም ስልጠና የሚሰጡ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በማሰልጠኛዎቻቸው ውስጥ በንድፈ ሃሳብ የተማሩትን የሚተገብሩበት ሆቴሎች ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር ጅምሮች አሉ፡፡ የንድፈ ሃሳብና የተግባር መቀናጀት ስልጠናው ነፍስና ስጋው የተጣመረ ይሆናል፡፡ ስልጠናዎች በንድፈሃሳብም በተግባርም የተደገፉ መሆን አለባቸው፡፡ ሙያተኛው ስላሉን ሃብቶች፣ ስለሚሠራው ሥራ በቂ ዕውትና ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል፡፡ የቱሪዝም ማሰልጠኛ ተቋማት የተደራጁና የበቁ መሆን አለባቸው። ንድፈ ሃሳብን ከተግባር ጋር አዋህደው የሚተገብሩ ሊሆኑ ይገባል። አሰልጣኞችም ራሳቸውን በዕውቀት እና በክህሎት እያሳደጉ ሊሄዱ ይገባል” በማለት አብራርተዋል፡፡

እንደ አገር በቱሪዝም ዘርፍ የተካኑ ባለሙያዎችን ማፍራት እና ወደ ሥራ ማሰማራት ይዟቸው የሚመጣ በርካታ ጥቅሞች እንዳሉ ጥናቶች ያስረዳሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ በጎርጎሮሳዊያን የዘመን ቀመር 2024 “Tourism for Development in Africa: Unlocking Inclusive Growth” በሚል ርዕስ የዓለም ባንክ ባወጣው ሰነድ ላይ እንዳስነበበው የቱሪዝሙን ዘርፍ በሙያው በተካኑና በበቁ ሙያተኞች መምራትና ማንቀሳቀስ ለአገራት ብዙ ጠቀሜታን ያስገኛል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ፡- የኢኮኖሚ እድገት እና የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የውጭ ምንዛሪ ገቢ፣ ለአገር የገጽታ ግንባታ እና ኢንቨስትመንት መሻሻል የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ከፍ ያለ መሆኑ ይጠቀሳል፡፡

ቱሪዝም በሰዎች ላይ ያተኮረ ኢንዱስትሪ ነው፡፡ ስኬቱም ውድቀቱም በሰዎች ችሎታ፣ ሙያዊ ብቃት እና ፈጠራ ላይ የተመሰረተ ነው። የቱሪዝም ዘርፉ ከያዘው ፀጋ ስፋትና ጥልቀት እንዲሁም ከኢኮኖሚ መሰረታዊ ምሰሶዎች እንደአንዱ አድርገው ለወሰዱ ለኢትዮጵያ እና ለሌሎች ታዳጊ አገሮች የሰለጠነ የሰው ኃይል መገንባት ቅንጦት ሳይሆን የግድ ነው። ስለሆነም በዕውቀትና በክህሎት የላቁ፣ በመጠንም በቂ የሆኑ የቱሪዝም ባለሙያዎችን ለማፍራት የትምህርትና ስልጠና ተቋማትን ማጠናከር፣ኢንዱስትሪ-የአካዳሚክ ትብብርን መፍጠር የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፣ በሥራ ላይ ላሉ ሙያተኞች ተከታታይነት ያለው የሥራ ላይ ስልጠና መስጠት፣ ለኢንዱስትሪው የፖሊሲ እና ተቋማዊ ድጋፍ ማድረግ ይገባል፡፡

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 ህብረት ስራ ጽ/ቤት ተደራጅቶ የሚገኘው የአቃቂ ብረታ ብረት ፋብሪካ ሰራተኞች ኃላ/የተ/ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበር በአደረገው ጠቅላላ ጉባኤ ማህበሩ እንዲፈርስ በሙሉ ድምፅ የተወሰነ በመሆኑ ይህን የማህበሩን መፍረስ የሚቃወም ወይም ይገባኛል የሚል አካል ካለ በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 92 መሰረት ጋዜጣው አየር ላይ ከዋለ ጀምሮ በ2 ወራት ውስጥ ተቃውሞውን በአካል በመቅረብ ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ህብረት ስራ ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 505 እዲያቀርብ እየገለጽን በዚህ ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ንብረት የመጠየቅ መብት የሌለው መሆኑን በመግለጽ ጥሪ እናስተላልፋለን፡፡

**በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ ጽ/ቤት**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 05 በካርታ ቁጥር 33811/9209/01 በሴሪ ቁጥር 021141 ወ/ሮ ኤልሣቤጥ የማነብርሀን ጣሰው ተሰጥቷቸው የነበረው ማህደር የጠፋ ስለሆነ በማናቸውም ምክንያት ይገኖዋለሁ የሚል በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ድረስ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይገኖዋለሁ የሚል ከሌለ ሌላ ማህደር እንደሚከፈትላቸው እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በቢኒያም ግርማ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ቦሌ9/49/4/1/28739/00 የሴሪ ቁጥር 053747 የተሰጠበት ቀን 23/03/07 ዓ.ም የቦታው ስፋት በሰነድ 265 ካ.ሜ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲፃፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 09 የሆነው መኖሪያ ቤት በቢኒያም ግርማ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ቦሌ9/49/4/1/28739/00 የሴሪ ቁጥር 053747 የተሰጠበት ቀን 23/03/07 ዓ.ም የቦታው ስፋት በሰነድ 265 ካ.ሜ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ኦርጂናል የጠፋ ስለሆነ ይዞታ ቤቱን በዕዳ ይገኖዋለሁ፤ አስይገኖዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጠ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ካርታውን የምናዘጋጅ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረው አመልካች በአራዳ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 13 ቀበሌ 11 በአዲሱ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር 340 በእነ ሳህለማርያም መታፈሪያ ስም የወጣው ቁጥሩ 12080 በቀን 22/1974 ዓ.ም ዋና ካርታ አመልካቾችን ከቤታቸው ጋር የተቃጠለ በመሆኑ በምትኩ ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው 26/02/2018 ጠይቋል፡፡

በመሆኑም የጠየቁትን አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይገኖዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ አራዳ ክ/ከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን ካልቀረቡ ግን የጠየቁትን አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 11 የካርታ ቁጥር 147/1295/001025 በሴሪ ቁጥር 062840 ጽጌ አበበ ኃይሉ ስም ያለውን ይዞታ አስመልክቶ ይህን ይዞታ በእዳ እገዳ ይገኖዋለሁ የሚል ተቋምም ሆነ ግለሰብ ወይም ይዞታው ላይ የይገባኛል ጥያቄ ያለው አካል ካለ በ30 (ሰላሳ) ቀን ውስጥ በየካ ክ/ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት ቀርቦ ካርታቸውን እንዲያስረክበን እንጠይቃለን።

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

የሹም ዘውዱ አስፋው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 10 መለያ ቁጥር AA000061000550216O214 የሆነው ሰርተፍኬት በፅፈት ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው የቤት ባለቤትነት ካርታ ሴሪ ቁጥር 248963 ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግንቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት /ካርታ እንደምሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ቅ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 01 ክልል ውስጥ በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070105275 በሴሪ ቁጥር 017974 በህሊና ሀይሉ ገብሬ ስም የተመዘገበ ይዞታና ቤት ባለቤትነት መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

የአዲስ በትረማርያም ሉቃስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የካርታ ቁጥር ሊዝ/ዕጣ/1453/92 የሴሪ ቁጥር 019366 ተመዝግቦ የነበረው ኦርጅናል የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በተለያየ ምክንያት ይገኖዋለሁ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ20 ቀናት ውስጥ በቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ለይዞታ ማህደር አስተዳደር ክፍል ካልቀረበ በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ጣዕመ ገብሬ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000060502022 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገኖዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

እነ ወ/ሮ መቅደስ ከበደ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 9 የቤት ቁጥር 319 ካርታ ቁጥር 9/26/389998/01 ተመዝግቦ የተሰጣቸው በእጃቸው መገኘት የነበረበት ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በ20 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ቅድስት ስናድር ደቦጭ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የይዞታ መለያ ቁጥር AA0000610073094720110 ሴሪ ቁጥር C 104341 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ የኮንደሚኒየም ቤት የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገኖዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር MK-B35-03-1387 ወ/ሮ ሀና ጌታቸው ጎሹ ስም የተመዘገበው የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር (ካርታ ቁጥር) AA000091300009350З1387 ሴሪ ቁጥር 177847 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 25/05/2018 ዓ.ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይገኖዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በልዑልሰገድ ይልማ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ለ/ኩራ/6/1/7/3/136421/00 የሴሪ ቁጥር 1662319 የተሰጠበት ቀን 21/07/2015 ዓ.ም የቦታው ስፋት በሰነድ 63.52 ካ.ሜ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 09 የሆነው መኖሪያ ቤት በልዑልሰገድ ይልማ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ለ/ኩራ/6/1/7/3/136421/00 የሴሪ ቁጥር 1662319 የተሰጠበት ቀን 21/07/2015 ዓ.ም የቦታው ስፋት በሰነድ 63.52 ካ.ሜ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ኦርጅናል የጠፋ ስለሆነ ይዞታ ቤቱን በዕዳ ይገኖዋለሁ፣ አስይገኖዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ካርታውን የምናዘጋጅ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

# የኮከብነት ዘውዱን ማን ያጠልቀው ይሆን?



ፎቶ ከገፀ ድር
ኮከብነቱን የማሸነፍ ዕድል የተሰጣቸው ቪክቶር ኦሲሚህን፣ ሞሀመድ ሳላህ እና አሽራፊ ሀኪሚ

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደሬሽን (ካፍ) የ2025 ለአህጉሪቱ ኮከብ እግር ኳስ ተጫዋች ዘውድ ለማጥለቅ እ.ኤ.አ ህዳር 19 ቀን 2025 በሞሮኮ ቀጠሮ ይዟል፡፡ ካፍ ለ2025 የአፍሪካ የዓመቱ ምርጥ ተጫዋች ሽልማት የተመረጡትን የመጨረሻ አስር ዕጩዎች ይፋ አድርጓል፡፡ ይህ የኮከቦች ስብስብ ባለፈው የውድድር ዘመን በአፍሪካም ሆነ በአውሮፓ ሜዳዎች ድንቅ ብቃትን ያሳዩ ተጫዋቾችን ያካተተ ሲሆን፣ ለአሸናፊነትም ትልቅ ሽሚያ እንደሚኖር ተጠብቋል።

ከእነዚህ ኮከቦች መካከል በሊቨርፑል እግር ኳስ ክለብና የግብፁ ኮከብ ሙሀመድ ሳላህ (በ2017 እና በ2018 አሸናፊው)፣ በፒኤስጂ የውድድር ዘመኑን በአራት ዋንጫዎች ያጠናቀቀውንና የሞሮኮውን ኮከብ አሽራፍ ሀኪሚ፣ እንዲሁም በቅርቡ ወደ ጋላታሳራይ የተዘዋወረውን የናይጄሪያ አጥቂ ቪክቶር ኦስሚህንን እና በቶተንሀም ሆትስፐር መሃል ሜዳውን የተቆጣጠረውን ፔፕ ማታሳርን ይገኙበታል። የባለፈው ዓመት አሸናፊ አድሞላ ሉክማን በዕጩዎቹ ውስጥ መካተት ያልቻለ ሲሆን ባለፉት ሁለት ዓመታት 2ኛ ሆኖ የጨረሰው ሞሮኮአዊው የፒኤስጂ ተጫዋች አችራፍ ሀኪሚ በዚህ ዓመት ትልቅ ግምት ስለማግኘቱ አፍሮ ስፖርት ዘግቧል፡፡

ከአስሩ ዕጩዎች መካከል ስምንቱ የሚጫወቱት በአውሮፓ ከፍተኛ ሊጎች ውስጥ ሲሆን፣ ሁለቱ ኮከቦች (ፊስቶን ማየሌ እና ኡሳማላምሊዊ) በአፍሪካ ውስጥ ባሉ ክለቦች መካከል በሚካሄድ የካፍ ውድድሮች ባሳዩት አስደናቂ ብቃት ዕጩ መሆን ችለዋል። ይህ የአፍሪካ የውስጥ ሊጎችም ዓለም አቀፍ ደረጃ ላይ ያሉ ኮከቦችን ማፍራት መቻላቸውን ያሳያል። እንደዚሁም እነዚህ ተጫዋቾች በዋናነት ዕጩ መሆን የቻሉት በካፍ ሻምፒየንስ ሊግ እና ካፍ ኮንፌዴሬሽን ካፕ ባሳዩት አስደናቂ ብቃት ነው።

ይህ ደግሞ የካፍ ኢንተር ክለብ ውድድሮች ደረጃ ከፍ ማለቱን ያሳያል። እነዚህ ውድድሮች የአፍሪካ ተጫዋቾች ዓለም አቀፍ ትኩረት እንዲያገኙ የሚያስችል ጠንካራ መድረክ መሆናቸውንም እንደሚያረጋግጥ ናይጄሪያዊ የስፖርት ጋዜጠኛ ፒተርስ ኦኮቻ ይገልጻል።

በሌላም በኩል በአፍሪካ ውስጥ ያሉ ክለቦች ተጫዋቾች ዋጋ እና ብቃት ከአውሮፓ ተጫዋቾች ጋር እኩል ተፎካካሪ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። ይህም የአውሮፓ ክለቦች በአፍሪካ የውስጥ ሊጎች ላይ ያላቸውን ክትትል እንዲያጠናክሩ ያደርጋል ተብሏል።

የ2025 የአፍሪካ ኮከብነት ሽልማት ዋነኛ ፍልሚያ በተለይም በሙሀመድ ሳላህ እና ችራፍ ሀኪሚ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ ሳላህ በሊቨርፑል ላለፉት በርካታ ዓመታት ያሳየው የማያቋርጥ ድንቅ ብቃት፣ ግቦችን የማስቆጠርና የማቀበል ችሎታው ለዚህ ሽልማት ዋነኛው መመዘኛ ሆኖ ቀርቧል።

በዕጩዎቹ ዝርዝር ውስጥ ብቸኛ የተከላካይ ስፍራ ተጫዋች የሆነው ሞሮኳዊው ሀኪሚ በበኩሉ በውድድር ዘመኑ ከፒኤስጂ ጋር አራት የሀገር ውስጥ ዋንጫዎችን (የዩኤኤፍኤ ቻምፒየንስ ሊግን ጨምሮ) ማንሳቱ፣ እንዲሁም በሞሮኮ ብሔራዊ ቡድን ውስጥ ወሳኝ ሚና መጫወቱ ትልቁ ጥንካሬው ነው። ሀኪሚ ባለፉት ሁለት ዓመታት በተከታታይ 2ኛ በመሆን ሽልማቱን በቅርብ ርቀት ማጣቱ፣ ዘንድሮም ለዋንጫ ከፍተኛ ግምት እንዲያገኝ አድርጎታል።

በቱርኪዬ ለጋላታሳራይ እግር ኳስ ክለብ እየተጫወተ የሚገኘው ናይጄሪያዊው ቪክቶር ኦስሚህን ሌላኛው ዕጩ ተጨዋች ሲሆን፣ 2023 አሸናፊ የሆነው ኦስሚህን በጣሊያኑ ናፖሊ ያሳየው የግብ ማስቆጠር ችሎታ እና በናይጄሪያ ብሔራዊ ቡድን ያለው ትልቅ ሚና ዕጩ እንዲሆን አስችሎታል። ምንም እንኳን የ2024 የሽልማቱ አሸናፊ አድሞላሉክማን (ከናይጄሪያ) በዕጩነት ባይካተትም፣ ኦስሚህን የሀገሩን ክብር ለማስጠበቅ ወደፍጻሜው ተመልሷል። ወጣቱ ሴኔጋላዊው ፔፕማታሳር በእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ በቶተንሀም ሆትስፐር መሃል ሜዳ ወሳኝ ሚና በመውሰድ ባሳየው የማያቋርጥ የብቃት እድገት ዕጩ ሆኗል። የእሱ ጨዋታዎች በጠንካራው የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ መሃል ሜዳ ያለውን የቴክኒክ ብቃትና ጥንካሬ የሚያንፀባርቁ ናቸው። ከሌላው ሴኔጋላዊ ኮከብ ኢሊማን ንዲያዬ ጋር ሆነው የአዲሱን የሴኔጋል ወጣት ትውልድ ስኬት ይወክላሉ።

የጊኒው ኮከብ ሰር ሁጊራሲ.በ ጀርመን ቡንደስሊጋ የውድድር ዘመን መጀመሪያ ላይ ባሳየው አስደናቂ የግብ ማሽን ብቃት በአውሮፓ ትኩረት ስቧል። የሱ ፈጣን የግብ ብዛት ሪከርዶችን ሰብሯል፤ ይህም በካፍ ምርጫ ኮሚቴ ዘንድ ከፍተኛ ግምት እንዲያገኝ አስችሎታል። የተጫዋቹ ዕጩነት በአውሮፓ መካከለኛ ክለቦች ውስጥም ቢሆን የላቀ ብቃት ማሳየት ለሽልማት ዕጩነት መብቃት እንደሚቻል ያሳያል።

የ2025 የካፍ የአፍሪካ ምርጥ ተጫዋች ሽልማት በሙሀመድ ሳላህ፣ አችራፍ ሀኪሚ እና ቪክቶር ኦስሚህን መካከል የጦፈ ፉክክር እንደሚካሄድ ይጠበቃል። ይሁን እንጂ እንደ ፔፕ ማታሳር እና ሰር ሁጊራሲ ያሉት አዲስ ኮከቦች ያልተጠበቀ ውጤት ይዘው ሊመጡ ይችላሉ።

የ2024 የአፍሪካ የዓመቱ ምርጥ ተጫዋች አሸናፊ የነበረው ናይጄሪያዊው አድሞላ ሉክማን በዕጩዎቹ ዝርዝር ውስጥ አለመካተቱ አግራሞትን የፈጠረ ሲሆን ምንም እንኳን በክለቡ አታላንታ የላቀ የውድድር ዘመን ቢኖረውም፣ የካፍ ኮሚቴ በሌሎች ተጫዋቾች ላይ ትኩረት አድርጓል። ይህ ደግሞ በሽልማቱ ላይ ያለው ፉክክር ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነ ያመላክታል ሲሉ የካፍ ድምጽ ሰጪ ኮሚቴ አባላት ይገልጻሉ።

ካፍ የዓመቱ ምርጥ ተጫዋች ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ዘርፎች የላቀ ብቃትን ያሳዩ ግለሰቦችንና ቡድኖችን ይሸልማል። የዓመቱ ምርጥ አሰልጣኝ አንዱ ሲሆን የ2025 የአሰልጣኝ ሽልማት ትልቅ ግምት ከተሰጣቸው ዕጩዎች መካከል የኬፕ ቨርዴን ብሔራዊ ቡድን በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ዓለም ዋንጫ እንድታልፍ ያደረጉት አሰልጣኝ ቡቢስታ ይገኙበታል። የቡቢስታ ስኬት በትንሽ ሀገር ውስጥ ትልቅ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል የሚያሳይ አብነት ነው። ናይጄሪያዊው ያኑ ኢስተር አኮሮንኮው እና ራሽዳት አጂባዴ በሴት ተጫዋቾች ዘርፍ በዕጩነት የቀረቡ ሆነዋል፡፡

የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደሬሽን ካፍ የራሱን "የአፍሪካ የዓመቱ ምርጥ ተጫዋች" ሽልማት መስጠት የጀመረው በ1992 ሲሆን የመጀመሪያው አሸናፊ ተጨዋችም ጋናዊው የቀድሞ ኮከብ እግር ኳስ ተጫዋች አቤዲ ፔሌ ስለመሆኑ የካፍ መረጃ ያሳያል፡፡ ካፍ የሽልማት ስነ ስርዓቱን ማካሄድ ከመጀመሩ አስቀድሞ ሽልማቱ በፈረንሳይ እግር ኳስ መጽሔት (France Football Magazine) አማካኝነት ከ1970 አንስቶ ይሰጥ ነበር።

የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደሬሽን (ካፍ) "የአፍሪካ የዓመቱ ምርጥ ተጫዋች" ሽልማትን አራት ጊዜ በማሸነፍ ካሜሮናዊው ሳሙኤል ኤቶ እና የአይቮሪ ኮስቱ ያያ ቱሬ ክብረ ወሰኑን ይጋራሉ። ዲዲዬ ድሮግባ፣ ኤልሃጂ ዲዩፍ፣ ንዋን ኮካኑ፣ ሙሀመድ ሳላህ፣ ሳዲዮ ማኔ ያሉ ተጫዋቾች ደግሞ ሁለት ሁለት ጊዜ ያሸነፉ አፍሪካውያን ከዋክብት ናቸው ይላል ካፍ ኦንላይን ድረ- ገጽ መረጃ፡፡